

በሃሩን ያህያ

# ለምን ራስዎን ያታልላሉ?

ትርጉም፦ አህመዲን ጀበል

HARUN YAHYA

AN INVITATION TO THE TRUTH

ደራሲው ሃሩን ያህያ በ450 አርእስት ሥር ከ45 ሺህ ገጾች በላይ ጽሑፎችን ሰንዝበ አብቅተዋል:: ከነዚህ ውስጥ 250ዎቹ መጻሕፍት ሲሆኑ ሥራዎቻቸውም በ57 ቋንቋዎች በዓለም ላይ ተተርጉመው ከ10 ሚሊዮን በላይ ቅጂዎች ተሸጠዋል::

ሥራዎቻቸውን መሠረት ያደረጉ 190 የቪዲዮ ክሮች በቪሲዲና በዲቪዲ ተዘጋጅተው ከ10 ሚሊዮን በላይ ቅጂዎች ለሽያጭ በቅተዋል:: በተለይ «ሰው ከጦጣ ነው የመጣው፤አላህ የለም::» ብለው ለሚያምኑ ሰዎች ምላሽ ባዘጋጇቸው 193 ግሩም መጻሕፍቶቻቸው ይታወቃሉ:: በቅርቡ ከአል-ጀዚራ ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ከነዚህ ሥራዎቻቸው ሁሉ አንዲት ሳንቲም እንደማያገኙ ገልጸዋል::

የሚያነሷቸው ከባባድ ጥያቄዎች ሳይንቲስቶችን ጭምር እጅ በማስጠት ወደ ቁርአን እንዲሳቡ እያደረገ ነው:: አንዳንዶች «ሃሩን ያህያ የሚባል ሰው የለም:: አልያም አንድ ግለሰብ አይደለም::» እስከ ማለት ደርሰዋል::

ሮይተርስ እንደዘገበው ከሁለት ወራት በፊት በአሜሪካ የቀረበው የሥራዎቻቸው ኤግዚቢሽን «አላህ የለም» ለሚሉት ሰዎች አስደንጋጭ ነበር::

Designed & Printed by
Dire Printing Sh.Co. Tel. 011-1552737

# ለምን ራስዎን ያታልላሉ?

ዝግጅት፡- ሀሩን ያህያ

ትርጉም፡- አህመዲን ጀበል

© የአማርኛው ትርጉም መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
All Rights Reserved

ረመዳን 1428 ሂጅራ(ኢስላማዊ አቆጣጠር)
መስከረም 2000 ዓመተ ልደት

## በቅርቡ በአላህ ፈቃድ የሚታተሙ
## የተርጓሚው ሥራዎች

1. ኢየሱስ ፍጡር ወይስ ፈጣሪ? (ዝግጅት)
2. እውን መጽሐፍ ቅዱስ የፈጣሪ ቃል ነውን?(ዝግጅት)

## የታተሙ መጻሕፍት

1. የሴቶች መብትና እኩልነት በኢስላምና በክርስትና(ዝግጅት)
2. ለምን ራስዎን ያታልላሉ?(ትርጉም)

አድራሻ ፦ ሞባይል 0911-17-41-12
ኢሜይል፦ xxbababa88@yahoo.com

## ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
| --- | --- |
| 1. መቅድም | 4 |
| 2. መግቢያ | 6 |
| 3. ዓለም ለምን ተፈጠረች? | 9 |
| 4. ራስዎን ሳያታሉ ከልብ ይመኑ! | 17 |
| 5. የቂን ይኑርዎት | 19 |
| 6. በእኺራ ከልብ ይመኑ! | 23 |
| 7. ሠይጣንን አይታዘዙ! | 25 |
| 8. በቃ! በቃ! ምክንያት አይፍጠሩ! | 31 |
| 9. አቅጣጫ እንዳይስቱ! | 35 |
| 10. በሐሰት አይደለሉ! | 38 |
| 11. ራስዎን በምንድነው የሚያታልሉት? | 41 |
| 12. «በኔ ስላልደረሰ አላውቅም!» | 43 |
| 13. «ልክ ነው ። ግን... አልተመቸኝም! » | 47 |
| 14. «ችግር አለብኝ! ስለዚህ...» | 50 |
| 15. «አላህ «ገፉሩ ረሂም» ነውና ይምረኛል! » | 54 |
| 16. «ጀነትማ እንገባለን...! » | 57 |
| 17. «እኔ ከሌላው በምን ተለየሁ?» | 62 |
| 18. «ሳይንስና ስልጣኔን እየተከተልኩ ነው።» | 64 |
| 19. ራስን ማታለልና መዘዙ! | 67 |

بسم الله الرحمن الرحيم

## መቅድም

ይህ መጽሐፍ «WHY DO YOU DECEIVE YOURSELF?» በሚል ርዕስ ሀሩን ያህያ ካዘጋጁት መጽሐፍ «ለምን ራስዎን ያታልላሉ?» በሚል ወደ አማርኛ የተመለሰ ነው:: መጽሐፏ ራሳቸውን በተለያዩ ምክንያቶች እያታለሉ ላሉት እያሉ ግለሰቦች ቀም ብለው በማሰብ፣ስለ ራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ በማሰላሰል ራሳቸው ከማታለል እንዲቆጠቡ ታስገነዝባለች::ራሳቸውን እያታለሉ እንዳልሆኑ የሚያስቡትን በሞላ ህይወታቸውን ዳግም እንዲመረምሩ ትጣራለች:: ለሁሉም ሰው የንቃት ደወል ታሰማለች:: ይህን መጽሐፍ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተርጉሜ ለአንባብያን ሳቀርብ በእንግሊዝኛው ላይ ያልነበረውን የአረብኛውን ቁርአንን ጨምሬያለሁ:: አንዳንድ ቦታ ላይ የራሴን አገላለጽ ተጠቅሜያለሁ::

ደራሲው ሃሩን ያህያ እ.ኤ.አ በ1956 በአንካራ ቱርክ የተወለዱ ሲሆን ምንም እንኳ የሚታወቁት በብዕር ስማቸው«ሃሩን ያህያ» ቢሆንም ትክክለኛ ስማቸው አድናን ኦክታር ነው:: ስለ ሳይንስና እምነት፣ ስለኢስላማዊ አስተምህሮቶች፣ ስለ ክርስትናና አይሁድ እምነቶች እንዲሁም በሌሎች ልዩ ልዩ አርእስቶች ላይ የጻፏቸው መጻሕፍትና በራሪ ወረቀቶች ብዛታቸው 450 የደረሱ ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 250ዎቹ የታተሙ መጻሕፍት ናቸው:: ኢስላምንና ሳይንስን አስመልክቶ በተለይ የዳርዊን ቲዎሪ ውድቅ መሆኑን ለማሳየት 193 መጻሕፍት ደርሰዋል::ሥራዎቻቸው በዓለም ታላላቅ 57 ቋንቋዎች ተተርጉመዋል::እነዚህ መጻሕፍቶቻቸው በአርባ ሀገራት በሚገኙ አሳታሚ ድርጅቶች አማካኝነት በዓለም ላይ ተሰራጭቷል:: በቱርክ ቋንቋ ከስምንት ሚሊዮን በላይ እንዲሁም በሌሎች ቋንቋዎች ከሁለት ሚሊዮን በላይ ቅጂ መጻሕፍቶቻቸው ተሸጠዋል::ከመጻሕፍት በተጨማሪ ከ190 በላይ ዶኩመንተሪ ፊልሞች በሥራዎቻቸው ላይ ተመስርተው ሲሠሩ ከአስር ሚሊዮን በላይ ቅጂዎችም ተሸጠዋል:: ፊልሞቹም ከሀያ ሀገራት በሚሰራጩ አንድ መቶ

ሳተላይት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ለእይታ በቅተዋል:: ሥራዎቻቸው በተለያዩ ቋንቋዎች በ40 የኢንተርኔት ድህረ-ገጾችም ይሰራጫሉ::ሃሩን ያህያ ከ2000 በላይ መጻሕፍት በሚገኙበት በግል ቤተመጻፍታቸው ውስጥ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በማንበብና በመጻፍ ያሳልፋሉ:: ኦገስት 6/2007 ከአልጀዚራ ሳተላይት ቴሌቪዢን ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ በሥራቸው ምክንያት ጊዜ ስለሌላቸው ትዳር እንዳልመሰረቱ ተናግረዋል:: ከነዚህ ሁሉ ሥራዎቻቸው አንዲት ሳንቲም ሳያገኙ በነጻ ያለ ኮፒ ራይት ለአታሚዎች እንደሚሰጡም አብራርተዋል::ለራሳቸው ባይነግዱም በተቀጣሪ ሠራተኛ ንግድ እንቅስቃሴያቸውን ያካሂዳሉ:: በግላቸው እጅግ የናጠጡ ሀብታም ሲሆኑ ገንዘባቸውን ለዲኑ ሥራ አውለውታል:: በአጠቃላይ ከኚህ ታላቅ ምሁር መጽሐፍ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ:: ምንዳቸውንም አላህ ያብዛላቸው:: እኛንም ዲኑን የሚከድም ሰው አላህ ያድርገን::

አህመዲን ጀበል
ረመዳን 1428 ሂጅራ
አዲስ አበባ

## መግቢያ

ሀይማኖተኛ ባልሆኑ ህብረተሰቦች ውስጥ የሚኖሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች የአኗኗር ዘይቤና የህይወት ግብ በአብዛኛው አንዱ ከአንዱ ተመሳሳይ ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ የተለያዩ ቢመስሉም በመጨረሻ እስከ አሁን ድረስ በእውነት አንድ ናቸው:: ምክንያቱም የሚኖሩባቸው ሁኔታዎች ቢለያዩም ፍላጐታቸው፣ የሚወዷቸው ነገሮች፣ ዕቅዶቻቸው፣አስተሳሰባቸው ለዚህ ዓለም ህይወት ያላቸው ግብ በተግባር ተመሳሳይ ናቸው:: የአንድ ሰው ፀባይ ቅርፅ መያዝ የሚጀምረው በህፃንነቱ የእድሜ ዓመታት ነው:: በእነዚህ የእድገት እርከኖች ህፃናት ያሉበትን ዓለም ባለማወቅ በጣም ነፃ የሆነ ኑሮ ይኖራሉ:: ከዛ በኋላ የት/ቤት ህይወትን በአስራዎቹ እድሜዎች ይጋፈጣሉ:: በእነዚህ ጊዜያትና ዓመታት ፍላጐታቸው በተለያዩ ብዙ ጓደኞች በዙሪያቸው መከበብ፣ በትምህርት ቤት ታዋቂ መሆን፣ ፋሽን ተከታይ መሆን እና ለሕዝብ መታየት ላይ ይወሰናሉ:: ከዛ በኋላ ትምህርት አልቆ የስራ ህይወት ይጀመራል:: በስራ ህይወት ውስጥ አንድ ሰው በሙያው ራሱን ለማሻሻል ብዙ ገንዘብ ለማፍራት እና ለእድገት ለመብቃት ይሞክራል:: ያለውን ጊዜና ኃይል ሁሉ ለዚህ ይሰጣል:: በተመሳሳይ ጊዜ አንደ ሚስት ፈልጐ አግብቶ እንዲሁም ቤተሰብ ለመመስረት ይሞክራል:: በእሱ ዓይኖች፣በዓለም ላይ በጣም አስፈላጊው ነገር ደስተኛ የሆነ ቤተሰብ ማቋቋም ነው::በእጭሩ ይወለዳል፣ ወደ ሥራ ህይወት ይገባል፣ያለውን ሁሉ ችሎታ ተጠቅሞ ገንዘብ እና ክብር ለማግኘት ይሞክራል፣በዛ ላይ ልጆቹን ይድራል፣ በመቀጠልም አያት ይሆናል::እናም በእነዚህ ዓላማዎች እና ሃሳቦች ተወስኖ ይኖራል:: ዓመታት በፍጥነት ይነጉዳሉ:: ከዛ በመቀጠልም በድንገት፣በጣም ትልቁንና ማምለጥ የማይቻለውን የህይወት እውነታ ይጋፈጣል:: የመሞቻ ጊዜ ይመጣል:: በዚህ ጊዜ እድሜው ምንም ይሁን ምን ከዚህ ዓለም ወደ ቀጣዩ ዓለም ሳይወድ በግዱ ይሻገራል:: እስከዛች ደቂቃ ድረስ ስለሞት በጣም ትንሽ ወይም ከነጭራሹ ምንም አያስብም:: በተለያዩ ጊዜያት ብዙ ሰዎች በአካባቢው ሲሞቱ አይቷል፣ የራሱን ሞት ግን ምንጊዜም እሩቅ አድርጐ ያስባል:: በህይወት ዘመኑ ሙሉ የሞትን ገሃዳዊ እውነታ ሳያስተውል ይኖራል:: ምክንያቱም

አእምሮው በዓለማዊ ነገሮች ስለሚወጠር ነው:: በመሆኑም ስለ ማይቀረው ሞት የነበረው አመለካከት በቂ ዝግጅት እንዳያደርግ መሰናክል ሆኖበታል:: በዚህም ምክንያት መሰረተ ቢስ አስተሳሰቦችን እንደ ጥሩ እድል አድርጎ ያያል::የአላህ(ሱ.ወ) ቀጠሮ የሆኑት ጀነት እና ጀሃነም ከመሳሰሉ አንገብጋቢ አጀንዳዎችን ወደ ጎን ሲላቸው ይስተዋላል:: ከእነዚህ እውነታዎች በመነሳት የህይወትን እውነተኛ ዓላማ ይስታል:: መረዳትም ያቅተዋል:: በዓለም ላይ በሚኖርበት ጊዜ መላ ዓላማዎቹ፣ እቅዶቹ እና ሐሳቦቹ አስፈላጊ ከሆነው ተልዕኮው በተለየ መልኩ አኩይ ስሜቱን ሲያሳድድ ይኖራል:: ዓለማዊ በሆኑት ነገሮች በጣም ጠንክሮ ይሠራል:: ነገር ግን ከዛ ባለፈ ለመጻኢው ዓለም ሙሉ በሙሉ ዝግጁ አይሆንም:: በዚህ ሁኔታ ሲዋልልና ሲባዝን ከሞት ጋር ይፋጠጣል:: ሳይጠብቀው፣ ሳይዘጋጅበት እና በድንገት ከእንቅልፉ ነቅቶ እንደሚደናበር ሰው ሆኖ ያገኘዋል:: በመጨረሻም ፀፀት ይሰማዋል:: ወደ ኋላ ሊመለስ ይፈልጋል፤ ነገር ግን አሁን በጣም ጊዜው ዘግይቷል ይባላል::አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ያለውን ከንቱና ከሳሪ ሰው እጣፈንታ በሱረቱ አል-ሰጅዳ ላይ እንደሚከተለው ይገልፃቸዋል:-

﴿وَلَوْ تَرَىٰٓ إِذِ ٱلْمُجْرِمُونَ نَاكِسُوا۟ رُءُوسِهِمْ عِندَ رَبِّهِمْ رَبَّنَآ أَبْصَرْنَا وَسَمِعْنَا فَٱرْجِعْنَا نَعْمَلْ صَٰلِحًا إِنَّا مُوقِنُونَ﴾ ﴿وَلَوْ شِئْنَا لَءَاتَيْنَا كُلَّ نَفْسٍ هُدَىٰهَا وَلَٰكِنْ حَقَّ ٱلْقَوْلُ مِنِّى لَأَمْلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنَ ٱلْجِنَّةِ وَٱلنَّاسِ أَجْمَعِينَ﴾[1]

*«በናንተ የተወከለው መልአክ ሞት ይገድላችኋል፣ከዚያም ወደ ጌታችሁ ትመለሳላችሁ በላቸው:: አመጸኞችም በጌታቸው ዘንድ ራሳቸውን ያቀረቀሩ ኾነው፡- ጌታችን ሆይ! አየን፤ ሰማንም መልካምን እንሠራለንና(ወደ ምድር ዓለም) መልሰን፤ እኛ አረጋጋጮች ነን፣(የሚሉ ሲኾኑ) ብታይ ኖሮ (አስደንጋጭን ነገር ታይ ነበርክ»(ሱረቱ አስ-ሰጅዳህ 31:11-12)*

ስለዚህ ሰው በእንዲህ ባለሁኔታ ህይወቱ እንዴት ይደመደማል? እንዴት እውነታውን ማስወገድ ይችላል? ጊዜው ከደረሰ በኋላ ምንም መፍትሄ በሌለው ነገር መፀፀት ምን ይበጀዋል? እንዴት እዚህ ዓለም ላይ

[1] سورة : السجدة

የተፈጠረበትን ዓላማ ሊዘነጋ ወይም ሊረሳ ይችላል? አንዳንድ ሰዎች የህይወትን እውነታ ለመዘንጋት እና ራሳቸውን ለማፅናናት የሚጠቀሟቸው የተለያዩ መከላከያ መንገዶች በምናባቸው ሊፈጥሩ ይችሉ ይሆናል:: በሌላ አገላለጽ ራሳቸውን ሊያታልሉ ይችላሉ::ራሱን የሚያታልል ሰው ሁሉንም እውነታዎች ሞትንም ጨምሮ ሁሉንም ኃላፊነቶች ማምለጥ እንደሚችል ያስባል::እንደ እውነቱ ከሆነ ራስን ማታለል መፍትሄ አይሆንም:: በተቃራኒው[1] በዚህ ዓለም ላይ የመኖርን እውነተኛ ምክንያት ያለመረዳት በቀጥታ ሰውየውን ወደ ጀሃነም ወደሚወስደው መንገድ እንዲጓዝ ያደርገዋል::አንድ ሰው ይህንን እውነታ ለመፈፀም የሚያስፈልገው እውነቱን በመዘንጋት ራሱን ማታለልን በመተው አላህ(ሱ.ወ) በዚህ ዓለም የፈቀደለትን ጊዜ የተቸረውን ያህል መጠቀም ያሻል::

ማን ፈጠረህ? ራስህን ልታታልል ትችላለህን? በዚህ ሁኔታ እያለህ የሞትን ፈተና ላለመጋፈጥ እና ለዘላለም ላለመፀፀት ምን ዋስትና አለህ?

ቁርአን በዚህ ዙሪያ ምን እንደሚል ተምረሃል? በጣም አስብበት:: ምክንያቱም በቁርአን ውስጥ ሰዎች እንዴት ራሳቸውን እንደሚያታልሉና እውነታውን እንደሚዘነጉ ተጠቅሷል:: ለማንም በመሞቻ ሰዓት ነቅቶ እና ተነስቶ እውነታውን ማየት ምንም እንደማይፈይድ እንዳትረሳ::አላህ(ሱ.ወ) ግልፅ የሆነ ማስጠንቀቂያ ስለዚህ ጉዳይ ሰጥቶናል:-

﴿وَلَن يُؤَخِّرَ ٱللَّهُ نَفْسًا إِذَا جَآءَ أَجَلُهَا ۚ وَٱللَّهُ خَبِيرٌۢ بِمَا تَعْمَلُونَ﴾[2]

*«ማንኛይቱንም ነፍስ (የሞት) ጊዜዋ በመጣባት ጊዜ አላህ በፍፁም አያቆያትም:: አላህም በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው::»(ሱረቱ አል-ሙናፊቁን:28-11)*

---

[2] سورة : المنافقون

## ዓለም ለምን ተፈጠረች?

እስኪ ለአንድ አፍታ በጉዳና ላይ ከሆንክ፣አካባቢህን እይ፡፡ በቤት ውስጥ ከሆንክ በመስኮት ወደ ውጭ ቃኝ፡፡ በዚች ደቂቃ ስለማታያቸው የመሬት ክፍሎች ሁሉ አስብ፡፡ውቅያኖሶችን፣ሐይቆችን እና ተራሮችን እንዲሁም ከምታያቸው ሰዎች ውጭ ስላሉት በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች እንዲሁም በህይወትህ ሙሉ አጋጥመውህ ስለማያውቁት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ፍጥረታት አስብ፡፡ በመጨረሻም፣ዓለምን ምድርን ስለ ህዋ አስብ፣ስፋቱ ወሰን የለሽ ስሆነው ጠፈር ከቢሊዮን ጋላክሲዎቹና በውስጡ ካሉት ከመቶ ሚሊዮን ኮከቦች፣ፕላኔቶች፣ ኮሚቶች እና በጣም ብዙ የሆኑ ግዑዝ አካላትን ያካተተውን ፍጥረተ ዓለም ቆም ብለህ አስብ፡፡

አሁን በንፁህ ልብህ አእምሮህን አዳምጥ እና አስብ፡፡ ለምን እና እንዴት እነዚህ ሁሉ ፍጥረታት ኖሩ? ህይወት ያላቸውም የሌላቸውም በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በዚህ እንከን የለሽ ስርዓት ውስጥ ሰላማዊ የሆነ ኑሮ በአንድ ላይ ሊያካሂዱ እንዴት ቻሉ? በዓለማችን ላይ ይህ የሆነበት መለኮታዊ ዓላማ እና ከፍተኛ የሆኑ ተልዕኮ ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ የሚስተዋለው ለምንድነው? በተለይም በሰው ልጅ በምድራዊ ዓለም ገዥና ሀላፊ ሊሆን የቻለበት ምክንያቱ ምንድነው? እነዚህ ሁሉ ነገሮች ምንድን ናቸው? በተለይም የሰው ልጅ፣በምድራችን ላይ ንፁህ ህሊና የተሰጠው ብቸኛ ፍጡር ፣ዓለማችንን ለማስተዳደር የታጨ የአምላክ አምባሳደር ሆኖ ለምን ተመረጠ? ነገሩ ይህ ከሆነ የሚሰራዉ ሥራ ምንድነው ?

የፍጥረትን እውነተኛ ምክንያት አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን ላይ ተናግሯል፡፡ ይህም የፈጠረን እንድንገዛው ብቻ ነው፡፡ይህንን በሚከተለው የቁርአን ጥቅስ እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡-

﴿وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ﴾[3]

*«ጋኔንና ሰውንም ሊገዙኝ እንጂ ለሌላ ለልፈጠርኳቸውም፡፡»(አዘ-ዛሪያት 51:56)*

---

[3] سورة: الذاريات

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰው ዓለማችን ከነሁሉም ይዘቱ ጋር ማለትም ባህሮች፣ ውቅያኖሶች፣ሐይቆች፣ዛፎች፣ተራራሮች እና ሁሉም ፍጥረታት ሰዎች የሱን ትእዛዝ ማክበራቸውንና አለማክበራቸውን ለማረጋገጥ በአላህ(ሱ.ወ) የተፈጠሩ ናቸው።ዓለማችን እና በውስጧ የያዘቻቸው ነገሮች ሁሉ ፕላኔቶች፣ ኮከቦች እና ሌሎች ግዑዝ አካላት ሰዎች የአምላክን ታላቅነትና የተትረፈረፈ እዝነት እንዲያዩ እና እንዲያመሰግኑት ነው የተፈጠሩት።ልክ እንዲሁ የሰው ልጅ በህይወቱ ውስጥ የሚያጋጥመው እያንዳንዱ ክስተት እንዲሁም ራሱን የሚያገኝበት ሁሉም ቦታዎች በዚህ ዓለም ላይ ሲኖር ከሚፈተንበት ፈተናዎች መካከል ናቸው።በሚከተለው የቁርአን ጥቅስ አላህ(ሱ.ወ) የሰው ልጆችን የፈጠረበት ዓላማና በዓለም ላይ መኖራቸው እነርሱን ለመፈተን ነው ይላል፡-

﴿ إِنَّا خَلَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ مِن نُّطْفَةٍ أَمْشَاجٍ نَّبْتَلِيهِ فَجَعَلْنَٰهُ سَمِيعًۢا بَصِيرًا ﴾[4]

*«እኛ ሰውን (በሕግ ግዳጅ) የምንሞክረው ስንኾን ቅልቅሎች ከኾኑ የፍትወት ጠብታ ፈጠርነው፤ሰሚ ተመልካችም አደረግነው።»(ሱረቱ አል-ኢንሳን(ዳህር):2)*

በዚህ የመፈተኛ አካባቢ፣አንድ ሰው የአላህን (ሱ.ወ) መመሪያ እንዲሁም የከለከላቸውን ነገሮች በማንኛውም ሰዓት የመከተልና የመተግበር ኃላፊነት አለበት። የአምላክን ፈቃድ በሚያገኝበት መንገድ መሥራት አለበት። ይህንን ኃላፊነት የሚጥሱ ግለሰቦች የተጣለባቸውን ግዴታ አልተወጡም።ውጤቱውም የከፋ የሆነውን ዘልአለማዊ የጀሃነም ቅጣት ይሆናል ተብሎ በቁርአን ውስጥ ተነግሮናል። ምክንያቱም አላህ(ሱ.ወ) ለለገሳቸው ጸጋዎች ሁሉ ከፍተኛ ውለታቢስነት ስላሳዩት ነው።

ምንም እንኳን ቢሆን ብዙ ሰዎች በአንድ አይነት ሁኔታ ለዚህ ነገር ምንም ትኩረት የማይሰጡ ናቸው። የህይወታቸውን ትክክለኛ ዓላማ በመርሳት፣ ለራሳቸው ደመነፍሳዊ ፍላጎቶች ቅድሚያ ይሰጣሉ።የተለያዩ ከንቱ ዓላማዎች ቢዚ ሲያደርጓቸው ይኖራሉ።ለአያሌ ወራት ብሎም ለዓመታት ዓለማዊ ለሆኑት ፍላጎቶቻቸው ሲባዝኑ ይስተዋላል። ነገር ግን ለአላህ(ሱ.ወ) ያላቸውን ኃላፊነት ፈፅሞ ማሰብ አይፈልጉም። በዓለማችን ላይ ለአላህ(ሱ.ወ)

[4] سورة : الإنسان

ያለመታዘዝ መዘዙ ጀሃነም መሆኑን በጭራሽ ይዘነጉታል፡፡ ነገር ግን በምድር ላይ የሚኖር አንድም ሰው ቢሆን እነዚህን እውነታዎች «አላውቃቸውም ነበር፡፡» ሊል አይችልም፡፡ ይህንንም አምላክ በሁሉም ዘመን ለነበሩ ሰዎች ከነብዩ አደም(ዐ.ሰ) ጀምሮ ፍላጎቱን ይፋ አድርጓል፡፡ እሱን እንዲያውቁ የሚያደርጋቸውን መጻሕፍት ልኮላቸዋል፡፡ እንዲሁም እንዴት ሊከተሉት እንደሚገባ አስተምሯቸዋል፡፡ በተጨማሪም ነብያቶቹን ልኮላቸዋል፡፡ከዚህ ሁሉ በኋላ ለሕዝቦቹ «አናውቅም ነበር፡፡» ማለት አይችሉም፡፡መረጃ ቀምባቸዋል፡፡ ይህ የቁርአን ጥቀስ ይህንን እውነት ያስታውሰናል፡-

﴿ رُسُلًا مُّبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى ٱللَّهِ حُجَّةٌۢ بَعْدَ ٱلرُّسُلِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمًا ﴾

*«ከመልክተኞች በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር አብሳሪዎችንና አስፈራሪዎች የሆኑን መልክተኞች (ላክን)[1] አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡»(አል-ኒሳእ 4:165)*

በአላህ(ሱ.ወ) የተላኩት ነቢያት ወደ ምድር የላካቸው መለኮታዊ መጻሕፍት እንዲሁም ለአማኝ ሕዝቦች የተሰጡ ምክሮች ለዚህ አዋጅ(ትምህርት) ማነሳሻ ናቸው፡፡ በዓለማችን የታሪክ ማህደር በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸው አማኞች ሌሎች ሰዎችን የአላህን(ሱ.ወ) እምነት እንዲቀላቀሉ ጥሪ አድርገዋል (ጋብዘዋል)፡፡ እንዲሁም የጀሃነም እና የጀነት መኖርን በመጥቀስ ስለ ዓለም ፍፃሜ ወይም ቂያማ ቀን አስጠንቅቀዋል፡፡

ከዚህ ጉን አንድ ሰው ስለተፈጠረበት እውነተኛ ዓላማ በጭራሽ ሰምቼ አላውቅም! በማንም ስለዚህ ጉዳይ ተመክሬም ሆነ የአምላክን መጽሐፍ አንብቤ አላውቅም አለ ብለን እንውሰድ፡፡በመግቢያችን ላይ እንደጠቀስነው ስለፍጥረት እና በአካባቢው ስላለው አንድ ወጥና ህብር ያለው ፍጥረት በማሰብ ይህ ግለሰብ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በአንድ ልዕለ ኃያል ለተወሰነ ዓላማ የተፈጠሩ(የመጡ) መሆናቸውን እንኳን ማወቅ አይሳነውም፡፡ አንድ ህይወት ያለው ሰው እሱ እራሱ የተፈጠረ መሆኑንና ከፈጣሪያችን ዘንድ ያለበትን

---

[1] سورة: النساء

ኃላፊነት መረዳት ይችላል:: ምክንያቱም አምላክ ሰዎችን የፈጠረው ትክክለኛ እና እውነተኛ የሆነውን መንገድ ከሚለዩበት አእምሮ ጋር ነው::ህሊናቸውን እያዳመጡ በአካባቢያቸው የሚገኘውን ነገር የሚመዝኑ ሰዎች፣እነዚህ እውነታዎች ላይ ሊደርሱ ይችላሉ::ለዚህ ታላቅ ተምሳሌት የሚሆነን ስለ ነቢዩ ኢብራሂም(ዐ.ሰ) በቁርአን የተነገረን ታሪክ ነው፡-

وَكَذَٰلِكَ نُرِيٓ إِبۡرَٰهِيمَ مَلَكُوتَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَلِيَكُونَ مِنَ ٱلۡمُوقِنِينَ ﴿٧٥﴾ فَلَمَّا جَنَّ عَلَيۡهِ ٱلَّيۡلُ رَءَا كَوۡكَبٗاۖ قَالَ هَٰذَا رَبِّيۖ فَلَمَّآ أَفَلَ قَالَ لَآ أُحِبُّ ٱلۡأٓفِلِينَ ﴿٧٦﴾ فَلَمَّا رَءَا ٱلۡقَمَرَ بَازِغٗا قَالَ هَٰذَا رَبِّيۖ فَلَمَّآ أَفَلَ قَالَ لَئِن لَّمۡ يَهۡدِنِي رَبِّي لَأَكُونَنَّ مِنَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلضَّآلِّينَ ﴿٧٧﴾ فَلَمَّا رَءَا ٱلشَّمۡسَ بَازِغَةٗ قَالَ هَٰذَا رَبِّي هَٰذَآ أَكۡبَرُۖ فَلَمَّآ أَفَلَتۡ قَالَ يَٰقَوۡمِ إِنِّي بَرِيٓءٞ مِّمَّا تُشۡرِكُونَ ﴿٧٨﴾ إِنِّي وَجَّهۡتُ وَجۡهِيَ لِلَّذِي فَطَرَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ حَنِيفٗاۖ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ﴿٧٩﴾[6]

*«እንዲሁም ኢብራሂምን(እንዲያውቅና ከአረጋጋጮችም ይሆን ዘንድ) የሰማያትንና የምድርን መለኮት አሳየነው::ሌሊቱም በርሱ ላይ ባጨለመ ጊዜ ኮከብን አየ፣ይህ ጌታዬ ነው አለ፣በጠለቀም ጊዜ፣ጠላቂዎችን አልወድም አለ::ጨረቃንም ወጪ ሆና ባየ ጊዜ፡- ይህ ጌታዬ ነው አለ፣በገባም ጊዜ ጌታዬ (ቅኑን መንገድ) ባይመራኝ በእርግጥ ከተሳሳቱት ህዝቦች እሆናለሁ አለ::ፀሐይንም ጮራዋን ዘርግታ ባየ ጊዜ፡-ይህ ጌታዬ ነው አለ:: በገባችም ጊዜ ወገኖቼ ሆይ! እኔ ከምታጋሩት ሁሉ ንጹህ ነኝ አለ::»(ሱረቱል አንዓም:75-79)*

እላይ ካለው ታሪክ እንደምንረዳው፣ነብዩ ኢብራሂም(ዐ.ሰ) የአላህን(ሱ.ወ) መኖር የተረዱት፣የሰማይና የምድርም ፈጣሪ እንዲሁም እሱን ብቻ መገዛት እንዳለባቸው የተረዱት ህሊናቸውን በማድመጥ ብቻ ነበር:: ከዚህ ምሳሌ እንደምንረዳው ሰዎች አላህን(ሱ.ወ) ማምለክ እንደሚገባቸው ለማወቅ በአዕምሮ ጓዳቸው አካባቢያቸውን መቃኘት (ማየት) ብቻ ይበቃቸዋል::ነገር ግን አላህ(ሱ.ወ) በቸርነቱ ስለተፈጠሩበት ዓላማና እና እንዴት እሱን ማምለክ

---

[6] سورة: الأنعام

እንዳለባቸው በተለያየ መንገድ ከዝርዝር መረጃ ጋር አቅርቦላቸዋል:: ያለ ጥርጥር ይህ አላህ(ሱ.ወ) ለሰው ልጆች ያለውን ወሰን የለሽ እዝነት፣ ምህረት እና ውዴታ የሚያሳይ ምልክት ነው::እንዲሁም የሰሙ አሊ-ሃዲ መገለጫ ነው:: ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ጉዳና እንዲከተሉ የሚያደርግ መመሪያ ነው::በዓለም ላይ፣ አላህ(ሱ.ወ) ሰዎች ይህንን እንዲያውቁ ለማድረግ ብዙ ዘዴዎችን ተጠቅሟል:: እንዲሁም እነዚህን ምልክቶች እንዲረዱ ጊዜ ሰጥቷቸዋል:: ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ፣ ሰዎች በነፃነት ህሊናቸውን ተጠቅመው እነዚህን ምልክቶች በግልፅ የሚያዩትን እውነታ፣ ዓለምን ሙሉ መመዘን ሲሳናቸው ይስተዋላል:: እንደ እነዚህ አይነት ሰዎች ምንም እንኳን ይህ ፀባያቸው ለዘላለም ቀጣይ በሆነው ህይወታቸው ላይ ጉዳት ቢያደርስባቸውም ከእነዚህ ሁሉ እውነታዎች ተፃራሪ የሆነ ባህሪን ያሳያሉ::

እስቲ አንዴ ወደ ራስህ ተመልከት:: ህፃናት፣ በአስራዎቹ እድሜ የሚገኙ ወጣቶች ፣ወንዶች፣ሴቶች፣አዛውንቶች፣ አብዛኛዎቹ የቀን ተቀን ሥራቸውን የሚያካሂዱት ልክ ሞትና የፍርድ ቀን እንደማያጋጥማቸው ሆነው ነው:: አንዱ የት/ቤት አውቶቢስ ለመያዝ ሲሞክር፣ አንዱ ከሥራ እንዳይዘገይ ወደ መኪናው ሲጣደፍ፣ ሌላው ማታ ለሚመጡ እንግዶቹ በዕቃ ግዥ ሲወጠር፣ ሌላኛው ደግሞ በቅርብ ሳምንታት ውስጥ ለሚወሰድ የልጅ ልጁ ዝግጅት ሲያደርግ::በእርግጥ እነዚህ ነገሮች ሁሉም ሰው የተጠመደባቸውን የተለመደውን ኑሮውን ሲያደርግ የሚተገብራቸው ናቸው::በግልፅ ሁሉም በጣም የተለመዱ ናቸው::ችግሩ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ተፃራሪ በሆነ አእምሮአቸው ውስጥ ይዋኙታሉ::እንዲሁም አላህ(ሱ.ወ) ከእርሱ ጋር መሆኑን ለማሰብ ፋታ የላቸውም::በተጨማሪም ሞት በፍጥነት እንደ ሚመጣባቸው እና በአላህ(ሱ.ወ) ፊት እርሱን ለዘነጉባቸው ዓመታት በተጠያቂነት እንደሚቆሙ በማሰብ ካሉበት ዝቅጠት አይመለሱም::ስለዚህ እንዴት ሰዎች እንደዚህ ግልፅ ከሆኑ እውነታዎች ጭፍን ይሆናሉ? ምንም እንኳን ስለ አምላክ መኖር ብዙ ምልክቶች ቢኖሩም እንዲሁም በርሱ ፊት ምንም የሚታደጋቸው ኃይል እንደሌላቸው እያወቁ? እንዴት ለእውነቱ አይናቸውን ይጨፍናሉ? ልክ ሰጉን እንገቷን አሸዋ ውስጥ እንደምትቀብረው

በተለይም እንደዚህ አይነት ፀባይ በሚያስከትለው ጉዳትና ኪሳራ ሲጠቁ መልሳቸው እንዴት ይሆን ይሆን?

ያለምንም ጥርጥር በአብዛኞዎቹ ሰዎች ላይ ይህ የሚደርስባቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ባለማወቃቸው አይደለም:: ነገር ግን ህሊናቸው ትክክለኛ የሆነውን ነገር ቢነግራቸውም እራሳቸውን ስለሚያታልሉ ነው:: «ማታለል» የሚለውን ቃል የምንጠቀመው፣ እነዚህ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ላይ የመረዳት ወይም የድንቁርና ችግር የለባቸውም:: ችግሩ ሰዎች ለዓለማዊ እውቀት በሚሰጡት ደረጃ(ልክ) እውነታውን በትንንት መቅረብ አለመቻላቸው ነው:: ምክንያቱም ከዛ በኋላ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ስለሚከዱት ነው:: አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ ስለእነዚህ ሰዎች እንደሚከተለው ይነግረናል:-

۝ سَأَصْرِفُ عَنْ ءَايَٰتِىَ ٱلَّذِينَ يَتَكَبَّرُونَ فِى ٱلْأَرْضِ بِغَيْرِ ٱلْحَقِّ وَإِن يَرَوْا۟ كُلَّ ءَايَةٍ لَّا يُؤْمِنُوا۟ بِهَا وَإِن يَرَوْا۟ سَبِيلَ ٱلرُّشْدِ لَا يَتَّخِذُوهُ سَبِيلًا وَإِن يَرَوْا۟ سَبِيلَ ٱلْغَىِّ يَتَّخِذُوهُ سَبِيلًا ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ كَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا وَكَانُوا۟ عَنْهَا غَٰفِلِينَ ۝[7]

***«እነዚያን ያለ አግባብ በምድር ላይ የሚኮሩትን ከአንቀጾቼ በእርግጥ እዞራቸዋለሁ:: ታዓምርንም ቢያዩ በርሷ አያምኑም፣ቅንንም መንገድ ቢያዩ መንገድ አድርገው አይይዙትም፣ግን የጥመትን መንገድ ቢያዩ መንገድ አድርገው ይይዙታል፣ይህ ከእነሱ በአንቀጾቻችን ስለ አስተባበሉና ከእርሱዋም ዘንጊዎች ስለሆኑ ነው::እነዚያም በአንቀጾታችንና መጨረሻይቱን ዓለም በመገኘት ያስተባበሉት ሥራዎቻቸው ተበላሹ፣ይሠሩት የነበረውን እንጂ ይመነዳሉን?»(ሱራ አል-አዕራፍ:146-147)***

۝ ٱلَّذِينَ يَسْتَحِبُّونَ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا عَلَى ٱلْءَاخِرَةِ وَيَصُدُّونَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ وَيَبْغُونَهَا عِوَجًا أُو۟لَٰٓئِكَ فِى ضَلَٰلٍۭ بَعِيدٍ ۝[8]

---

[7] سورة : الأعراف
[8] سورة: إبراهيم

*«እነዚያ የቅርቢቱን ሕይወት ከመጨረሻይቱ ህይወት ይበልጥ የሚወዱ፣ከአላህም መንገድ የሚያግዱ መጣመሟዋንም የሚፈልጉዋት ናቸው፣እነዚያ በሩቅ ስህተት ውስጥ ናቸው።» (ሱረቱል ኢብራሂም፡3)*

እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን በማታለልና ዓይናቸውን በመጨፈን እንዲሁም ምክርን ባለመስማትና ራሳቸውን በማታለል ተዘናግተው ሳሉ ሞት ስለሚመጣባቸው ሰዎች አላህ(ሱ.ወ) በሌላ ጥቅስ እንዲህ ይላል ፡-

اَقْتَرَبَ لِلنَّاسِ حِسَابُهُمْ وَهُمْ فِي غَفْلَةٍ مُّعْرِضُونَ [9] ۝

*«ለሰዎች እነሱ በዝንጋቴ ውስጥ(መሰናዳትን) የተው ኾነው ሳሉ ምርመራቸው ቀረበ።» (ሱረ አል-አንቢያ፡1)*

የሰው ልጅ የቂያማ ቀን በሕይወት ዘመኑ በነበረበት ጊዜ ለፈፀመው ነገር ለጥያቄ እንደሚቀርብ ግልፅ ነው።ሙሉ በሙሉ ተዓራሪ ሆኖ መቅረት እና ተዓራሪ ከሆንው አመለካከቱ ለመውጣት/ለማምለጥ ምንም ሙከራ አለማድረግ በጣም ከንቱነትና ይቅር የማይባልለት ድርጊት ነው።ከዚህ በመቀጠል ይህ ድርጊት ትክክለኛው ፍትሕ እንዲከፈለው የአምላክ ፈቃድ ነው። ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) የአኺራን መኖርንና የሞትን ቅርበት እንደ ሚከተለው ያስታውሱናል ፡-*«ከጫማችሁ ጠፍር በበለጠ ጀነት ለእያንዳንዳችሁ ቅርብ ነው። እንዲሁም (ገሀነም) እሳት።»(ኢማሙ አህመድ ኢቢን ሀንበል፣ጥራዝ 1፣ቁጥር 387፣ኢማም ኢብን ከሲር)*

ለዘላለም ስቃይ እራስህን መዳረግ ካልፈለክ በቀር ምንም ምኞት የሌለበትን (ጀሀነምን) ተጠንቀቅ! ለዓለማዊ ህይወትህ እራስህን አሳልፈህ በመስጠት እራስህን አታታል። በዓለም ላይ የመኖርህ ዋናው(ትክክለኛው) ምክንያት የተሳካ ህይወት እንዲኖርህ ወይም ባለፀጋ እንድትሆን ወይም ደስተኛ ቤተሰብ እንዲኖርህ አሊያም ልጆች እንዲኖሩህ አይደለም። ለአንተ መኖር ማናቸውም ትክክለኛ ምክንያቶች አይደሉም። የአንተ ዋንኛው ዓላማ አላህን(ሱ.ወ) መገዛት (መታዘዝ) እንዲሁም የሱን ፈቃድ ማግኘት፣ምህረቱን ማግኘትና ወደ ጀነት መግባት ነው።

---

[9] سورة: الأنبياء

በተፈጥሮ ሰዎች በዓለም ላይ በሚኖሩበት ጊዜ በንግድ ስኬታማ ሊሆኑ ይችላሉ:: ወደ ከፍተኛ ሥልጣን ደረጃ ሊያድጉ ይችላሉ፤ አግብተው ልጆችና የልጅ ልጆች ሊያፈሩ ወይም እነዚህን ነገሮች ለማሳካት ጥረት ሊያደርጉ ይችላሉ:: ነገር ግን በዓለም ላይ የመኖራቸውን ብቸኛ ዓላማ እስካልተገበሩ ድረስ እንዲሁም በተመሳሳይ ጊዜ የአላህን(ሱ.ወ) ፈቃድ እስካልፈለጉ ድረስ (ይህ ሁሉ ከንቱ ይሆንባቸዋል):: በተቃራሪው የሚያደርግ ሰው በመሞቻው ጊዜ ሁሉም ነገር ትርጉም ያጣበታል:: በዚህም ጊዜ አላህን(ሱ.ወ) ማምለክ ብቻ ትክክለኛው ነገር እንደሆነ ይረዳል:: አላህ(ሱ.ወ) ከቁርአን ጥቅስ ጋር ያዛምዳል:-

﴿٣٦﴾ وَمَا أَمْوَٰلُكُمْ وَلَآ أَوْلَٰدُكُم بِٱلَّتِى تُقَرِّبُكُمْ عِندَنَا زُلْفَىٰٓ إِلَّا مَنْ ءَامَنَ وَعَمِلَ صَٰلِحًا فَأُو۟لَٰٓئِكَ لَهُمْ جَزَآءُ ٱلضِّعْفِ بِمَا عَمِلُوا۟ وَهُمْ فِى ٱلْغُرُفَٰتِ ءَامِنُونَ[10] ﴿٣٧﴾

*«ገንዘቦቻችሁንም ሆኑ ልጆቻችሁ ወደ እኛ አያቃርቧችሁም::(ከእኛ ዘንድ የክብር ባለቤቶች) እነዚያ ያመኑትና መልካም የሠሩት ብቻ ናቸው::ለእነሱ፣በመልካም ሥራዎቻቸው ሳቢያ፣ድርብ ድርብርብ ምንዳዎች ተዘጋጅተዋል::በጀነት ሰገነቶች ውስጥም በሰላም(ይኖራሉ)::»(ሱረቱል-ሰበእ:37)*

በሌላ ጥቅስ አላህ(ሱ.ወ) እራሳቸውን በዚህ ዓለም ኑሮ ውስጥ በንብረት እና በሰድሎች ራሳቸውን ስለሚደልሉ እና የተፈጠሩበትን ዓላማ ስለሚረሱና በዚህ የተነሳ ለትልቅ ስቃይ ስለሚጋለጡ ሰዎች ሁኔታ ተናግሯል:-

﴿٢٦﴾ يَٰلَيْتَهَا كَانَتِ ٱلْقَاضِيَةَ ﴿٢٧﴾ مَآ أَغْنَىٰ عَنِّى مَالِيَهْ ﴿٢٨﴾ هَلَكَ عَنِّى سُلْطَٰنِيَهْ ﴿٢٩﴾ خُذُوهُ فَغُلُّوهُ ﴿٣٠﴾ ثُمَّ ٱلْجَحِيمَ صَلُّوهُ[11] ﴿٣١﴾

*«ምነው እርሷ(ሞት የህይወቴ) ፍፃሜ በሆነች (ከሞት በኋላ ዳግም ባልተቀሰቀስኩ):: ገንዘቤም (ቅንጣት) አልፈየደኝም:: ስልጣኔ ከእኔ ጠፋ (ከጥፋት አላዳነኝም):: ያዙት፣ ቀፍድዱትም ገሃነም ውስጥ ማግዱትም::»(ሱረ አል-ሓቃህ:27-31)*

---

[10] سورة سبأ
[11] سورة : الحاقة

## ራስዎን ሳይሸውዱ ከልብ ደመኑ!

ባለፉት ምዕራፎች በአካባቢያችን በምድር ላይ እና በህዋ ውስጥ የሚገኙትን ህይወት ያላቸውንና የሌላቸው ነገሮችን ሁሉን መመልከት ሞክረናል:: በዚህም የተነሳ የአንድ ሰው መፈጠር አላህን(ሱ.ወ) ለመገዛት (ለማመስከ) ወደ ሚለው እውነታ ደርሰናል:: ይህንን ምዕራፍ በጣም ወሳኝ የሆነውን ጉዳይ በማንሳት እንጀምር::

አሁን እድሜዎ ስንት ነው? 30 አመትህ ነው እንበል ተጥሎም 30 ዓመት ከአስር (10) ወራት ወደ ኋላ እንመለስ ብንል ይህም ማለት በምድር ላይ እስከ አሁን አልተፈጠርክም ::እንዲሁም ለወደፊትም እንደሚፈጠሩ ምንም አይነት ምልክት የለም::በኋላ የወንድ የዘር ፈሳሽ እና የሴት እንቁላል ተዋህደው ተፀነሱ፤ በመቀጠልም የዘጠኝ(9) ወር ጊዜያዊ የማህፀን ቆይተው እድገትዎን ጨርሰው ወደ ዓለማችን ህፃን ሆነው መጡ:: ይህም ማለት ወደ ህይወት የመጡት ከምንም ነበር:: በመጀመሪያ አንድ ሴል (ህዋስ) ነበሩ:: በመቀጠልም ይህ ህዋስ ተከፋፍሎ ሁለት፤ አራት፤ስምንት፤አስራ ስድስት፤ ሰላሳ ሁለት፤ሆነ......በመጨረሻም ህይወት ያለው ሰው ከብዙ ሴሎች የተሠራ፤ እጆች፤እግሮች፤ አይኖች፤ጆሮዎች ፤አፍንጫ ፤የደም ዝውውር፤ የመተንፈሻ ስርዓት እና ሌሎችም ያሉት ሆነ::ነገር ግን በሆነ ጊዜ አንድ ህዋሳት የነበረው ሰው ከነመረጃው እውቀቱ እና የመደሰት ብቃት ወዳለው ተለወጠ::ስለእሱ ሲያስቡ እንዴት በጣም ልዩ የሆነ ሂደት እንደሆነ በቀላሉ ይረዳሉ::እንዴት ቀጥሎ ይህ ታዓምር ተፈጠረ? እንዴት ጉብዝ የሆነ ፍጡር በሁለት ለዓይን ከማይታዩ ክፍሎች ውህደት ተፈጠረ? እና እንዴት ይህ ፍጡር ሁሉም ክፍሎች ያሉት ፍጥረት ሆኖ ወደዚህ ዓለም ሊመጣ ቻለ? ለዚህ ምላሽ በሚከተለው ጥቅስ ተሰጥቷል፡-

﴿هُوَ ٱلَّذِى خَلَقَكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍ ثُمَّ مِنْ عَلَقَةٍ ثُمَّ يُخْرِجُكُمْ طِفْلًا ثُمَّ لِتَبْلُغُوٓا۟
أَشُدَّكُمْ ثُمَّ لِتَكُونُوا۟ شُيُوخًا ۚ وَمِنكُم مَّن يُتَوَفَّىٰ مِن قَبْلُ ۖ وَلِتَبْلُغُوٓا۟ أَجَلًا مُّسَمًّى وَلَعَلَّكُمْ
تَعْقِلُونَ﴾[12]

*«እርሱ ያ ከአፈር፣ ከዚያም ከፍትወት ጠብታ ከዚያም ከረጋ ደም የፈጠራችሁ (አምላክ) ነው::ከዚያም ህፃን አድርጎ(ወደ ዚች ዓለም) ያወጣችኋል::ከዚያም ጥንካሬያችሁን ትደርሱ፣ለሽምግልናም ትበቃም ዘንድ(ዕድሜ) ይሰጣችኋል:: ከመካከላችሁ (ወደዚች ዓለም ከመምጣቱም) በፊት የሚሞት አለ::እስከ ተወሰነ ጊዜ ትቆዩ፣(የአምላካችሁን ጥበብና ችሎታም) ትገነዘቡ ዘንድ(ይህንን አደረገ)::» (ሱረቱል ጋፊር 40:67-68)*

በእነዚህ ጥቅሶች እኛንም ጭምር የሁሉም ሰዎች ፈጣሪ እና ሁሉንም ህይወት ያላቸው ነገሮች የፈጠረው አላህ(ሱ.ወ) እንደሆነ እናም ከዚህ እውነት ጋር ሲገጣጠሙ ሰዎች እውቀታቸውን ሊጠቀሙ ይገባል::እውቀቱን የሚጠቀም ሰው የተፈጠረበትን ትክክለኛ ዓላማ(ምክንያት) ያገኛል:: እንዲሁም እራሱን ለአላህ(ሱ.ወ) እምነት ያስገዛል::ህይወቱን ሙሉ የሱን ውዴታና ምህረት ለማግኘት ይሰጣል:: ሰዎች የተፈጠሩበትን አኳኋን ዘንግተው በጌታቸው ላይ እንዳያምጹ አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ እንደሚከተለው አፈጣጠራቸውን እንዲመራመሩ ይጋብዛል:-

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلْإِنسَٰنُ مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ ٱلْكَرِيمِ ۝ ٱلَّذِى خَلَقَكَ فَسَوَّىٰكَ فَعَدَلَكَ ۝ فِىٓ أَىِّ
صُورَةٍ مَّا شَآءَ رَكَّبَكَ ۝ كَلَّا بَلْ تُكَذِّبُونَ بِٱلدِّينِ ۝ وَإِنَّ عَلَيْكُمْ لَحَٰفِظِينَ ۝ كِرَامًا
كَٰتِبِينَ ۝ يَعْلَمُونَ مَا تَفْعَلُونَ﴾[13]

*«የሰው ልጅ ሆይ! ፍፁም ቸር በሆነው ጌታህ (ላይ እንድታምጽ) ያነሳሳህ ምንድን ነው? በፈጠረህ፣አካለ ሙሉ ባደረገህና ባስተካከለህም በመረጠው ቅርጽና ውበት በፈጠረህም (ጌታህ ላይ እንድታምጽ ያነሳሳህ ምንድን ነው?) (የሰው ልጅ ሆይ! ከአመጽ ታቀብ! የመጭውን ዓለም መኖር ታስተባብላላችሁ:: በእናንተ ላይ*

---

[12] سورة : غافر
[13] سورة : الانفطار

*ተቆጣጣሪዎች) (ተሹመውባችኋል)::(በእሳህ ዘንድ) የተላኩና ጸሐፊዎችም (የሆኑ ተቆጣጣሪዎች):: የምትፈጽሙትን(እያንዳንዱን ተግባር) ያውቃሉ::»(አል-ኢንፈጣር :82:6-12)*

ነገር ግን እነዚህ ሁሉ እውነታዎች ቢኖሩም ሰው ራሱን በማታለል ከእውነተኛው መንገድ በመውጣት እንዲሁም ጥረቶቹን በማይረቡ ነገሮች ላይ በማጥፋት ራሱን ለአደጋ አጋልጧል::ምንም እንኳን የዓለማችን እያንዳንዱ ነገር እጹብ ድንቅ ተዓምር ቢሆንም፣ይህንን ለማየት እና ለመስማት ሲያዳግተው ይስተዋላል:: አሊያም የአእምሮውን ደወል ባለመስማት፣ ስለሚያየው እና ስለሚሰማው ነገር ስሜቱ ድንዙዝ ይሆናል:: አንድ ሰው ስለ አላህ(ሱ.ወ) መኖርና ታላቅነት ካላሰበ፣ በገሃዳዊ ዓለም ባየው ነጸብራቅ መልስ ባለመስጠቱና ቸልተኛ በመሆኑ ለዘላለማዊ ፀፀት ይዳረጋል::ስለዚህም ሰዎች እራሳቸውን ማታለል ማቆም ያስፈልጋቸዋል::እንዲሁም ማንኛውም ፍጥረት በዓለማችን ላይ የተፈጠረው ለምክንያት እንደሆነ መገንዘብ አለባቸው::እንዲሁም በአእምሮአቸው ውስጥ ያላቸው ጥሩ ነገሮች ሁሉ እንደ በረከት የተሰጣቸው ነው::በሠሩት ስራ ሁሉ በፍርዱ ቀን ለተጠያቂነት ይቀርባሉ::

## <u>የቂን ይኑርዎት !</u>

እውነተኛ እምነት ያላቸው ሰዎች እራሳቸውን አያታልሉም::በማንኛውም ጉዳይ ላይ እውነቱን አይክዱም:: ምክንያቱም ለኃያሉ አላህ(ሱ.ወ) ውዴታና ፍርሃት አላቸው::በተጨማሪም የሱን ፈቃድ ያለማግኘት አደጋንና ትእዛዛቱን ከመናቅ በእጅጉ የጸዱ ናቸው::ነገር ግን በቁርአን ውስጥ «በልባቸው ውስጥ ህመም ያለባቸው» ተብለው የተጠቀሱት ሰዎች አላህን(ሱ.ወ) በማምለክ ላይ ስልቹ ናቸው::በሱረቱ አል-ኒሳዕ 72 ላይ አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ በማለት ይጠቅሳቸዋል:- *«ከእናንተ ውስጥ ወደ ኋላ የሚቀር አለ::»(4:72)*

እነዚህ ሰዎች ከቁርአን ጋር የሚሄደውን የአኗኗር ዘይቤ ኢስላማዊ መርህ ያውቃሉ። ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ላይ የቂን ስለሌቸው ቸልተኝነትን ያበዙ ሰዎች ሁልጊዜ አላህን(ሱ.ወ) ላለማመናቸው ምክንያት ያቀርባሉ። ምክንያቱም በዚህ ዘላቂ በሆነ የምክንያት ፍሰጋ የተሰማሩ ናቸው።እራሳቸውን የሚያታልሉ ሰዎች በውሸት ራሳቸውን ሲሸነግሉ ኖረው ለፍርድ ይቀርባሉ። ወይም ማንኛውም ሁኔታ ወይም ጉዳይ ቢሆንም ከእውነቱ ይቀሰበሳሉ። በሌላ ጥቅስ አላህ(ሱ.ወ) ሲያወሳ እነርሱ «አላህን የሚያመልኩት በድርብቡ ነው» እናም እንደሚፈለግባቸው እራሳቸውን ለአላህ(ሱ.ወ) በየቂን አይሰጡም። በእውነቱ እነርሱ የቂን በሌለው(ከምር ባል ሆነ) ኢባዳቸው ጠቅለል ባለ መልኩ የሚያታልሉት በእርግጥ እራሳቸውን ብቻ ነው። አላህ(ሱ.ወ) ይህንን በቁርአን ውስጥ ገልጾታል፦

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَقُولُ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَبِٱلْيَوْمِ ٱلْآخِرِ وَمَا هُم بِمُؤْمِنِينَ ۝ يُخَٰدِعُونَ ٱللَّهَ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَمَا يَخْدَعُونَ إِلَّآ أَنفُسَهُمْ وَمَا يَشْعُرُونَ ۝ فِى قُلُوبِهِم مَّرَضٌ فَزَادَهُمُ ٱللَّهُ مَرَضًا ۖ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌۢ بِمَا كَانُوا۟ يَكْذِبُونَ ۝ ﴾[14]

*«ከሰዎች መካከል፦ «በአላህና በመጨረሻው ቀን (መኖር) አምነናል» የሚሉ (ወገኖች) አሉ ፈጽሞ አማኞች አይደሉም።አላህና እነዚያ ያመኑትን ሲያታልሉ (ይሞክራሉ)። እራሳቸውን እንጂ ሌላ ማንንም አያታልሉም።ግና (ይህን) አይገነዘቡም ልባቸው ውስጥ በሽታ አለ። አላህ በሽታን ጨመረላቸው። ይዋሹት በነበረው ሰበብ አሳማሚ ቅጣት ይጠብቃቸዋል።» (አል-በቀራህ 2:8-10)*

ሃቀኝነት ለአላህ(ሱ.ወ) ሃይማኖት ወሳኙ ነገር ነው። አንድ ሰው የሆነ አይነት አምልኮ በልምድ የተነሳ በቸልተኝነት ወይም በዙሪያው ያሉ ሰዎችን ወቀሳ ለማምለጥ ብሎ የሆነ የአምልኮ ስርአት ሊኖራቸው ይችላል።አሁንም እርሱ እራሱን ብቻ ነው የሚያታልለው። እላይ ባሉት ጥቅሶች እንደተብራራው በአላህ(ሱ.ወ) እይታ ግለሰቡ የሚያደርገው ሁሉ ምንም ዋጋ ይኖረዋል ብሎ

---

[14] سورة : البقرة

መጠበቅ አይችልም።በቁርአን ውስጥ አላህ(ሱ.ወ) በቸልተኝነት የሚካሄዱ የአምልኮ ሥራዎች ተቀባይነት እንደሌላቸው ያስጠነቅቃል፦

وَمَا مَنَعَهُمْ أَن تُقْبَلَ مِنْهُمْ نَفَقَٰتُهُمْ إِلَّآ أَنَّهُمْ كَفَرُوا۟ بِٱللَّهِ وَبِرَسُولِهِۦ وَلَا يَأْتُونَ ٱلصَّلَوٰةَ إِلَّا وَهُمْ كُسَالَىٰ وَلَا يُنفِقُونَ إِلَّا وَهُمْ كَٰرِهُونَ [15] ﴿٥٤﴾

***«የሰጡት (ጋብት) ተቀባይነት እንዳይኖረው እንቅፋት የሆነው በአላህና በመልክተኛው በመካዳቸው፣ሶላትን እየተሰላቹ እንጂ የማይሰግዱ፣እየጠሉ እንጂ የማይሰጡ በመሆናቸው ነው።»(ሱረቱ ተውባ 9:54)***

ሐቀኛ ያልሆኑ ሰዎች አላህ(ሱ.ወ) ግዴታ ያደረገባቸውን ባለመወጣታቸው ማስቲያና ማብቂያ የሌላቸው ምክንያቶችን ይደረድራሉ። እንዲሁም በዓለማዊ ፍላጎቶች ላይ ሕይወታቸውን ያባክናሉ። በህፃንነታቸው፣በት/ቤት ጊዜያቸው ፣ወደ ሥራ ሕይወት ሲገቡ፣እራሳቸውን ሲያገኑ ፣ሲደስቱ፣ ዓመታትን ሁሉ ሲባዝኑ ወዘተ …በማናቸውም ሁኔታዎች አላህን(ሱ.ወ) ባለማመናቸው እና ትእዛዙን ባለመከተላቸው ከተፈበረኩ ምክንያቶች ጋር ይመጣሉ። በሚቀጥሉት ምዕራፎች ሰዎች በቀን ተቀን ኑሮአቸው የሚያቀርቡዋቸውን ምክንያቶች እናነባለን።አስፈላጊ የሆነው ነገር ሰዎች እነዚህን ምክንያቶችን ሲያቀርቡ ሀቀኛ እንዳልሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ምክንያቱም ሰዎች በህይወት እያሉ የአላህን(ሱ.ወ) ትእዛዝ እንዳያከብሩ የሚያደርጋቸው ምንም አይነት ምክንያት የለም። አንድ ሰው እንደ እዚህ አይነት ምክንያት ሲያመጣ ይህ የሚያሳየው የሱን ሐቀኛ አለመሆን ወይም የእምነት ማነስን ነው።በእያንዳንዱ ደቂቃ አላህ(ሱ.ወ) አብሮት እንዳለ የሚያውቅ ሰው፣ሁሉንም ነገር እንደሚያይ ፣እንደሚሰማ፣እንዲሁም ሰዎች ሚስጥር ናቸው ብለው የሚይዟቸውን እንደ ሚያጋልጥ የሚያውቅ እሱን በመገዛት(በማምለክ) ረገድ ምንም አይነት ኢ-ተአማኒነት ለማሳየት አይሞክርም። እንደዚህ ያለ ሰው ምክንያት ቢያቀርብ ገና ወደ ከንፈሮቹ ቃላቶቹ ከመውጣታቸው በፊት አላህ(ሱ.ወ) እንደሚያውቀው በደንብ ያውቃል። እንዲሁም አላህ(ሱ.ወ) በጥርጣሬ የሚያመልከው ሰው ውስጥ ያለውን ቸልተኝነትም በደንብ ያውቃል።እንደዚህ ያለ ያልታመነ ፀባይ ይቅር እንደማይባልም ይረዳል።ስለዚህ እራስን ማታለል

---

[15] سورة : التوبة

ማምለጫ እንዳልሆነ እና የበለጠ ትልቅ ጉዳት እንደሚያመጣበት ያውቃል። እንደዚህ ያለ ሰው በማናቸውም ሁኔታ የአላህን(ሱ.ወ) ውዴታ(ሰዝነት) ከመጠየቅ አይቦዝንም። ምክንያቱም ለጠንካራ እምነቱ ምስጋና ይግባውና ምንም አይነት ድክመት የለበትም።በሁሉም ጊዜያት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ታማኝ ነው።

በልባቸው ውስጥ ህመም ያለባቸው ሰዎች ምንም እንኳን አላህን(ሱ.ወ) በግልፅ ባይወቅሱም ሁልጊዜም በእምነታቸው ደካማ ናቸው።ይህም ማለት እምነታቸው በሆነ ሁኔታ ላይ የተመረከዘ ነው።ከእምነታቸው ለማፈንገጥ ምንም አይጠራጠሩም።እምነታቸው ከጥቅማቸው ወይም ምኞታቸው ጋር በሚጋጭበት ጊዜ ማንኛውንም ወደ እእምሯቸው የመጣ አምልኮን በማምለክ (ዱዓን በመለመን) የህሊና ተጠያቂነታቸውን ለማቅለል ይሞክራሉ። እነዚህ ሰዎች በጣም በግልፅ ራሳቸውን ያታልላሉ። ነገር ግን ይህንን መቼም ሊያውቁት አይችሉም። በአላህ(ሱ.ወ) እይታ እነዚህ ሰዎች ላይ የሚስተዋለው የኢ-ታማኚነት ሁኔታ ውስጥ ላለመውደቅ ከፈለክ እራስህን እንዳታታልል ተጠንቀቅ። እውቀትህ በቂ ካልሆነ የአላህን(ሱ.ወ) ቁርአን በመቅራት ልታውቀው ትችላለህ። ምክንያቱም በቁርአን ውስጥ ጌታችን ራሱን ለባሪያዎቹ አሳውቋል። በዚህ መንገድ አላህን(ሱ.ወ) በረከት ልትረዳ ትችላለህ። እንዲሁም ሙሉ ለሙሉ ቅን አማኝ መሆን ያስችልሃል።ነገር ግን አላህን(ሱ.ወ) እና ዲኑን(ሃይማኖቱን) በድንቁርና(ጃሂሊያ) አመለካከት ከገመገምከው መመለሻ ወደ ሌለው ስህተት ውስጥ ትወድቃለህ።አላህን(ሱ.ወ) በጠንካራ እና በቅን እምነት ካተገዛኸው(ካመለከው) ብቻ ጀነትን እንደምታገኝ እንዳትረሳ። ይህ እውነት በነቢያችን(ሰ.ዐ.ወ) በተጨማሪ ተገልጿል። ስለዚህ፡- *«ማንንም ሰው ከአላህ ጋር ማንንም ሳያጋራ(ሳያሻርክ) ከአላህ ጋር የተገናኘ ጀነት ይገባል።» (በሂህ ሙስሊም)*

## በአኺራ ከልብዎ ይመኑ!

ባለፉት ምዕራፎች እንዳነሳነው፣ የራሱን ፍላጐቶች እና ምኞቶች የሚያሳድድ፣ የማይረባ ሥራ የሚሰራ እና የአላህን(ሱ.ወ) መመሪያ እና ክልከላ ማስታወስ የማይፈልግ ሰው ከሞት በኋላ ደግሞ እንደሚነሳ በሠራው እንደሚጠየቅና የሚገባውን እንደሚከፈለው ሊያስብ አይፈልግም። በዚህ ምክንያት ምንም እንኳ ህሊናው ከሞት በኋላ ህይወት እንዳለ ቢያሳውቀውም ህሊናውን መጨፈኑና እራሱን ማታለልን ይመርጣል። ለዚህም ነው ለምሳሌ «ዳግም-ውልደት» የሚባለው አስተሳሰብ ሰዎች የተቀበሉትና በተለይም በቅርብ ጊዜ እየተስፋፋ የመጣው። ይህ ማለት ደግሞ ለብዙ ጊዜ በተለያየ ቦታና ጊዜ የሞቱ ሰዎች ዳግም በተለያየ ማንነት እንደሚፈጠሩ የሚሰብክ ነው። ይሄ የሚሆንበት ምክንያትም በህይወት ለሠራናቸው ሥራዎች በጀሃነም ቅጣት ይጠብቀናል ወይም ሌላው ቢቀር ሊጠብቀን ይችላል ብለው የሚያስቡ ሰዎች ከሞት በኋላ ህይወት እንዳለ መቀበሉ አይዋጥላቸውም። በመሆኑም እነዚህን የተሳሳቱ እምነቶችንና ሃሳቦችን ምንም እንኳ ሙሉ ለሙሉ ከእውነት የወጡ ቢሆንም በጥቂት ማስረጃ እንኳ እንዲረጋገጥላቸው ሳይጠይቁ ሰዎች በደስታ ይቀበሏቸዋል።

እራሳቸውን ሊሸውዱና ከሞት በኋላ ህይወት መኖሩን የማይቀበሉ ሰዎች በማንኛውም ታሪካዊ ጊዜ ውስጥ ነበሩ። በእውነቱ ቁርአን ላይ አላህ(ሱ.ወ) እነዚህ ሰዎች ከማሰብና ምክንያታዊነት የሚያፈነግጡበትን መንገድ ያስጠነቅቃል። ይሄን የሚያደርጉትም ከሞት በኋላ ህይወት መኖሩን ላለመቀበልና እውነቱን ላለመጋፈጥ ሲሉ ነው። እነዚህ ጥቂት አስፈላጊ ጥቅሶች ናቸው፡-

وَضَرَبَ لَنَا مَثَلًا وَنَسِيَ خَلْقَهُۥ ۖ قَالَ مَن يُحْيِ ٱلْعِظَٰمَ وَهِيَ رَمِيمٌ ﴿٧٨﴾ قُلْ يُحْيِيهَا
ٱلَّذِىٓ أَنشَأَهَآ أَوَّلَ مَرَّةٍ ۖ وَهُوَ بِكُلِّ خَلْقٍ عَلِيمٌ[16] ﴿٧٩﴾

---

[16] سورة يس

*«ለኛ ምሳሌ አደረገልን፡፡ሕፈጣጠሩንም ዘነጋ፡፡» የበሰበሱ አጥንቶችን ሕያው የሚያደርግ ማን ነው?» አለ፡፡በል፡- «ያ መጀመሪያ ከምንም ያስገኛቸው(አምላክ) ሕያው ያደርጋቸዋል፡፡ እርሱ ፍጡራንን ሁሉ ጠንቅቆ አዋቂ ነው፡፡»(ሱረቱ ናዚዓት 79:10-12)*

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ከሞት በኃላ ትንሳኤና ሕይወት የለም ብለው የማያስተባብሉ ሰዎች በርግጥ ከሞት በኃላ መነሳት እንዳለ ያምናሉ (ሲቀሰቀሱ ለነርሱ ጥቅም እንዳልሆነ) ነገር ግን የተቻላቸውን ያህል የረቀቁ ጥበቦችና ሉጂኮችን በማምጣት ወደ አዕምሯቸው ሰርጾ እንዳይገባ ይከላከላሉ፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች ውስጥ እንደምንመለከተው ትንሳኤን የማይቀበሉና የሚያውቁትም ትንሳኤ ለእነሱ ጥቅም አለመሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህ ሰዎች ይሄ ሃቅ ወደ አእምሯአቸው እንዳይዘልቅ ያግዱታል፡፡ከተጨማሪም የተወሳሰበ የንግግርና አመክንዮ በመጠቀም ሌሎችም የእነሱን መንገድ እንዲከተሉ እውነቱን በመሸፈን ያበረታታሉ፡፡ ቁርአን የሚከተለውን ምሳሌ ይሰጣል፡-

أَءِذَا كُنَّا عِظَٰمًا نَّخِرَةً ﴿١١﴾ قَالُوا۟ تِلْكَ إِذًا كَرَّةٌ خَاسِرَةٌ ﴿١٢﴾ فَإِنَّمَا هِىَ زَجْرَةٌ وَٰحِدَةٌ[17] ﴿١٣﴾

*«(በዚህች ዓለም ውስጥ የትንሣኤን እምነት ባለመቀበል) እንዲህ ይላሉ፡- «ወደ ድሮው እኛነታችን እንመለሳለን?»ይላሉም፡- «ይህች በኪሣራ የተሞላች መመለስ ናት፡፡) ከሞት በኃላ ዳግም የመቀስቀስ ነገር እውነት ከሆነ የሚገጥመን ኪሣራ እጅግ ለስከፊ ነው)፡፡»(ሱረቱ ያሲን 36:78-79)*

ከሞት በኋላ ስላለው ስማያዊ ህይወት እራሳቸውን የሚሸውዱበት መንገድ የሚመርጡት ሰዎች ይህንን ምክንያት በአጠቃላይ አስተሳሰባቸውና ባህሪያቸው ላይ ያንፀባርቃሉ፡፡ ከሞት በኋላ ፍርድ መኖሩንና ወይ በጀነት ወይም ደግሞ በገሃነም ዘላለማዊ ህይወት መኖሩን የማይቀበሉ ሰዎች ለስጋዊ ፍላጐታቸው ለከት አይኖራቸውም፡፡ ሰዎች የሥጋ ነገራቸውን የሚገቱት ከሞት በኃላ ፍርደ አለ ብለው በመፍራት ነው፡፡ይህንን «ፋራ[1]ሙጠዋ ወዘተ» በማለት ለአላህ(ሱ.ወ) የሚከፍሉትን መስዋዕትነት ማንኳሰስና መተው ይጀምራሉ፡፡ከሞት በኋላ ህይወት ያለ መሆኑን የሚያምኑ ብቻ እራስን

[17] سورة: النازعات

በማታለል እውነትን መተው ከፍያው ትልቅ ህመምና ስቃይ መሆኑን ያውቃሉ።

ትንሽ ስታስብ በአካባቢህ ያለው ነገር ሁሉ የአጋጣሚ ሥራ ወይም ውጤት አለመሆኑንና ይልቁንም በአላህ(ሱ.ወ) ውስጠ የንፋስ ኃይል[1] እውቀትና ቁጥጥር መሆኑን በቀላሉ ትመለከታለህ። በተጨማሪም ከላይ በጥቅሶቹ ውስጥ እንደተባለው ከሞት በኋላ ህይወት እንዲኖር ማድረግ ለአላህ(ሱ.ወ) ቀላል ነገር ነው። እናም ከሞት በኋላ ህይወት መኖሩ ለመለኮታዊ ፍትህ ተስማሚ መሆኑ ምንም እንዳች ጥርጥር የለውም። በማንኛውም ሁኔታ እነዚህን እውነታዎች ላለመተውና እራስህን ላለማሳሳት ተጠንቀቅ። ምክንያቱም እንደዚህ የሚሳሳቱት ሰዎችና ከሞት በኋላ ህይወት ያለመሆኑን የማይቀበሉት ከስህተታቸው አይማሩም፤ ለዘላለምም በስቃይ ውስጥ ይሆናሉ።

## ሠይጣንን አይታዘዙ!

አብዛኛዎቹ ሰዎች የሠይጣንን እውነተኛ ገፅታ አያውቁም። እናም ከሌሎች የሚሰሙትንና በፊልም በሚያዩት ላይ በመመርኮዝ እንደ ሃሳባዊ ፍጥረት ይመለከቱታል።ስለሆነም አንዳንዶች ሰይጣን ከአላህ(ሱ.ወ) በርግጠኛነት ያነሰና የራሱ ነፃ ኃይል እንዳለው ሲያምኑና አግዝፈው ሲያካብዱት ሌሎች ደግሞ ሰይጣን መኖሩን በጥርጣሬ አይን ይመለከታሉ። ለመቀበልም አይችሉም። ሰይጣን እንዳለ ቢያምኑ እንኳ በነሱ ላይ ምንም የሚያመጣው ነገር እንደሌለ አይቀበሉም። ማናቸውም እነዚህ አቋሞች በምንም አይነት መረጃ ወይም ማስረጃ የተደገፉ ሳይሆኑ ከጭፍን እምልኮ የሚመጡ ናቸው። በሌሎች እንደሚሆነው ሁሉ በዚህ ነገር ላይም የመጨረሻውን ትክክለኛና አስተማማኝ መረጃ ከእውነተኛ የአላህ(ሱ.ወ) ቁርአን ልናገኝ እንችላለን። ነብያችን(ሰ.ዐ.ወ) እንደሚሉት፦*«ከሁሉም ቃሎች የአላህ(ሱ.ወ) ቃል ይበልጣል። ከሀሉም መንገድ ደግሞ የሙሐመድ መንገድ ይበልጣል»። (ሱነን ኢብን ማጃህ፣ ሙቀዲማ፣)*

ቁርአን ላይ እንደተነገረን በመጀመሪያና ከምንም በለይ ሰይጣን የራሱ የሆነ ነፃ ኃይል የለውም። በአላህ(ሱ.ወ) የተፈጠረና ሙሉ ቁጥጥር ሥር ያለ ፍጡር ነው።በዓለም ላይ የሚታየው ሁሉ የሚከሰተው በአላህ(ሱ.ወ) ፈቃድ ነው።

ሰይጣን ከአላህ(ሱ.ወ) ቅጥር ከተባረረ በኋላ የዓለም ፍፃሜ እስኪመጣ ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቆታል:: ከአላህ(ሱ.ወ) ዘንድ እንደተባረረና የጠየቀውም ጊዜ እንዴት እንደተሰጠው እንደሚከተለው ተነግሮናል፡-

وَلَقَدْ خَلَقْنَٰكُمْ ثُمَّ صَوَّرْنَٰكُمْ ثُمَّ قُلْنَا لِلْمَلَٰٓئِكَةِ ٱسْجُدُوا۟ لِءَادَمَ فَسَجَدُوٓا۟ إِلَّآ إِبْلِيسَ
لَمْ يَكُن مِّنَ ٱلسَّٰجِدِينَ ﴿١١﴾ قَالَ مَا مَنَعَكَ أَلَّا تَسْجُدَ إِذْ أَمَرْتُكَ ۖ قَالَ أَنَا۠ خَيْرٌ مِّنْهُ
خَلَقْتَنِى مِن نَّارٍ وَخَلَقْتَهُۥ مِن طِينٍ ﴿١٢﴾ قَالَ فَٱهْبِطْ مِنْهَا فَمَا يَكُونُ لَكَ أَن تَتَكَبَّرَ فِيهَا
فَٱخْرُجْ إِنَّكَ مِنَ ٱلصَّٰغِرِينَ ﴿١٣﴾ قَالَ أَنظِرْنِىٓ إِلَىٰ يَوْمِ يُبْعَثُونَ ﴿١٤﴾ قَالَ إِنَّكَ مِنَ ٱلْمُنظَرِينَ
﴿١٥﴾ قَالَ فَبِمَآ أَغْوَيْتَنِى لَأَقْعُدَنَّ لَهُمْ صِرَٰطَكَ ٱلْمُسْتَقِيمَ ﴿١٦﴾ ثُمَّ لَءَاتِيَنَّهُم مِّنۢ بَيْنِ أَيْدِيهِمْ
وَمِنْ خَلْفِهِمْ وَعَنْ أَيْمَٰنِهِمْ وَعَن شَمَآئِلِهِمْ ۖ وَلَا تَجِدُ أَكْثَرَهُمْ شَٰكِرِينَ ﴿١٧﴾ [18]

*«ፈጠርናችሁ::(እጅግ የተዋባችሁ አደረግን) ቀረጽናችሁም በዚያም መላእክትን፡- «ለአደም ስገዱ::» በማለት አዘዝን:: ሰገዱ ዲያብሎስ ሲቀር::እርሱ ከሰጋጆች አልነበረም:: (አምላከም) :- ባዘዝኩህ ጊዜ እንዳትሰግድ የከለከለህ ምንድን ነው?» ሲል ጠየቀው::«እኔ ከርሱ የተሻልኩ ነኝ:: እኔን የፈጠርከኝ ከእሳት ሲሆን፣ እነርሱን ግን የፈጠርከው ከጭቃ ነው::» አላህ «ከርሷ(ከጀነት) ውረድ በውስጧ ሆነህ ልትኮራ አይገባህም::ውጣ አንተ ከወራዶች ነህና::» አለው::(ዲያብሎስም) እስከ ሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ አቆየኝ::»ሲል ጠየቀው::(አላህም)» አንተ (እስከ ተወሰነ ወቅት ድረስ) ከሚቆዩት ተደርገሃል::«መንገድ እንድትስት ስላደረግከኝ ከቀና ጎዳና መካከል እቀመጥባቸዋለሁ::»አለ «ከዚያም በፊት ለፊታቸውም፣ከበስተኋላቸውም ፣ከበስተቀኛ ቻቸውም፣ከበስተግራቻቸውም አመጣባቸዋለሁ::አብዛኛዎቹንም(ሰበጋዎችህ) ምስጋና አድራሾች ሆነው አታገኛቸውም::» (አላህም) አለው:: «የተዋረድህና የተባረርክ ሆነህ ከእርሷ ውጣ:: ከነርሱ መኃል የተከተለህን ገሃነምን በእርግጥም በናንተ እሞላለሁ::»(አል-አዕራፍ 7:11-18)*

ከአላህ(ሱ.ወ) ዘንድ ተባሮ በዘላለማዊ ሥቃይ እንዲኖር ከተፈረደበት በኋላ ሰይጣን ሰዎችን በሐሰተኛ መንገዶቹ ሊያሳስታቸው ምሎ ተገዝቷል:: የከፋት

[18]سورة : الأعراف

ሥራዎቹንም ጀምሯል።አላህ(ሱ.ወ) ፣የሰይጣን ተግባሮች እውነተኛ አማኞችን ከማይታዘዙት ለመለየት እንዲችል አድርጕታል።የሰይጣን አሳሳች ጨዋታዎች ፣ወጥመዶች እና እቅዶች በማንኛውም በህይወት ያለ ሰው ላይ ያነጣጥራሉ። እያንዳንዱ ህይወትን የሚያጣጥም ሁሉ በዚህ ይፈተናል። ሰይጣን ያለ ልዩነት ሁሉንም ሊያሳስት ይሞክራል። በመሆኑም ማንም እራሱን ከሰይጣን ተፅእኖ ውጭ እንደሆነ አድርጕ መመልከት የለበትም። አንድ ሰዉ ይህንን ካወቀ በጥንቃቄ ይኖራል።እናም ትንሿን የሰይጣንን ወጥመድ እንኳ መመርመር ይችላል።ሰይጣን እንዴት ሰዎችን እንደሚያታልል ሃሳባችንን ሰብሰብ አድርገን ብናስተነትን ሙዕሚኖችም እንዴት ከዚህ የሰይጣን ፈተና መውጣት እንዳለባቸው እናውቃለን።በዚህ የተነሳም ሰይጣን እውነተኛ የአላህ(ሱ.ወ) ባሪያዎችን ተፅእኖ ሊያደርግባቸው አይችልም።ምክንያቱም ሰይጣን ከእውነተኛ ው መንገድ እንዲወጡ ሊያደርጋቸው እንደሚችል አይረሱትም። ስለሆነም እራሳቸውን በጥንቃቄ ይጠብቃሉ።

ሠይጣንም፣ሰዎችን ከአላህ(ሱ.ወ) ጉዳና ለማውጣት ብዙ ብልሃቶችን ተጠቅሞ አላህ(ሱ.ወ) እርሱን ብቻ እንዲያመልኩ የሚያዘውንና በቃሉም በቁርአን ሊኖር የሚገባውን ኢስላማዊ ስርዓት እንዳናምን ያሰናክናል። ከእነዚህም ምክንያቶች አንዱ ሰዎች አላህን(ሱ.ወ) ለማምለክ እንደማይችሉ ብዙ ምክንያቶችን በማቅረብ ነው። በሌላ አባባል ሠይጣን ለሰው ልጅ የሚያደርገው ሁሉ ምክንያታዊ እንዲመስል ያደርጋል። ለምሳሌ አንድ አላህን(ሱ.ወ) ማምለክ ያለበትን ወጣት ገና ብዙ ጊዜ ስላለው ግዴታውን በአግባቡ እንዳይወጣ እንቅፋት ይሆንበታል። ምክንያቱም የሥራና የትምህርት ጊዜ ስላለው ያን ባያደርግ ደግሞ በሌለው የሕብረተሰብ ክፍል ውግዘትን ያስከትልብሃል በማለት በጆሮ ሊያንሾካሹክ ይችላል። ሰውየውም ጥብቅ እና ጠንካራ እምነት ከሌለው በነዚህ ሁኔታዎች በቀላሉ ሊታለል ይችላል። ይሁንና በሰይጣን ተፅዕና ቀንበር ሥር በቀላሉ ይወድቃል።ሠይጣንም ይህ ስለማይበቃው ሰውየውን በቀላሉ አይለቀውም። ከላይ እንዳየነው ሰውዬው ወይም ልጁ ወደ ጀሃነም እስከሚገባ ድረስ አይለቀውም።በዚህም ሰውዬው በሚያደርገው በሚሰጠው ምክንያት ያ የሚሠራው ሥራ በትክክለኛው መንገድ እንደሆነ በማሳመን (በመጉትጉት)

የአላህን(ሱ.ወ) ትእዛዝ አለመቀበሉና አላህን(ሱ.ወ) ማምለክ ስህተት እንደሆነ ለማሳየት ይጥራል፤ ይተጋል:: በእውነት ከላይ ለማየት እንደተሞከረው እያንዳንዱ ሰው በህሊናው ፈጣሪውን አላህን(ሱ.ወ) መገዛት እንዳለበት ያውቃል::ሠይጣንም በሚያመጣለት ትክክለኛ በሚመስሉ ምክንያቶች አላህን(ሱ.ወ) መገዛቱ አስፈላጊ እንዳልሆነ ያንሾከሽክለታል:: በሌላ አባባል ምንም እንኳን ምን ማድረግ እንዳለበት ህሊናው ቢያውቅም በተለያዩ ምክንያቶች እራሱን አያሳምንም:: ከትክክለኛው የሕይወት ግቡ ስንካላ የመሆን እድሉ ይሰፋል:: እነዚህ ሰዎች በሰይጣን ጉትጎታ ብዛት እንደሚታለሉ እና እምነታቸውንም እንደሚያጡ አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን ይናገራል::ከእነዚህም ውስጥ በነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን ሲኖሩ የነበሩና የኢማን ድክመትም የነበረባቸው ሰዎች እንዳሉ ምሳሌ ይሰጠናል:: ጦርነት(ጂሃድ) ለትክክለኛ ነገር ከሆነ ተገቢ ነበር::ነብያችንም(ሰ.ዐ.ወ) ሰዎች ለትክክለኛው ነገር እንዲያምኑ ነግረዋቸው ነበር:: ነገር ግን ሰዎች ራሳቸው ባመጡት ሰበብ ወደ ጦርነት ላለመሄድ ፈልገው ነበር:: አላህም(ሱ.ወ) እነዚህን ሰዎች «ልባቸው የታመመ ሰዎች» በማለት ይገልፃቸዋል::

የሠይጣን ብልጣብልጥ ክፋት የትም ቦታ ተንሰራፍቶ ያለ ነው:: በዚህም ክፋት የተነሳ የሰው ልጅ አውቆም ሆነ ሳያውቅ በእለት ተእለት ሕይወቱ የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች ማለፍ ተስኖት ስህተት ውስጥ ይወድቃል:: እናም በጎ አማኝ ካልሆነ ይህ የክፋት ተፅዕኖ ጠቅላላ የህይወቱን አቅጣጫ አስቶት በቀጥታ ወደ ጀሃነም እንዲገባ ሊያደርገው ይችላል:: ያም ትክክለኛው የሠይጣን ዓላማ ነው:: ሠይጣን የሰው ልጆች በአላህ(ሱ.ወ) ላይ አምጸው የዘላለም ስቃይ እንዲደርስባቸው ይፈልጋል:: ወደ እሳቱም እስከሚገቡ ድረስ የሰው ልጅን ማባረሩን አያቆምም:: ይህ ሁሉ ወጥመድ ሠይጣን የሰው ልጅ ተከታትሎና ጠብቆ በትንሹም ሆነ በትልቁ የጥፋት አጋጣሚ ውስጥ በመክተት ከራሱ ጋር ወደ ጀሃነም ለመክተት ነው:: በአንድ ጥቅስ ላይም አላህ(ሱ.ወ) የሰው ልጅ ወደዚህ ጥፋት እንዳይገባ ያስጠነቅቃል:-

إِنَّ ٱلشَّيْطَٰنَ لَكُمْ عَدُوٌّ فَٱتَّخِذُوهُ عَدُوًّا ۚ إِنَّمَا يَدْعُوا۟ حِزْبَهُۥ لِيَكُونُوا۟ مِنْ أَصْحَٰبِ ٱلسَّعِيرِ [19] ﴿٦﴾

*«ሰይጣን በእርግጥም ጠላታችሁ ነው:: ስለሆነም ጠላት አድርጋችሁ ያዙት:: ተከታዮቹን የሚጠራው ከእሳት ሰዎች እንደሆኑ ነው::» (ፋጢር 35:6)*

አላህ(ሱ.ወ) በሚከተለው ጥቅስ ስለ ታላቁ ጥፋት ያስረዳናል::ከሰው ልጅ ፍጥረት ማግስት እስከ አሁን ድረስ ሠይጣን ቁጥር ስፍር የሌላቸውን የማያምኑ ሰዎችን አሳስቷል:: የቁርአንም ይህንን እውነታ ያወሳል:-

وَلَقَدْ صَدَّقَ عَلَيْهِمْ إِبْلِيسُ ظَنَّهُۥ فَٱتَّبَعُوهُ إِلَّا فَرِيقًا مِّنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿٢٠﴾ وَمَا كَانَ لَهُۥ
عَلَيْهِم مِّن سُلْطَٰنٍ إِلَّا لِنَعْلَمَ مَن يُؤْمِنُ بِٱلْءَاخِرَةِ مِمَّنْ هُوَ مِنْهَا فِى شَكٍّ ۗ وَرَبُّكَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ
حَفِيظٌ [20] ﴿٢١﴾

*«ሰይጣንም ምኞቱን አረጋገጠባቸው:: እነርሱም ተከተሉት፣ ጥቂት ሰማኞች ሲቀሩ:: እርሱ በእነሱ ላይ ምንም ዓይነት ሥልጣን አልነበረውም:: ግና በመጪው ዓለም የሚያምነውን፣ከሚጠራጠረው ለዩለት ለንፅ (እንዲጉተጉታቸው አደረግን)::ጌታህ ሁሉንም ነገር የተቆጣጠረ ነው::»(ሰበእ 34:20-21)*

ካሳለፍነው ጥቅስ ማየት እንደቻልነው ሠይጣን የሰውን ልጅ የማስገደድ ኃይል እንደሌለው አይተናል:: በተለይ ለሰይጣን ሽንገላ ተጋላጭ የሚሆኑት ጥልቅ እምነት የሌላቸው ናቸው:: ይህንንም የሚያሳካው የአላህን(ሱ.ወ) ሰማያዊ አዋጅ እንዲጻፈሩ በማድረግ ነው:: በሚቀጥለው የቁርአን ጥቅስ ሠይጣን እራሱ ስህተቱን እንደሚያምን ይናገራል:-

وَقَالَ ٱلشَّيْطَٰنُ لَمَّا قُضِىَ ٱلْأَمْرُ إِنَّ ٱللَّهَ وَعَدَكُمْ وَعْدَ ٱلْحَقِّ وَوَعَدتُّكُمْ
فَأَخْلَفْتُكُمْ ۖ وَمَا كَانَ لِىَ عَلَيْكُم مِّن سُلْطَٰنٍ إِلَّآ أَن دَعَوْتُكُمْ فَٱسْتَجَبْتُمْ لِى ۖ فَلَا تَلُومُونِى

[19] سورة فاطر

[20] سورة سبأ

وَلُومُوٓاْ أَنفُسَكُم مَّآ أَنَا۠ بِمُصْرِخِكُمْ وَمَآ أَنتُم بِمُصْرِخِيَّ إِنِّي كَفَرْتُ بِمَآ أَشْرَكْتُمُونِ مِن قَبْلُ إِنَّ ٱلظَّٰلِمِينَ لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ [21]

*«ሰይጣንም ሁሉም ነገር ከተጠናቀቀ በኋላ እንዲህ ይላል፡- «አላህ እውነተኛ ቃል ኪዳን ሰጣችሁ::እኔም ቃል ገባሁላችሁ:: ግና ቃሌን አፈረስኩ::እኔ በናንተ ላይ (ወደ ጥፋት) በመጥራት በቀር ምንም ስልጣን አልነበረኝም:: ግና እናንተ ጥሪዬን ተቀበላችሁ እኔን አትውቀሱኝ:: ራሳችሁን ውቀሱ:: እኔ (ከአላህ ቅጣት) ልረዳችሁ አይቻለኝም:: እናንተም እኔን መርዳት አይቻላችሁም:: ከዚህ ቀደም የፈፀማችሁትን እኔን ከአላህ ጋር የማጋራት ድርጊት ካድኩ::በዳዮች በእርግጥም አሳማሚ ቅጣት አላቸው::»(ኢብራሂም 14:22)*

የሰይጣን ተንኮሉ ደካማ እንደ ሆነ ሁሉ ከተንኮሉ መጠበቂያ መንገዱም እንዲሁ ቀላል ነው:: አላህ(ሱ.ወ) ከሰይጣን ጉትጎታ ማምለጫ ዘዴን እንዲህ ያመላክተናል፡-

إِنَّ ٱلَّذِينَ ٱتَّقَوْاْ إِذَا مَسَّهُمْ طَٰٓئِفٌ مِّنَ ٱلشَّيْطَٰنِ تَذَكَّرُواْ فَإِذَا هُم مُّبْصِرُونَ [22]

*«የሰይጣን ጉትጎታ ሲያገኝህም (ከተንኮሉ) በአላህ ተጠበቅ:: እርሱ ሰሚ ዐዋቂም ነውና:: እነዚያ አላህን የሚፈሩት የሰይጣን ጉትጎታ ባገኛቸው ጊዜ (አላህን) ያስታውሳሉ::ወዲያውም (እውነት) ይገለፅላቸዋል::»(አል-አዕራፍ 7:200-201)*

ከዚህ ጥቅስ ሠይጣን በአማኞች ላይ ምንም አይነት ተፅዕኖ ሊኖረው እንደማይችል እንገነዘባለን:: ከሠይጣን ፈተናም ለማምለጥ ብቸኛው አማራጭ ወደ አላህ(ሱ.ወ) ጥላ ስር መጠጋት እና እርሱ ለሚለውም ነገር በትክክል መታዘዝ ነው:: በትክክለኛው መንገድ የሚያስብ ማንኛውም ሰው ነገሮችን በግልፅ ማየት ከቻለ፣ ባለው ኢማን ቁራጥነትና መስዋዕትነት(በአላህ ፈቃድ) ከሰይጣን የማታለያ ዘዴና የጥፋት ወጥመድ በቀላሉ ማምለጥ ይችላል::

---

[21] سورة : إبراهيم
[22] سورة : الأعراف

አብዛኛው ሰው ይህ አደገኛ ሁኔታ ሊመጣበት እንደሚችል አያውቅም:: ስለሆነም ብዙዎች በሠይጣን ክፋት የሚደርስባቸውን ደባ አይረዱትም:: ሠይጣንም እነዚህን ሰዎች በቀላሉ በጆሮቻቸው በማንሾካሾክና በማባበል ወደ ጆሮዎቻቸው ወደ ልባቸው ይጠጋል:: ሰዎችም ይህንን የማታለልና የማባባል ጉትጎታ በመስማት ሠይጣን ወደሚጠራቸው ጉዳና ይሄዳሉ::

ሠይጣን ብልህ የሚመስሉ ሰዎችን ብልህ ወዳልሆኑ ባህሪያት እንዴት ሊያስገባቸው ይችላል? እነዚህን ሰዎች ራሳቸውን አታለው ወደ ጀሃነም ጎዳና እንዲያመሩ የሚያደርጋቸው በምን አይነት መንገድ ነው? በማስከተል ሰዎች እንዴት ራሳቸውን አታለው ወደ ሠይጣን የጥፋት ጎዳና እንደሚገቡና እንደሚሰወጡ ለዚህም ያላቸውን ምክንያት እና በዚህም ወደ እስንዋሪ ጉዳና እንደሚያመሩ እንመለከታለን::

## በቃ! በቃ! ምክንያት አይፍጠሩ!

ከአላህ(ሱ.ወ) ጉዳና ሰዎችን ለማውጣት ሠይጣንም ብዙ ብልሃቶችን ተጠቅሞ አላህ(ሱ.ወ) እርሱን ብቻ እንዲያመልኩ የሚያዘውንና በቃሉም በቁርአን ሊኖር የሚገባውን ኢስላማዊ ስርዓት እንዳንላበስ እንቅፋትና ደንቃራ ይሆናል:: ከእነዚህም ምክንያቶች አንዱ ሰዎች አላህን(ሱ.ወ) ለማምለክ እንደማይችሉ ብዙ ምክንያቶችን በማቅረብ ነው:: በሌላ አባባል ሠይጣን ለሰው ልጅ የሚያደርገው ሁሉ ምክንያታዊ እንዲመስል ያደርጋል::ለምሳሌ አላህን(ሱ.ወ) ማምለክ ያለበትን አንድ ወጣት ገና ብዙ ጊዜ ስላለው ግዴታውን በዚህ ጊዜ ለመወጣት እንዳይጨናነቅ ያደርገዋል::ምክንያቱም የሥራ እና የትምህርት ጊዜ ስላለው ያን ባያደርግ ደግሞ በሌላው የሕብረተሰብ ክፍል ትችትን ያስከትልብሃል በማለት በጆሮ ሊያንሾካሹክ ይችላል:: ግለሰቡም ጥብቅ እና ጠንካራ ኢማን ከሌለው በነዚህ ሁኔታዎች በቀላሉ ሊታለል ይችላል:: ሠይጣንም ይህ ስለማይበቃው ሰውየውን በቀላሉ አይለቀውም:: ከላይ እንዳየነው ሰውዬው ወይም ልጁ ደረጃ በደረጃ ወደ ጀሃነም የሚያስገባውን ሥራ ሁሉ እስኪያሠራው ድረስ አይለቀውም::በዚህም ሰውየው የሚያቀርበው ምክንያታዊ በሚመስል ሽንገላ ትክክለኛ እንደሆነ በማሳመን (በመጉትጎት)

የአላህን(ሱ.ወ) ትእዛዝ በመጣሱ በዚህ ጊዜ አላህን(ሱ.ወ) መገዛት እንደማይችል ና እንዳታተው አድርጎ ለማሳየት ይጥራል፤ ይተጋል።

በእውነት ከላይ ለማየት እንደተሞከረው እያንዳንዱ ሰው በህሊናው ፈጣሪውን አላህን(ሱ.ወ) በትክክል መገዛት እንዳለበት ያውቃል።ሠይጣንም በሚያመጣለት ትክክለኛ በሚመስሉ ምክንያቶች በስርአት አለመገዛቱ ትክክል እንደሆነ ያሳስባል። በሌላ አገላለጽ ምንም እንኳን ምን ማድረግ እንዳለበት ህሊናው ቢያውቅም በተለያዩ ምክንያቶች እራሱን አያሳምንም። እንዲህ ራሱን እያታለለ ትክክለኛውን ነገር ባለማድረግ ለሰይጣን ጉትጎታ ይረታል።

አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን እነዚህ ሰዎች በሰይጣን ማባበል ብዛት እንደሚታለሉ እና እምነታቸውንም እንደሚያጡ ይነግረናል።ከእነዚህም ውስጥ በነብያችን(ሰ.ዐ.ወ) ዘመን ሲኖሩ የነበሩና የኢማን ድክመትም የነበረባቸውን ሰዎች እንዳሉ ምሳሌ ይሰጠናል።ጦርነት ለትክክለኛ ነገር ከሆነ ጂሃድ ተገቢ ነው።ነብያችንም(ሰ.ዐ.ወ) ሰዎች ለትክክለኛው ነገር እንዲያምኑ ነግረዋቸው ነበር።ነገር ግን ሰዎች ራሳቸው ባመጡት ሠበብ ወደ ጂሃድ ላለመሄድ ፈልገው ነበር።አላህም(ሱ.ወ) እነዚህን ሰዎች ልባቸው የታመመ ሰዎች በማለት ይገልፃቸዋል፦

﴿ وَلِيَعْلَمَ ٱلَّذِينَ نَافَقُوا۟ ۚ وَقِيلَ لَهُمْ تَعَالَوْا۟ قَـٰتِلُوا۟ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ أَوِ ٱدْفَعُوا۟ ۖ قَالُوا۟ لَوْ نَعْلَمُ قِتَالًا لَّٱتَّبَعْنَـٰكُمْ ۗ هُمْ لِلْكُفْرِ يَوْمَئِذٍ أَقْرَبُ مِنْهُمْ لِلْإِيمَـٰنِ ۚ يَقُولُونَ بِأَفْوَٰهِهِم مَّا لَيْسَ فِى قُلُوبِهِمْ ۗ وَٱللَّهُ أَعْلَمُ بِمَا يَكْتُمُونَ ﴾[23]

*«....ኑ በአላህ መንገድ ተዋጉ፤ወይም ቢያንስ (ሀገራችሁን ከጠላት ጥቃት) ተከላከሉ።»በተባሉ ጊዜ፦«ውጊያ መኖሩን ብናውቅ ኖሮ በእርግጠም እንከተላችሁ ነበር።» አሉ።እነርሱም ያን ጊዜ ከእምነት ይልቅ ለክህደት የቀረቡ ነበሩ፤ ልቦናዎቻቸው ውስጥ የሌለውን በአፋቸው ተናገሩ አላህ (ልባቸው ውስጥ) የደበቁትን (ሚስጥር) ከማንም ይበልጥ አዋቂ ነው።»(ኣሊ-ዒምራን 3:167)*

[23] سورة : آل عمران

ይህ የነዚህ ሰዎች አባባል በሰይጣን ተፅእኖ ሥር ውጤት ነው:: ምክንያቱም ምን መደረግ እንዳለበት በህሊናቸው ከማወቃቸው ሌላ የነቢያችንን(ሰ.ዐ.ወ) ትምህርት ሰምተዋል:: እንዲሁም የአላህን(ሱ.ወ) ዲን በደንብ ያውቁታል:: ነገር ግን እውነቱን እያወቁና ግዴታ የተደረገባቸውን ከማከናወን ይልቅ እስከአሁን ድረስ ከቸልተኝነታቸው የተነሳ በሰይጣን ወጥመድ ውስጥ ወድቀዋል::ምንም እንኳን ሙስሊሞች እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ቢያውቁም እንደማያውቁ እየተናገሩ ሌሎች አማኞችና ራሳቸውን ለማታለል ይሞክራሉ::እነዚህ ግለሰቦች በአላህ(ሱ.ወ) ትእዛዝ መሠረት መኖር እንዳለባቸው ጠንቅቀው በደንብ ያውቁታል!እንደዚሁም ውዴታውን ማግኘት እንዳለባቸው ይረዳሉ::ነገር ግን በአንጻሩ እንደ ታዘዙት ግዴታቸውን እንዳልተወጡ ያውቃሉ:: የነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ሸፋዓን (ምልጃን) እንደሚያገኙ በለራሳቸው በመግለፅ ህሊናቸውን ይደልላሉ:: ነገር ግን ምንም እንኳን ከህሊናቸው በተፃራሪ እንደሚሰሩ ቢያውቁም ህሊናቸውን የራሳቸውን በፈጠሩት ልብወለድ ለማሳመን ይሞክራሉ::ቁርአን ይህንን ግብታዊ ባህሪያቸውን በተመለከተና የተጣለባቸውን ሀይማኖታዊ ግዴታ ገቢራዊ ባለማድረጋቸው የሚያቀርቡት ሰንካላ ምክንያት ዋጋ ቢስ መሆኑን ሲያወሳ፡-

فَرِحَ ٱلْمُخَلَّفُونَ بِمَقْعَدِهِمْ خِلَٰفَ رَسُولِ ٱللَّهِ وَكَرِهُوٓا۟ أَن يُجَٰهِدُوا۟ بِأَمْوَٰلِهِمْ وَأَنفُسِهِمْ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ وَقَالُوا۟ لَا تَنفِرُوا۟ فِى ٱلْحَرِّ ۗ قُلْ نَارُ جَهَنَّمَ أَشَدُّ حَرًّا ۚ لَّوْ كَانُوا۟ يَفْقَهُونَ ﴿٨١﴾[24]

*«እነዚያ (በተቡክ ዘመቻ) የቀረት ከመልዕክተኛው ተነጥሎ መቅረታቸው አስደሰታቸው:: በአላህ መንገድ በገንዘቦቻቸውም በነፍሶቻቸውም መታገልን ጠሉ:: «በዚህ ሞቃታማ ወቅት አትዝመቱባ ሲሉም ሰዎች አሳነፉ::የገሃነም እሳት አቃጣይ ነው::» በላቸው ቢገባቸው::» (ሱረቱ ተውባ 9:81)*

[24] سورة: التوبة

ሰይጣን እነዚህን ሰዎች የእየሩን ጸባይ እንደምክንያት እንዲያቀርቡ በማድረግ ወደኋላ እንዲሉ አሳመናቸው:: ዛሬም ቢሆን ሰይጣን ያለምንም ጥርጥር አንድ ነገር ለማድረግ እየፈለጉ የተለያዩ ማባበያዎችን እና ምክንያቶችን እያቀረበ በርካታ ሰዎችን ያሳስታቸዋል::ምክንያቱም የእያንዳንዱን ሰው ድክመት ያውቃል::ሰይጣን የተለያዩ አቅዶችን ለተለያዩ ሰዎች መንደፍ ይችላል:: የሚፈታተናቸው ሰዎች ሳይንቲስቶች፣ ፕሮፌሰሮች፣ወንዶች ወይም መሪዎች ፣ተራው ሕብረተሰብ፣ አርቲስቶች፣ በአጭሩ ሁሉም አይነት ባህል እና ሀብት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ::ሁሉንም ሰዎች በምን ዓይነት መንገድ መቅረብ እንዳለበት ሰይጣን ያውቃል::ማንኛውንም ዓይነት ዘዴ ቢጠቀም በተፅእና ሥር ሊያደርጋቸው የማይችለው እውነተኛ ሙስሊሞችን ብቻ ነው:: አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን እንደሚለው አላህን(ሱ.ወ) ስለሚፈሩና ትጣቱንም ስለሚጠነቀቁና በተሰጣቸው ጎዳና በጥንቃቄ ስለሚጓዙ ነው::እውነተኛ ሙስሊሞች ከዚህ በተጨማሪ በጣም በጉብዝና ህሊናቸውን ያዳምጣሉ፣ አይምሮአቸውንም ይጠቀማሉ እንዲሁም በአላህ(ሱ.ወ) እምነት አላቸው:: ሰይጣን አንተንም በእሳት ውስጥ ከራሱ ጋር ለመጨመር እንደሚፈልግና እቅድም እንደሚያወጣ እንዳትረሳ:: ባገኘሸው አጋጣሚ ሁሉ ወደ ክፉት ተግባር ሊነዳህ ያፈልጋል:: በሰይጣን ይህንን እድል አትስጠው:: የሚቻለውን ምክንያት ሁሉ በጆርህ ያንሾካሹክልሃል:: የአላህን(ሱ.ወ) መንገድ እንዳትከተል፣ እሱን እንዳትታዘዝና እንዳታመልክ ለማድረግ ይታገላል:: በተጨማሪም በጣም የሚስጥና ምክንያታዊ በሚመስል መንገድ ጉዳዩን ያቀርብልሃል::በዚህም ያሳምንህና እራስህን እንድታታልል በማድረግ ከጫወታ ውጭ ያደርግሃል::

ህሊናህን በማዳመጥ በቀላሉ የአላህን(ሱ.ወ) ውዴታ እንድታገኝ ወደሚያደርግህ ዲናዊ መመሪያ በመመለስ ከርሱ ተፅእኖ ትጠበቃለህ:: በዚህ ዓለም ራስህን ከጀሀነም እሳት ከመከላከል ሌላ ምንም በጣም አስፈላጊ ወይም አስቸኳይ ነገር ምን አለ? ስለዚህ ከሰይጣን ምክራዊ ማሳመኛዎች የሚቀርቡልህ አንተ ራስህን እንድታታል የሚያበረታቱህን ማድመጥ የለብህም:: ምክንያቱም በቂያማ እለት ምንም አይነት ከንቱ ምክንያት ተቀባይነት የለውም:: አላህ(ሱ.ወ) በቁርአኑ እንደሚነግረን የምክንያት ማቅረብን አይቀበልም:: ይህ

ነው እውነቱ ስለዚህ ተጠንቀቅ! በኢስላም መሠረት ህይወትዎን ላለመምራትዎ ምክንያት አቀርባለው ብለው በማሰብ በማንኛውም ሁኔታ እራስዎን አያሞኙ።

## አቅጣጫ እንዳይስቱ!

ሌላኛው የሰይጣን ታክቲክ ሰዎችን ምንም ወደ ማይጠቅም እና ዓላማ ወደሌለው ሥራ ማስቀየስ ነው።ከአላህ(ሱ.ወ) ፈቃድ ጋር ምንም የማይስማሙ እንቅስቃሴዎች እና ሥራዎችን በሚያማምሩ ቀለሞች ይቀባና በሚስብና አምንታዊ በሆነ መልኩ ጎላ ብለው እንዲታዩ ያደርጋቸዋል።በዚህ ሥር የሚወድቅ ሰው እራሱን ሙሉ በሙሉ ለዓለማዊ እቅዶች፣ጥቅሞች እና ግቦች አሳልፎ ይሰጣል። እነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ ሲገባ፣ አንድ ቀን የዚህ ዓለም ህይወቱ እንደሚያበቃ በአእምሮው ውል አይልበትም።እንዲሁም በአላህ(ሱ.ወ) ፊት ለተጠያቂነት እንደሚቀርብም ጭምር በአዕምሮው ውል አይልም። በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ እንደገለፅነው ህይወቱን በሙሉ የሚያጠፋው ከፍተኛ ስልጣንን፣ብዙ ገንዘብንና መዋዕለ ንዋዮችንና ደማቅ የወደፊት ኑሮን ሲያሰላስልና ሌተቀን ሲያውጠነጥን ይኖራል። የት እንደሚሞትና እንዴት እንደሚሞት፣ በሚቀጥለው ሰከንድ ስለመኖሩ እንኳን ዋስትና የሌለው ሰው እንዲህ ያለ ፍሬ ቢስ ፍላጉትና ቀመር ሲኖረው በጣም ግዙፍ ስህተት እንደሆነ ግልፅ ነው። ነገር ግን ለአብዛኛዎቹ ሰዎች፣ እንደዚህ መኖር አስፈላጊ እንደሆነ እራሳቸውን አሳምነዋል። እራሳቸውን በመደለል በቁርአን ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ማሰብ ያቆማሉ። የራሳቸውን በማታለል ኑሮአቸውን ይቀጥላሉ። በዚህ መሠረት ያዘጋጁትን እያንዳንዱን አለማዊ ግብ ልክ በዓለም ላይ እንዳለ ወሳኙ ነገር አድርገው ይቆጥሩታል። ለምሳሌ ዋነኛው የፀሐፊ አስፈላጊው ኢላማ የአለቃዋን ስብሰባ አለመርሳት፣ ለተማሪ የሚቻለውን ትልቁን ውጤት ማምጣት፣ ለሱቅ ሻጭ ብዙ ጫማዎች በቀን ውስጥ መሸጥ፣ ለቢዝነስ ሰው ዋነኛ ጨረታዎችን ማሸነፍ፣ ለአትሌት በውድድሩ ላይ ትልቅ ውጤት ማምጣት፣ ለዘፋኝ ብዙ ሰዎች ሲዲውን እንዲያደምጡ ማድረግ፣ ለወጣት ሴት ወደ የምትሄድበት ፓርቲ በጣም ቆንጆ ልብስ መልበስ፣ ለተርጓሚ ትክክለኛዎቹን ቃላት ማግኘት፣ እና ለፀሐፊ

በጣም ስኬታማ የሆኑ መጽሐፎች እና ጽሑፎች መጻፍ:: መጀመሪያ ላይ እንዳልነው እነዚህ የሰው ልጅ በህይወቱ የሚመኛቸው ናቸው::ለሰው ልጅ እነዚህ ሁሉ በላይ የአላህን(ሱ.ወ) ውዴታ በማግኘትና የእርሱ ባሪያ በመሆን ከሚገኘው ጀነት ጋር በፍጹም አይነጻጸሩም:: ታዲያ ለጀነት ከሚሰሩው ልፋት የበለጠ ምን አስፈላጊና አንገብጋቢ ሥራ አለ?

ሰው ራሱን ካታለለ፣ በእውነቱ ከሆነ በዚች ዓለም የመኖሩ ምክንያት እነዚህ የዓለማዊ ፍላጐቶቹ ብቻ ናቸው ብሎ ካመነ በድንገት ከሞት ጋር ፊት ለፊት ሲፋጠጥ ትልቅ ፀፀት ይሰማዋል:: እስከዚያች ደቂቃ ድረስ በጣም አስፈላጊዎቹ ነገሮቹ ቤቱ፣ንግዱ፣ሚስቱ(ባሏ)፣ መኪናው፣ ዲፕሎማዎቹ፣ ጓደኞቹ፣ቤተሰቦቹና የቢዝነስ ትውውቆቹን አድርጐ ያምናል:: ነገር ግን የሞትን መልአክ ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያየው ብልጭልጩ ዓለም እንዴት የውሸት እንደነበሩና መፈተኛዎቹም ጭምር እንደነበሩ ይረዳል:: ከዛ በኋላ ወዲያውኑ የጀነት ብዙ ኒዕማ በአንድ በኩል እና ሀይለኛ እሳት የአካል እና የአእምሮ ስቃይ በሌላ በኩል፣ እርዳታ የለሽ ተስፋ የማይሰጥ እና ፀፀት በአላህ(ሱ.ወ) በሥራው የተጠያቂነትን ቃል ሲሰጥ አመድ አፋሽ ሆኖ ሲቀር በገሀድ ያያል:: በዛች ደቂቃ አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ የአላህን(ሱ.ወ) ውዴታ ለማግኘት የሚሰራው ሥራ መሆኑን በተግባር ያረጋግጣል:: ነገር ግን ይህ ሰው በህይወቱ ሙሉ እንዲዚህ አይነት ነገር አድርጐ አያውቅም:: የአላህን(ሱ.ወ) ፈቃድ ለማግኘት ሞክሮ አያውቅም::በትልቅ ምሬት እድሜውን ሙሉ ጥረት ያደረገበት ዓላማው እድሜውን የገፋበት እና ህይወቱን ያበላሸበት ምንም የማይፈይድ ከንቱ መሆኑን ይረዳል:: እውነቱ ግን ይህ ሊረዳው የማይችለው ነገር አልነበረም:: በህሊናው ምን መሆን እንደሚጠበቅበት ያውቅ ነበር:: ነገር ግን እራሱን በማታለል ከዚህ ሲሸሽ ነበር:: አላህ(ሱ.ወ) በቁርአኑ ውስጥ ስለ እንደዚህ አይነት ሰዎች እንዲህ ይነግረናል፦

﴿ وَزَيَّنَ لَهُمُ ٱلشَّيْطَٰنُ أَعْمَٰلَهُمْ فَصَدَّهُمْ عَنِ ٱلسَّبِيلِ وَكَانُوا۟ مُسْتَبْصِرِينَ ﴾ [25]

---

[25] سورة : العنكبوت

*«....ሰይጣን (ከፉ) ሥራዎቻቸውን መልካም አደርጐ አሳያቸው::ከ(ቀኑ) ጐዳናም አገዳቸው::የማሰብ ችሎታው ነበራቸው(ግና አልተጠቀሙበትም)::»(አል-ዐንከቡት 29:38)*

በሌላ አባባል እነዚህ ሰዎች እውነቱን ለማወቅ(ለማየት) ብቁ ቢሆኑም በሰይጣን ማታለያ ሥር ይወድቃሉ:: እናም ህይወታቸውን በማይረቡ ነገሮች ላይ ያጠፋሉ::አላህ(ሱ.ወ) በዚህ ጥቅስ እንደሚነግረን ከሞቱ በኋላ ጥፋታቸው (ስህተታቸውን) ማመን ለእነዚህ ሰዎች ምንም አይፈይድላቸውም:-

وَجَآءَ رَبُّكَ وَٱلْمَلَكُ صَفًّا صَفًّا ﴿٢٢﴾ وَجِاْىٓءَ يَوْمَئِذٍۭ بِجَهَنَّمَ ۚ يَوْمَئِذٍ يَتَذَكَّرُ ٱلْإِنسَٰنُ وَأَنَّىٰ لَهُ ٱلذِّكْرَىٰ ﴿٢٣﴾ يَقُولُ يَٰلَيْتَنِى قَدَّمْتُ لِحَيَاتِى ﴿٢٤﴾ فَيَوْمَئِذٍ لَّا يُعَذِّبُ عَذَابَهُۥٓ أَحَدٌ ﴿٢٥﴾ وَلَا يُوثِقُ وَثَاقَهُۥٓ أَحَدٌ[26] ﴿٢٦﴾

***«ጌታህ በመጣ ጊዜ፣ መላእክትም በሰልፍ በመጡ ጊዜ(የሚከሰት አስደንጋጭ ቀን) ገሃነምም የዚያን ቀን እንድትመጣ ይደረጋል::ያን ቀን የሰው ልጅ(በዚህች ዓለም ህይወቱ የፈፀመውን እያንዳንዱ ተግባር) ያስታውሳል፣(ጥፋቱን ይገነዘባል) ግና ማስታወስ ምን ሊፈይደዋልካ ወይኔ ለዘላለማዊ ሕይወቴ (የሚጠቅመኝን ጽድቅ ተግባር) ባስቀደምኩ ኖሮ !» ይላል፣(በቁጭት) በዚያን ቀን ወንጀለኛ ከእርሱ(ከአላህ) ይበልጥ የሚቀጣ አንድም የለም::እንደርሱ የሚርድም የለም::»(አል-ፈጅር 89:22-26)***

እንደዚህ ከሚሉት አንዱ ላለመሆን ከሞት በኋላ «ይህ ቢሆን ኖር......» ከማለትህ በፊት አሁኑኑ የህይወትህ ትክክለኛ ዓላማ ምን እንደሆነ አሁኑኑ ቆም ብለህ አስብ!. ተግባርህም ሁሉ ምንያህል ይህንን ዓላማ ከዳር እንደሚያደርስም ጭምር አስተንትን:: ተጠንቀቅ! የምትሠራቸው እርባና ቢስና ዓለማ የለሽ ሥራዎች ጠቃሚ ናቸው ብለህ በማሰብ እራስህን አታታልል:: ይህ ለምትሠራው ነገር ሁሉ ተጠያቂ ነህ:: በቀን ውስጥ ለምትሠራው እያንዳንዱ ሥራ ሁሉ:: በተፈጥሮ ለብዙ ነገሮች ጠንክረህ መሥራት አለብህ:: ተግባርህ ሁሉ ዓላማው የአላህን(ሱ.ወ) ውዴታ በማግኘት ጀነቱን

---

[26] سورة : الفجر

የሚያጎናጽፉህ መሆን አለባቸው። ማንኛውም ሥራ አላህ(ሱ.ወ) የማይፈቅደው አይነት መሆኑን ኢስላም ካስተማረህ እንዲሁም ከሞት በኋላ ላለው ህይወትህ ጠቃሚ ካልሆነ አቁመው። ጥሩ እና ጠቃሚ ናቸው ዲኑ በሚላቸው ሥራዎች ላይ ብቻ እራስህን አሳልፈህ ስጥ። ህሊናህ በጣም አመቺ በሆነ መንገድ ይህንን እንድትለይ ያስችልሃል። ህሊናህን አድምጥና እርምጃ ውሰድ። ሰይጣን ዋጋ የሌላቸው እና አሳሳች ነገሮች እያመጣ አቅጣጫህን እንዲያስቀይረህ አታድርገው።

## በሐሰት አይደለሉ!

ሰዎችን ከአላህ(ሱ.ወ) መንገድ በማስቀየሱ ሥራው ሰይጣን ጠቃሚ ያልሆኑ ሥራዎችን በጣም አስፈላጊ ከማስመሰል አያቆምም። በተጨማሪም ብዙ አይነት መደለያዎችን ያቀርባል። ተፈፃሚነት በሌለው ነገር ከንቱ ተስፋ ይሰጠናል። አላህ(ሱ.ወ) በዚህ ጥቅስ ስለሰይጣን ሀሰተኛነት ይነግረናል፡-

﴿ يَعِدُهُمْ وَيُمَنِّيهِمْ ۖ وَمَا يَعِدُهُمُ ٱلشَّيْطَٰنُ إِلَّا غُرُورًا ﴾[27]

*«(ተፈፃሚነት የሌለው) ተስፋ ቃል ይሰጣቸዋል።ከንቱ ምኞቶችንም ያስመኛቸዋል። ሰይጣን ከንቱ ቃልን እንጅ አይገባላቸውም።»(አን-ኒሳእ 4:120)*

በሰይጣን ተፅእኖ ሥር ያሉ ሰዎች ለዘላለም እንደሚኖሩ አድርገው የረጅም ጊዜ እቅዶችን ይነድፋሉ። የአላህን(ሱ.ወ) ውዴታ ከማግኘት ይልቅ ራሳቸውን እንደ ገንዘብ፣ ንብረት፣ ስልጣን እና ደረጃ ላሉት ለዓለማዊ ፍላጎቶች አሳልፈው ይሰጣሉ።በሌላ ጥቅስ አላህ(ሱ.ወ) ይህንን ሌላ የሰይጣን ማሳሳቻ አድርጎ ይወስደዋል፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ ٱرْتَدُّوا۟ عَلَىٰٓ أَدْبَٰرِهِم مِّنۢ بَعْدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُمُ ٱلْهُدَى ۙ ٱلشَّيْطَٰنُ سَوَّلَ لَهُمْ وَأَمْلَىٰ لَهُمْ ﴾[28]

---

[27] سورة : النساء

[28] سورة : محمد

*«እነዚያ ቅኑ ጉዳና ግልጽ ከሆነላቸው በኋላ ወደ ኃላ ያፈገፈጉት ሰይጣን (እኩይ ምግባራትን) መልካም አደርጉ አሳደታቸዋል:: በማይጨበጡ ተስፋዎችም አንገዷቸዋል ::» (ሙሐመድ 47:25)*

ማንኛውም ሰው ዘርፈ ብዙ እቅዶች እና ለብዙ ሺህ ጉዳዮች እንደየሁኔታውና እንደጉዳዩ ሰፋትና ጥበት ሁኔታ ራሱን ይዘፍታል:: ምንም እንኳ የሰዎች እቅድ እንደሞያቸው፣ እንደ እድሜያቸው እና የህብረተሰብ ደረጃቸው ቢለያይም በአብዛኛው ዓለማዊ ነው:: ለምሳሌ ነጋዴ የወደፊት ትልቁ ምኞቱ ትልቅ ፋብሪካ እንዲኖረው ነው:: የፋብሪካው ባለቤት ከሆነ በኋላ ደግሞ እቃዎቹ በመላው ዓለም እንዲሸጡለት ነው:: ወይም አንድ ዘፋኝ ደግሞ በሀገሩ ውስጥ በሁሉም ሰው ለመታወቅ፣ ለመወደድ እና ለመከበር በተጨማሪም ችሎታው ለማስመስከር ነው:: በዚህ ስኬታማ ሲሆን ደግሞ በዚሁ ሥራ ዓለም ዐቀፍ እውቅና፣ስኬት… ወዘተ እንዲኖረው ነው:: እንደዚህ አይነት ምኞት ስላላቸው የተለያዩ ሰዎች ምሳሌ መስጠት እንችላለን:: በዚህ ዓለም ኑሮ ውስጥ ፍላጉታቸውን ለማሟላት እንደዚህ አይነት ሰዎች ሌተቀን ይሠራሉ:::ብዙ መስዋቶቶችን ይከፍላሉ:: ብዙ አደጋዎችን ያጋጥማቸዋል:: እንዲሁም ከብዙ አይነት መሠናክል ለማምለጥ ይታገላሉ:: ሁሉም ሰው ይህንን ቅድሚያ ሰጥቶ ያስባል:: ነገር ግን የፈለጉትን ለማሳካት በህይወታቸው ረጅም ዓላማ እንግበው ይነሳሉ:: ግና ይህንን ለማሳካት የህይወታቸው ራዝማኔ በቂ ነውን? ነገር ግን እላይ በተጠቀሱት እቅዶች በአንዱም ስኬታማ የመሆን ዋስትና የለም:: በአንጻሩ ሞት ሁሉም ጋር እንደሚደርስ እርግጥ ነው:: ምንም እንኳ ይህ ቢሆንም እነዚህ ሰዎች ከሞት በኋላ ለሚያጋጥማቸው አስጨናቂ ዓለም ምንም አይነት እቅድ ወይም ዝግጅት የላቸውም:: መላ ሕይወታቸውን ዓለማዊ ምኞታቸውን ዕውን በማድረግ ላይ ያውሉታል:: በቁርአን ላይ እንደተገለጸው ሰይጣን ተስፋ ስለሰጣቸውና እነርሱም ሕይወታቸውን በእነዚህ ተስፋዎች በመታለል እንዲያልፍ ስለሚስማሙ፣ አንድ ቀን ሞት እንደሚመጣና በዚህም የተነሳ ዕቅዶቻቸው በሙሉ ያለፍጻሜ በጅምር እንደሚቀሩ እንኳን አያስቡም:: አንድ ሰው የረጅም ጊዜ ዓላማዎችን ከማሳደድ ይልቅ፣ለአላህ(ሱ.ወ) ሀላፊነት እንዳለበትና በፍርዱ ቀንም እርሱ ፊት ይህንኑ እንደሚጠየቅ በማወቅ አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን በገለጸልን መንገድ

መኖር ይገባዋል፡፡ይህ ካልሆነም ፣ለዘላለማዊ ሕይወት መዘጋጀት ስላቃተውና የተሰጠውን ዕድል ስላልተጠቀመ ጀነት ከመግባት ይከለከላል፡፡ አላህ(ሱ.ወ) በፈቀደለት ጊዜ ራሱን በከንቱ ሥራዎች የሚያባክን ሰው በወዲያኛው ዓለም ለፀፀት ይዳረጋል፡፡ ይህን አስመልክቶ የሚከተለው ማስጠንቀቂያ ቀርቦልናል:-

﴿٣٧﴾ أَوَلَمْ نُعَمِّرْكُم مَّا يَتَذَكَّرُ فِيهِ مَن تَذَكَّرَ وَجَآءَكُمُ ٱلنَّذِيرُ [29]

*«መገሰፅ የሚሻ ሁሉ ሊገሰፅ የሚችልበትን ያህል ዕድሜ አልሰጠናችሁምን?» (ፋጢር: 35:37)*

በዚህ ምዕራፍ እንደተገለጸልን እያንዳንዱ ሰው ምክር የሚቀበልበትና የራሱን የኅሊና ድምፅ የሚያዳምጥበት ጊዜ ተሰጥቶታል፡፡ ሰይጣን ምንም ያህል ወደተሳሳተ ጐዳና ሊመራው ቢሞክርም፣ ሰው ጥሪውን ንቆ የአላህን(ሱ.ወ) መንገድ የመከተል ዕድል አለው፡፡ይህን የማድረጊያው ብቸኛው መንገድ በአላህ(ሱ.ወ) ላይ የሚኖር ፍጹም ኢማንና ተወኩል ነው፡፡ ሰይጣን በእነዚህ ፀባያት ወደ ሰው የሚገፋፋው እያንዳንዱ ጥሪትና የሚሰጠው እያንዳንዱ ተስፋ ከንቱ መሆኑን ቁርአን ይነግረናል:-

﴿٦٤﴾ وَٱسْتَفْزِزْ مَنِ ٱسْتَطَعْتَ مِنْهُم بِصَوْتِكَ وَأَجْلِبْ عَلَيْهِم بِخَيْلِكَ وَرَجِلِكَ وَشَارِكْهُمْ فِى
ٱلْأَمْوَٰلِ وَٱلْأَوْلَٰدِ وَعِدْهُمْ ۚ وَمَا يَعِدُهُمُ ٱلشَّيْطَٰنُ إِلَّا غُرُورًا ﴿٦٥﴾ إِنَّ عِبَادِى لَيْسَ لَكَ
عَلَيْهِمْ سُلْطَٰنٌ ۚ وَكَفَىٰ بِرَبِّكَ وَكِيلًا [30] ﴿٦٥﴾

*«ከነርሱ ውስጥ የቻልከውን በድምጽህ አታልል፡፡ በፈረሰኛና በእግረኛ ሠራዊትህም ዝመትባቸው፡፡ገንዘባቸውንም፣ልጆቻቸውንም ተጋራቸው፡፡ቃልም ግባላቸው፡፡»(አለውም)፡፡ሰይጣን የሚገባላቸው ቃል ከዳን ማታለል እንጅ ሌላ አይደለም፡፡«በባሮቼ ላይ ግን ቅንጣት ሥልጣን የለህም፡፡»(አለውም)፡፡ረዳትነት በጌታህ በቃ፡፡»(አል-ኢስራእ 17:64-65)*

ሰይጣን ዓለማዊ ምኞቶችንና ረጅም ዕቅዶችን በማሳደድ በእውነት ሊዘጋጁበት የሚያስፈልግምትን ስፍራ እንዳያስረሳም ይጠንቀቁ፡፡ ዓለማዊ ሐሳቦችንና

---

[29] سورة فاطر
[30] سورة : الإسراء

ኃላፊነቶችን እንደራስዎ አድርገው በመቀበል እንዳች ጠቃሚ ነገር እየሰሩ መሆኑን በማመን ራስዎን እያታለሉ።።የሚከተለውን የአላህ(ሱ.ወ) መመሪያ በሕይወትዎ ለአንድ አፍታ እንኳን እንዲጠፋዎ ባለማድረግ በሥራ ላይ ያውሉት፡-

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ وَلْتَنظُرْ نَفْسٌ مَّا قَدَّمَتْ لِغَدٍ ۖ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرٌۢ بِمَا تَعْمَلُونَ ۝ وَلَا تَكُونُوا۟ كَٱلَّذِينَ نَسُوا۟ ٱللَّهَ فَأَنسَىٰهُمْ أَنفُسَهُمْ ۚ أُو۟لَـٰٓئِكَ هُمُ ٱلْفَـٰسِقُونَ [11] ۝

*«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፡፡ እያንዳንዷ ነፍስ(ከመልካም ተግባር) ለነገዋ ያስቀደመችውን ታስተውል፡፡ አላህን ፍሩ አላህ የምትሰሩትን ሁሉ አዋቂ ነው፡፡ እንደነዚያ አላህን በመርሳታቸው አላህ ራሳቸውን እንዲረሱ እንዳደረጋቸው ሰዎች አትሁኑ፡፡ እነዚያ እነርሱ አመፀኞች ናቸው፡፡» (አል-ሐሽር 59:18-19 )*

## ራስዎን በምንድነው የሚያታልሉት?

ሰዎች ራሳቸውን የሚያታልሉት በምን ዓይነት ውሸት ነው? ሰይጣን ሰዎችን ወደ ጎዳናው ለመቀላቀል የሚሞክረው የተለያዩ የማታለያ ስልቶችን፣ ማባበያዎችንና ተስፋዎችን በመጠቀም ነው፡፡ የተፈጠሩለትን ዓላማ እንዲረሱ በማድረግ፣ ወደ ዓለማዊ ጥቅሞችና አላፊ ምኞቶች ላይ እንዲያተኩሩ ይመራቸዋል፡፡ አንድ ሰው የሰይጣንን ጥሪ ተቀብሎ ከጌታችን ጥሪ ፊቱን ካዞረ፣እውነትን በጥሞና ለማየት ይሳነዋል፡፡ አላህ(ሱ.ወ) በሱረቱ አዝ-ዙክሩፍ ስለ እነዚህ ዓይነት ሰዎች ሁኔታን ገልጾልናል፡-

۝ وَمَن يَعْشُ عَن ذِكْرِ ٱلرَّحْمَـٰنِ نُقَيِّضْ لَهُۥ شَيْطَـٰنًا فَهُوَ لَهُۥ قَرِينٌ ۝ وَإِنَّهُمْ لَيَصُدُّونَهُمْ عَنِ ٱلسَّبِيلِ وَيَحْسَبُونَ أَنَّهُم مُّهْتَدُونَ ۝ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءَنَا قَالَ يَـٰلَيْتَ بَيْنِى وَبَيْنَكَ بُعْدَ ٱلْمَشْرِقَيْنِ فَبِئْسَ ٱلْقَرِينُ ۝ وَلَن يَنفَعَكُمُ ٱلْيَوْمَ إِذ ظَّلَمْتُمْ أَنَّكُمْ فِى ٱلْعَذَابِ مُشْتَرِكُونَ

---

[11] سورة : الحشر

﴿ أَفَأَنتَ تُسْمِعُ ٱلصُّمَّ أَوْ تَهْدِى ٱلْعُمْىَ وَمَن كَانَ فِى ضَلَـٰلٍ مُّبِينٍ ﴿٤٠﴾ فَإِمَّا نَذْهَبَنَّ بِكَ فَإِنَّا مِنْهُم مُّنتَقِمُونَ ﴿٤١﴾ [32]

*«ከአልረሕማን ግሣጼ (ከቁርአን) የሚደናበርም ሰው ለርሱ ሰይጣንን እናስጠጋለን ፣ ስለዚህ ሰይጣን ለርሱ ቁራኛ ነው::እነሱም (ተደናባሪዎች) ተመሪዎች መሆናቸውን የሚያስቡ ሲሆኑ እነርሱ (ሰይጣናት) ከቀጥተኛው መንገድ ከእርግጥ ያግዷቸዋል:: (በትንሣኤ) ወደኛ በመጣም ጊዜ (ቁራኛዬ ሆይ!) በእኔና ባንተ መካከል የምሥራቅና የምዕራብ ርቀት በኖረ ወይ ምኞቴ! ምን የከፋህ ቁራኛ ነህ ይላል::ስለ በደላችሁም ዛሬ እናንተ በቅጣት ተጋሪዎች መሆናችሁ አይጠቅማችሁም:: (ይባላሉ)::አንተ ደንቆሮዎችን ታሰማለህን? ወይስ ዕውሮችንና በግልፅ ጥመት ውስጥ የኾኑትን ሰዎች ትመራለህን?»(አል-ዙክሩፍ 43:36-40)*

በዚህ ምዕራፍ ላይ እንደሚታየው አላህ(ሱ.ወ) እነዚህን ሰዎች እንደ ዐይነ ስውርና መስማት የተሳናቸው ሰዎች አድርጎ ይገልጻቸዋል::ይህ ግን አካላዊ ዐይነ ስውርነት ወይም መስማት መሳን አይደለም::እንዲህ ያሉትን ሰዎች አላህ(ሱ.ወ) ዐይነ ስውርና መስማት የተሳናቸው አድርጎ የሚገልጻቸው በመንፈሳዊ መልኩ ሲሆን፣ እውነቱንም የሚንቁት የእርሱን የእውነተኛ መንገድ ጥሪ ስለማያዳምጡ ነው:: ባጭሩ እነዚህ ሰዎች ዕውቀታቸውንና ጎሊናቸውን መከተል እያቃታቸው፣ የአላህን(ሱ.ወ) መመሪያዎችና የፍርድ ቀንን ይንቃሉ:: ይህን በማድረግ ራሳቸውን(ከማይረባ ነገር) እየጠበቁ መሆኑን ያምናሉ::ሀቁ ግን ራሳቸውን ብቻ እያታለሉ መሆኑ ነው:-

﴿ بَلْ أَكْثَرُهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ٱلْحَقَّ فَهُم مُّعْرِضُونَ ﴿٢٤﴾ [33]

*«...ግና ብዙዎቹ እውነትን አያውቁም በመሆኑም ይሸሻሉ::»(አል-አንቢያእ 21:24)*

*እንደዚሁም:-*

﴿ وَلَـٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٣٠﴾ [34]

---

[32] سورة : الزخرف
[33] سورة : الأنبياء
[34] سورة : الروم

*«....ግና ከሰዎች ብዙዎች ከጌታቸው ጋር መገናኘታቸውን ያስተባብላሉ።»(ሰዑ-ሩም 30፡8)*

እርስዎ ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል ላለመሆን እንደገና በማሰላሰል ራስዎን እያታለሉ አለመሆንዎን ያረጋግጡ! እውነትን ላለማየት ዓይንዎን ጨፍነው ራስዎን ማታለልዎን በዓለም ላይ እያሉ አሁኑኑ ይፈትሹ! ያለዚያ ከዚህ ዓለም በኋላም ከባድ ኪሳራ ይመጣቦታል።

## « ለሳልደረሰብኝ አላውቅም! »

የአንድን ሰው የሕይወት ተሞክሮ እያንዳንዷን ጊዜ ከአንድ የፊልም መቃን (ፍሬም) ጋር ብናነጻጽራት፣በብዙ ትሪሊዮን የሚቆጠሩ መቃኖችን ልናይ እንችላለን። እነዚህ ትሪሊዮኖች እያንዳንዳቸው ለሰውየው የተሰጠውን ዕድል ይወክላሉ።እያንዳንዱ የሕይወት ጊዜ የፍርዱ ቀን ከመድረሱ በፊት ስለ እውነታዎች የማሰብና እውነቱን የማየት ዕድል ማግኛ ነው። ይህንን ቡራኬ ለራሳቸው ጥቅም የሚያውሉ ሰዎች ስለዓለማዊው እውነተኛ አቅጣጫ በማሰብ ይህንኑ ለመረዳት የሚችሉ ሰዎች ናቸው። የማያስቡና ሕይወታቸውን በስህተት ላይ መሥርተው የሚኖሩ ሰዎች በዚህ ዕድል ሊጠቀሙ አይችሉም። በርግጥ ፣የአስተሳሰብ አድማሳቸው ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገር ነው።አንዳንድ ሰዎች ማሰብን ስለወደፊቱ እንደማሰብ ብቻ አድርገው ይቆጥራሉ። ለእነርሱ፣ ስለወደፊት ዕቅድ ማውጣትና በዚህም ላይ መዋዕለ ንዋይን ማፍሰስ ብቻ ነው ማሰብ። ለሌሎችም ማሰብ ስለአለፈው ጊዜ መተረክ ሆኖ ይታያቸዋል።ጊዜያቸውን በሙሉ ባለፈው ጊዜ ምን እንዳተረፉና እንዳጡ በማሰብ ላይ ያጠፉታል። ሌሎችም ስለሳሬ ብቻ እንጂ ስለነገ ማሰብ በፍጹም እንደማይጠቅም አድርገው ያምናሉ። ይህ የእነርሱ አመለካከት ነው። ከቀን ወደ ቀን ይኖራሉ እንጂ፣ የተወሰነ ዓላማ ወይም ግብ የላቸውም።ጠዋት ሲነሱ ቁርሳቸውን ምን እንደሚበሉና ወደ ሥራ በሚሄዱበት ወቅትም እዚያ እንዴት እንደሚደርሱ ነው የሚያስቡት። ለምሳ ከማን ጋር እንደሚሄዱ፣ ወደ ማታ እንግዶቻቸውን ምን እንደሚጋብዟቸውና የትኛውን አክስዮን ቢገዙ እንደሚቀጣቸው ያስባሉ።በማግስቱ ለእግር ኳስ ውድድር ቲኬት ስለማግኘት አለማግኘታቸው፣ ወይም ወደ ፓርቲ ማንን ይዘው እንደሚሄዱ ያሰላስላሉ።

በአጭሩ፣የአብዛኛዎቹ ሰዎች አዕምሮ ባብዛኛው በተራ፣ ቀላልና ዕለታዊ ሀሳቦች የተሞላ ነው።በሚሊዮን የሚቆጠሩ የዓለም ሰዎች ሕይወታቸውን በእነዚህና በተመሳሰሉት ሀሳቦች ተጠምደው ያሳልፋሉ።እነርሱ የሚጓጉት ለዱንያ ብልጭልጭ ነገሮች ሲሆን፣ጠለቅ ስላሉ ነገሮችና ስለ አኺራ (ጀነት፣ጀሃነም) ማሰብ በርግጥ አያረካቸውም።እዚህ ላይ ትክክለኛው እሳቦት ማለት ግን ስለሰው ሕይወት ዓላማ፣ ስለአካባቢያችን ፍጥረት ማረጋገጫ፣ በዓለም ላይ ስለሚታዩት ነገሮች፣ስለ አላህ(ሱ.ወ) የመፍጠር ፍጹም ብቃት፣ስለሞት፣ ስለወዲያኛው ዓለምና የቂያማ ቀን፣ ጥቅልሉ ይይዛል።ይህ ነው አብዛኛው ሰው የሚጉድለው።

ይህን አስተውለዋል? ሰዎች ለዓመታት ተምረው የባዩሎጂ አዋቂዎች፣ መሐንዲሶች ወይም የህክምና ዶክተሮች አሊያም ፕሮፌሰሮች ቢሆኑም ፣ከምንና እንዴት እንደተፈጠሩ ወይም ለምን ዓላማ እየኖሩ እንደሆነ በፍጹም አያስተነትኑም። የመመረቂያ ጽሑፎችን ይጽፋሉ፣የዶክትሬት ዲግሪ ያገኛሉ ፣ የፋካሊቲ ሀላፊዎች ወይም ሰዎችን የሚያክሙ ዶክተሮች ወይም ጠበቆች፣ ቢሆኑም ለምን ወይም እንዴት እንደተፈጠሩ ወይም ስለመፈጠራቸው የአላህ (ሱ.ወ) ባለዕዳ ስለመሆናቸው በፍጹም ለአንድ አፍታ እንኳ ማሰብ የተሳናቸውና የማያውቁ ስንቶች ናቸው? መጻሕፍት የሚደርሱ፣ በቴሌቭዥን ውይይት ላይ የሚካፈሉ፣ ሀሳባቸውን በምክንያት አስደግፈው የሚገልጹና አመለካከታቸውንም ከሽነው የሚሰነዝሩ ቢሆኑም እንኳን፣ የሞትን መኖርና ለአላህ(ሱ.ወ) ስለሚሰጡት መልስ በአዕምሯቸው አንድም እንኳ ጊዜ የማይፈቅዱ ቤቱ ይቁጠራቸው።

እነዚህ ሰዎች ከባድ ስህተት እየሠሩ ነው፣ ምክንያቱም ሞት በማንኛውም ሰው ላይ በፍጥነት ወይም ዘግይቶ ይመጣል። እያንዳንዱን ሰው ስለምድራዊ ቆይታው አላህም(ሱ.ወ) እንዲተርክለት መጥራቱ አይቀርምና። እያወቁ ሀሳበ-ቢስ መሆን ምን ይጠቅማል?

ማንኛውም ጤናማ ሰው ስለ አላህ(ሱ.ወ) መኖር የሚያስብበት አዕምሮ የፍጥረትን ዓላማን በመገንዘብ አላህን(ሱ.ወ) እንዴት ማወቅ እንደሚገባው ለመረዳት የሚያስችለው ኀሊና አለው:: ዳሩ ግን በጣም አንገብጋቢ ስለሆኑት ስለ እነዚህ ጉዳዮች የማያስቡት ሰዎች በዓለማዊ ሕይወታቸው ላይ ተፅዕኖ(አደጋ) ስለሚያደርሱት ሌሎች ነገሮች በግልጽ የማሰብ ችሎታ ያላቸው መሆኑን ነው:: ለምሳሌ፣በንግድ ጉዳዮች ላይ በገንዘባቸው እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በሚገባ ስለሚያውቁ ይህንኑ በትኩረት ያስባሉ:: በሥራ ሕይወታቸው ላይ የሚያጋጥሟቸውን ዝርዝር መልሶችን ለማግኘት የሚችሉም ናቸው:: አንድ ነገር ሲፈልጉ ይህንኑ ለመፈጸም የረጅም ጊዜ ዕቅድ በማዘጋጀት ይህንኑ ደረጃ በደረጃ ሥራ ላይ ያውሉታል::ባጭሩ፣ሰዎች ዓለማዊ ትርፋቸውን ስለሚመለከቱ ጉዳዮች በግልጽ የማሰብ ችሎታ አላቸው:: በዚህ ምክንያት፣አላህ(ሱ.ወ) ካልፈቀደው በስተቀር፣ «አይመስለኝም» ወይም «በአዕምሮዬ መጥቶልኝ አያውቅም» የሚሉት ሃሳቦች በወዲያኛው ዓለም ተቀባይነት አይኖራቸውም::

ማንኛውም ሕፃን ሲወለድ አላህ(ሱ.ወ) ወደ ፈጠረው ዓለም ውስጥ ነው የሚቀላቀለው:: አንድ ሰው ሲመለከት፣ ታላቅ ፣ያሸበረቀ ፍጥረት እንከን የለሽ ቅርፅና እስከ መጨረሻዋ ዝርዝር ድረስ የታቀደ ሥርዓት ያጋጥመዋል:: ስለሚያጋጥመው ነገር የሚያስብ ሰው እነዚህ ነገሮች የተፈጠሩ መሆናቸውን በቀላሉ ለመረዳት የሚችል ሲሆን፣ በዕለታዊ ኑሮና ዓለማዊ ምኞቶች የተጠመደ ሰው ግን የሚያየውን ለዕድል ይሰጥና እውነቱን ሳያስተውለው ይቀራል:: ለእንዲህ ያለውን ሰው ቀላል ሥዕል አሳይተህ «ይህ ሥዕል ራሱን በአጋጣሚ የሳለ ነበር» ብለህ ብትጠይቀው፣ በፍጹም አይደለም፣ የሳለው ሰዓሊ መኖር አለበት» ሲል ይመልሳል:: ይኸው ሰው ግን ስለከበበው ተፈጥሮአዊ ልዩ ሥዕልና ለምን እንደተፈጠረ ማሰብን አይፈልግም:: በተመሣሣይ መንገድ፣ሰዎች የዓለም ላይ ሕይወት ጊዜያዊ መሆኑንና እውነተኛው ሕይወታቸው ከሞታቸው በኋላ የሚጀምረው ዘላቂ ሕይወታቸው መሆኑን ማሰብን አይፈልጉም::ብዙ ሰዎች በየቀኑ ሲሞቱ ቢያዩም፣የራሳቸው ሞት ግን በአዕምሮአቸው ውል አይልባቸም:: ፍጹም

እንማደይሞቱ አድርገው የዓለም ዕቅዶችን የሚያወጡ ሲሆን ስለወደያኛው ዓለም ግን ምንም ዝግጅት አያደርጉም። ስለሰው ተፈጥሮ ዓላማ፣ በመላው ላይ ተሠራጭቶ ስለሚታየው የአላህ(ሱ.ወ) ጥበብ፣ ስለሞት፣ ስለወዲያኛው ዓለም፣ስለፍርድ ቀን ማሰቡ ቀላል ቢሆንም ባለማሰብ እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን እየጎዱ ነው። ሰዎች ከሚያምኑት በተቃራኒ፣ ስለማንኛቸውም ስለ እነዚህ ነገሮች ማሰብ አደናጋሪም ከባድም አይደለም። ረጅም ምርምር ማካሄድ፣ ሁለገብ ትምህርት መቅሰም ወይም ልዩ ልዩ ሰፊ ዕውቀት ማግኘትም አያስፈልግም። ለምሳሌ:- እያንዳንዱ ኅሊና ያለው ሰው እስተሳሰቡ በየቀኑ ወደምንተንፍሰው የሕይወት ማቆያ አየር አስደናቂ አፈጣጠር፣ ወፎችን እንዲበሩ ወደሚያደርገው የተሟላ የክንፍ አደረጃጀትና ወደ አካባቢያችን ያሸበረቀ ዓለም ሊሳብ ይችላል። በተመሣሣይ መንገድ፣ አንድ ሰው የሞት ዜና ዕለታዊ ድርጊት በሆነበት ዓለም እየኖረ አንድ ቀን እንደሚሞት ላለማሰብ አይችልም። አንድ ሰው የኅሊናውን ድምፅ ለመስማት ጆሮውን ካልዘጋ፣ በዋጋቢስ ድርጊቶች ላይ ካልተጠመደና ራሱን በቁስ አካላዊ መጣቀሚያዎች ካላታለለ በስተቀር፣ እነዚህ ጥልቅ ነፀብራቆች በአዕምሮው ውስጥ ሥር ሳይሰዱ አይቀሩም።

ይሁን እንጂ አንድ ሰው ስለነዚህ ነባራዊ እውነታዎች ለማሰብና ይልቁንም ወደስህተት እንዳይወድቅ ሙሉ ፈቃደኝነት ማሳየት ያስፈልገዋል። መዘንጋት የሌለበት እያንዳንዱ ሰው ሠይጣን የሚባል ጠላት ያለበት መሆኑን ነው። ሠይጣን ሰዎች ይህንን በማንፀባረቅና ብሎም ሐቅን በመረዳት ወደ አላህ(ሱ.ወ) እንዲመለሱ ስለማይፈልግ፣በርግጥ ይህን እንዳያደርጉ ሊከለክላቸው ይሞክራል። ለሰዎች በብልጠት ላይ የተመሰረቱ ማባበያዎችን ማቅረብም ይሞክራል። ከእነዚህ የሰይጣን ሸንገላዎች ውስጥ በጣም ውጤታማ የሚመስለው ባለማሰብ ከኃላፊነት ነፃ ሊሆኑ የሚችሉበት ውሸት ነው። በዚህ የሚወድቁ ሰዎች «አላወቅሁም ነበር» ወይም «ማንም አልነገረኝም» በማለት የሚያመልጡ ቢመስላቸውም እንኳን ራሳቸውን እያታለሉ ነው።

ሰዎች ራሳቸውን በማታለል በራሳቸው ላይ እያፈዙ ከደምሰራቸው ይበልጥ የሚቀርባቸው አላህ(ሱ.ወ) ስለእያንዳንዱ ከንቱና ሥርዓት የለሽ ድርጊታቸው እንደሚያውቅ ይዘነጋሉ። በመሆኑም አላህ(ሱ.ወ) ያስቀመጠበትን ኃላፊነት ችላ የሚል ሰው በርግጥ በራሱ በተፈጠረው ችግር ውስጥ እየወደቀ ነው። ችላ በማለቱና ባለማሰቡ፣ ራሱን ብቻ ነው የሚያታልለው። ወደ ወዲያኛው ዓለም ሲሄድ፣ ወደጉን ሲገፉቸው የኖሩትን እውነታዎች ሲጋፈጥና በአላህ(ሱ.ወ) ዘንድ በሚጠየቅበት ጊዜ «አላወቅሁም»፣ «እንዲህ አልገመትኩም» የሚሉት በእውነት ላይ ያልተመሠረቱትን ማስተባበያ ምክንያቶችን ያቀርባል። እነዚህ ምክንያት ተብዬዎች ዋጋ ቢሶች መሆናቸውን ቁርአን እንዲህ ይነግረናል:-

يَوْمَ لَا يَنفَعُ ٱلظَّٰلِمِينَ مَعْذِرَتُهُمْ ۖ وَلَهُمُ ٱللَّعْنَةُ وَلَهُمْ سُوٓءُ ٱلدَّارِ ﴿٥٢﴾[35]

«በደለኞች(ለጥፋታቸው) የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ቅንጣት ፋይዳ በማይኖራቸው (ቀን) » (ጋፊር 40:52)

እንደዚሁም በሌላ የቁርአን አንቀጽ አላህ(ሱ.ወ) ስለዚህ ዕውነታ ያስጠነቅቃል:-

فَيَوْمَئِذٍ لَّا يَنفَعُ ٱلَّذِينَ ظَلَمُوا۟ مَعْذِرَتُهُمْ وَلَا هُمْ يُسْتَعْتَبُونَ ﴿٥٧﴾[36]

*«በዚያ ቀን እነዚያ የበደሉት ሰዎች ምክንያቶቻቸው ቅንጣት አይፈይዳቸውም። በወቀሳም አይታበሩም።» (አር-ሩም 30:57)*

## «ልክ ነው ። ግን... አልተመቸኝም! »

አላህ(ሱ.ወ) ቁርአንን ያወረደው ለሰዎች መመሪያነት ነው። እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ሁሉም ሰው በቁርአን ውስጥ የተገለጹትን መመሪያዎች የመፈጸም ግዴታ አለበት።በቁርአን በተለያዩ ሁኔታዎች ተቀባይነት እንዳለቸው ከተገለጹት ምክንያቶች በስተቀር ሌሎቹ ዋጋቢስ ናቸው። እያንዳንዱ ሰው ሃይማኖታዊ ግዴታውን በትክክል መፈጸሙን ወይም አለመፈጸሙን በፍርድ ቀን ይጠየቃል።በዚህ መሠረት በአላህ(ሱ.ወ) ተቀባይነት ካላቸው በቂ ምክንያቶች በስተቀር ትክክለኛ ሙስሊም ላለመሆኑ የተለያዩ ምክንያቶችን የሚደረድር ሰው ራሱን እያታለለ ነው።ይህ ግልጽ እውነታ ቢሆንም አንዳንድ

---

[35] سورة : غافر

[36] سورة : الروم

ሰዎች እንደ ምክንያት ያገለግሉናል የሚሏቸውን ሁኔታዎች በማቅረብ አላህ(ሱ.ወ) ያደረገባቸውን ግዴታዎች(ኃላፊነት) ቸላ ይላሉ። ተማሪ ሳሉ እንድ ምክንያት በሥራ ዓለም በሚገቡበት ጊዜ ሌላ፣ ልጆች ሲኖራቸውም እንዲሁ ሌላ ምክንያት ያቀርባሉ። እውነተኛ ኢስላማዊ ኑሮ የመኖር ፍላጐት ስለሌላቸው ግዴታ(ዋጂብ) የተደረገባቸውን ላለመተግበር ልዩ ልዩ በርካታ ምክንያቶችን እንደ እንቅፋት አድርገው ያቀርባሉ።ከሚያቀርቡት መሰናክሎች መካከል ዋነኛው «አሁን ጊዜውና ሁኔታዎች አያመቹኝም» የሚል ነው። ሰዎች በዕለታዊ ኑሮ ላይ ለማንኛቸውም ጉዳይ ጊዜ አያጡም ። ሌላ መስዋዕትነት መክፈል ያለባቸውም ቢሆንም እንኳን ለዱንያ ከሆነ ምንጊዜም ቢሆን ጊዜ ማግኘት ይችላሉ።በተለይም የግል ጥቅማቸው አደጋ ላይ ሲሆን። ከዚህም በተጨማሪ ሁኔታዎች ጠቃሚ የሆነ ገንዘብ የሚያስገኝ ሥራ ለማከናወን ከከለከሏቸው ስለ ሁኔታው በፍጥነት በማሰብ እንቅፋቱ ሲወገድ የሚችልበትን መንገዶች ይፈልጋሉ።ይሁን እንጂ ሰዎች ኢባዳቸውን በመተግበር (በማክበር) ረገድ በአብዛኛው የዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ቆራጥነት አያሳዩም። «መጾም እፈልጋለሁ፣ግን ጊዜ የለኝም። ... ትምህርቱን ማጥናት ስላለብኝ ለሰላት ጊዜ የለኝም።» የሚሉ ምክንያቶች በአካባቢዎ ዘወትር ያጋጥምዎታል። በተመሳሳይ መንገድ፣ «ታጋሽ ሰው መሆን እፈልጋለሁ፣ግን ባንድ ጊዜ አይሆንም።» ወይም «በጣም የሚያናድድ ሁኔታ ላይ ብሆንም እንኳን ልናደድ አልፈልግም።» በማለት ስለመጥፎ ጠባያቸው ምክንያት የሚያቀርቡ በርካታ ሰዎችንም ማየት ይችላሉ። በእውነቱ ከሆነ ቀደም ሲል እንደ ገለጽነው እነዚህ ሰዎች የአላህን(ሱ.ወ) ዲን በሐቅ እየቀረቡት ስላልሆነ፣ጊዜውንና ሁኔታዎችን ቸላ ለማለት የሚችሉ ሲሆን፣ ቁሳዊ ትርፍ ለማግኘት በሚያስቡበት ጊዜ ግን ማንኛዎቹንም መፍትሔዎች ያገኛሉ። ጥያቄው ከፈጠራቸው ከአላህ(ሱ.ወ) የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት የማሟላት ጉዳይ ከሆነ ግን ወዲያውኑ ስለችግሮች አንስተው መነጫነጭ ይጀምራሉ። ይህን ጉዳይ በቀላሉ ለመረዳት እንዲቻል እስቲ አንድ ተጨባጭ ምክንያት እናቅርብ። አንድ ሰው ብዙ ገንዘብ ለሚከፈልበት ሥራ በቀን (ካለው) አንድ ሰዓት እንዲመድብ ቢጠየቅ (የወርሃዊ ደመወዙን አሥር እጥፍ ይሆናል እንበል) በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም ወዲያውኑ ይቀበለዋል። ይህ

ሰው ስለዩኒቨርስቲ ፈተናዎቹ እየተዘጋጀ ሲሆን ወይም በዚያው ወቅት ሌላ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ሊኖረው ይችላል።ምንም ሥራ በመሥራት ላይ ሲሆን ቢችልም ቢያስፈልግ የእንቅልፍ ጊዜውን ይሰዋል፤ ወይም የመዝናኛ ጊዜውን ይቀንሳል እንጂ ጊዜ ማጣትን እንደ ችግር አድርጐ አያቀርብም። አጠቃላይ ፕሮግራሙን ወዳያውኑ ሊሠራ ለሚችለውና ጥሩ ክፍያ ካለው ሥራ ጋር እንዲጣጣም እንደገና ያስተካክላል። ይህ በአብዛኛዎቹ ዘንድ የሚስተዋል የማይካድ ሃቅ ነው።አንድ ሰው የአላህን(ሱ.ወ) ትዕዛዛት በመተግበር ውዴታውን በማግኘት ረገድ ተመሣሣይ ወኔ አለማሳየቱ ቸልተኝነት፣እርግጠኛ ያለመሆንና ኀሊና ማጣት ነው።ከሁሉም በላይ አንድ ሰው ለሊባዳው የሚያገኘው ምንዳ ጀነትና የአላህን(ሱ.ወ) ዘላለማዊ ድግስ ሲሆን ለአንድ ሥራ ከሚገኝ ጥቂት ተጨማሪ ብር ጋር ሊነፃፀር የማይችል ታላቅ ውለታ ነው።

ይሁን እንጂ ብዙ ሰዎች ለማግኘት ጥረት በሚያደርጉት ንብረትና ገንዘብ፣ በሚይዟቸው የክሬዲት ካርዶች፣በሚቆጥቡት ዶላርና ቤቶች፣ በሚያሽከረክሯቸው መኪናዎችና በሚለብሷቸው ውድ ልብሶች በመመሰጥና በመታለል ሃይማኖታዊ ግዴታቸውን ወደ ጐን በመተውና ስለ አኺራ ችላ በማለት ዓለማዊ ጉዳዮችን ወደማሳደዱ እቅጣጫ ያመራሉ።ለወዲያኛው ዓለም (አኺራ) ዋጋ ለሚያስጣቸው ኢባዳ ራሳቸውን ከማስገዛት ይልቅ «ጊዜ የለኝም... ሥራ ይበዛብኛል። ...በጣም ወሳኝ ሥራ አለኝ። ...ኢንሻአላህ ወደፊት ዕቅድ አለኝ ወይም በኋላ እሠራዋለሁ።» በማለት ራሳቸውን ያታልላሉ።አላህ(ሱ.ወ) በሚያስተምረው ከፍተኛ እንክብካቤ መሰረት ሕይወታቸውን አይመሩም፤ አይሰግዱም ወይም አይፆሙም። አላህ(ሱ.ወ) ከሰጣቸው ነገሮች ውስጥ ለችግረኞች ምፅዋት ካለመስጠታቸውም በተጨማሪ ጊዜያቸውን ዓለማዊ ትርፎችን በማሳደድ ብቻ ያባክኑታል። የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ተቀባይነት የሚያገኙ መስሏቸው ኢባዳቸውን የማይተገብሩ ወይም የሚያዘገዩ ሰዎች በወዲያኛው ዓለም ምን እንደሚያጋጥማቸው በሚከተለው አኳኋን ይነገራቸዋል፦

﴿ يُنَبَّؤُا۟ ٱلْإِنسَٰنُ يَوْمَئِذٍۭ بِمَا قَدَّمَ وَأَخَّرَ ۝ بَلِ ٱلْإِنسَٰنُ عَلَىٰ نَفْسِهِۦ بَصِيرَةٌ ۝ وَلَوْ أَلْقَىٰ مَعَاذِيرَهُۥ ۝ ﴾[27]

*«የሰው ልጅ በዚያን ቀን ያስቀደመውና ያዘገየው ነገር (ሁሉ) ይነገረዋል:: በእርግጥም የሰው ልጅ በራሱ ላይ መስካሪ ነው:: (ሳጠፋቸው ጥፋቶች) ሰበቦችን ሁሉ ቢደረድርም::» (ስል-ቂያማህ 75:13-15)*

ስለዚህ ይጠንቀቁ! እንደነዚህ አይነት ሰዎች በወዲያኛው ዓለም ትርጉሙ-ቢስ የሚሆኑ ምክንያቶችን በመፍጠር ራስዎን አያታሉ:: በላይኛው ምዕራፍ እንደተገለጸልን፣ ምንም ዓይነት ምክንያቶችን ብንፈጥርም በርግጥ ተቀባይነት እንደማይኖራቸው ለመረዳት የሚያስችል የማሰብ ችሎታ አለን:: የራሳችንን ፍላጎቶች ካሳደድን ይህንኑ ለአላህ(ሱ.ወ) የመተረክ ግዴታ አለብን:: የመጨረሻው የዘላለም ደኅንነታችን በአላህ(ሱ.ወ) ምሕረት ብቻ የሚገኝ ስለሆነ፣ የምንሠራው ምንም ዓይነት ሥራ ቢሆን የአላህን ምህረት ከሚያስገኝ ይበልጥ አጣዳፊ ወይም አስፈላጊ አይደለም::

## « ችግር አለብኝ! ስለዚህ... »

እንዳንድ ሰዎች አለመመቸትንና ችግርን ሀይማኖታቸውን በቅጡ ላለመከተላቸው የሚያቀርቡት ሰበብ ነው::ለምሳሌ አላህን (ሱ.ወ) ለመገዛት ከልብ የማይፈልግ ሰው ጤናማ ሆኖ ሳለ «በሽተኛ ነኝ» ሲል ምክንያት ያቀርባል::ይህንን በማድረጉ ራሱንና በዙሪያው ያሉ ሰዎችን በማታለል ግዴታውን ላይወጣ ይችላል::እንዲህ ያለው ሰው አላህ(ሱ.ወ) ሁሉን ነገር እንደሚያውቅ ሊዘነጋ አይገባውም::ማንኛውም የሰው ልጅ ሀሳብና ድርጊት ከአላህ ሚስጢር አይደለም:: በአዕምሮ ውስጥ የሚመላለሰውን ሁሉንም ሀሳቦች፣የሰው ልጅ በልቦናው የሚሰማውን ሁሉና በውስጡ በሚስጥር የያዘውን አላህ (ሱ.ወ) ያውቃል:: ቁርአን እንደሚነግረን:-

---

[27] سورة: القيامة

﴿إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ﴾[38]

*«አላህ ልቦና ውስጥ ያለ(ሚስጥራችሁን) ሁሉ አዋቂ ነው::»(ኣሊ-ዒምራን 3:119)*

እነዚህ ሰዎች የአላህን(ሱ.ወ) ውዴታ በማግኘት ጀነት የመግባት ዕድል የተሰጣቸው ሆኖ እያለ ሕመምን እንደምክንያት በማቅረብ ከቁርአን አስተምህሮ ራሳቸውን በጣም በማራቅ የራሳቸውን ግላዊ ፍላጐቶች ያሳድዳሉ:: ሐቀኛ ባለመሆናቸው የተነሳና የአላህን(ሱ.ወ) መመሪያዎች ላለመከተል የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ተአማኒ ባለመሆናቸው በወዲያኛው ዓለም መራራ ሥቃይን ይቀበላሉ::የእካል ሕመም ላለባቸው ሰዎች በቁርአን በርካታ አስተያየቶች (ምሕረት) ተሰጥቷል:: ለምሳሌ ፆም አላህ(ሱ.ወ) ግዴታ ካደረጋቸው ነገሮች መካከል አንዱ ነው:: በመሆኑም፣ ሰዎች ይህን መመሪያ የመፈጸም ግዴታ አለባቸው:: በቁርአን ውስጥ ሰዎች በዚህ አምልኮ ውስጥ በምን አኳኋን ነፃ ሊሆኑ እንደሚችሉ በግልጽ ይነግረናል:-

﴿أَيَّامًا مَّعْدُودَٰتٍ ۚ فَمَن كَانَ مِنكُم مَّرِيضًا أَوْ عَلَىٰ سَفَرٍ فَعِدَّةٌ مِّنْ أَيَّامٍ أُخَرَ ۚ وَعَلَى ٱلَّذِينَ يُطِيقُونَهُۥ فِدْيَةٌ طَعَامُ مِسْكِينٍ ۖ فَمَن تَطَوَّعَ خَيْرًا فَهُوَ خَيْرٌ لَّهُۥ ۚ وَأَن تَصُومُوا۟ خَيْرٌ لَّكُمْ ۖ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ﴾[39]

*«(የፆም) ቀናት በቁጥር የተወሰኑ ናቸው:: ከመካከላችሁ የታመመ ወይም በጉዞ ላይ ያለ (ሕና በዚህ ሳቢያ ፆም የፈታ) ከሌሎች ቀናት ቁጥሮችን (ፆም የፈታባቸውን ቀናት ያከዕ) ይፁም:: እነዚያ ፆምን የማይችሉ ወገኖች (ለእያንዳንዱ ለገደፉት ዕለት ለንድን) ደሃ በማብላት ቤዛ መክፈል አለባቸው:: በፍላጐት ከተጠቀሰው የቤዛ መጠን በላይ የጨመረ( ደሀ ድርጊቱ) ለርሱ በጣም ነው::(በፆም የሚገኘውን የላቀ ምንዳ) ከተገነዘባችሁ::»(አል-በቀራህ 2:184)*

በዚህ ምዕራፍ እንደምንመለከተው፣አላህ(ሱ.ወ) የመንገደኞችንና የህሙማንን ሁኔታ ስለሚያውቅ የመፆምን ግዴታ የሚወጡበትን መንገድ ያቃልላል:: በምዕራፉ በመቀጠልም አላህ(ሱ.ወ) ለሙዕሚኖች ያለውን ከፍተኛው ርህራሄ ያመለክታል:: ወደ ኋለኛው ምዕራፍ፣ አላህ(ሱ.ወ) ሌላ የፆም ሕግ ማቃለያ

---

[38] سورة : آل عمران
[39] سورة : البقرة

እንዳለ ይነግረንና እርሱም ለባሪያዎቹ ምንጊዜም ቀላል ነገሮችን ሊያቀርብላቸው እንደሚወድ ያስታውሰናል:-

﴿ شَهْرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِىٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلْقُرْءَانُ هُدًى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَٰتٍ مِّنَ ٱلْهُدَىٰ وَٱلْفُرْقَانِ ۚ
فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهْرَ فَلْيَصُمْهُ ۖ وَمَن كَانَ مَرِيضًا أَوْ عَلَىٰ سَفَرٍ فَعِدَّةٌ مِّنْ أَيَّامٍ أُخَرَ ۗ يُرِيدُ
ٱللَّهُ بِكُمُ ٱلْيُسْرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ ٱلْعُسْرَ وَلِتُكْمِلُوا۟ ٱلْعِدَّةَ وَلِتُكَبِّرُوا۟ ٱللَّهَ عَلَىٰ مَا
هَدَىٰكُمْ وَلَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ ﴾[40]

*«(አላህ ትፆሙት ዘንድ የወሰነው የረመዳን ወር ለሰው ዘር መመሪያ የሆነው(መለኮታዊ) አመራርና (እውነት ከሐሰት) ለመለየት የሚያስችሉ ግልፅ አናቅጽ የሰፈረበት ቁርአን የወረደበት(ወር) ነው:: ከመካከላችሁ በዚህ ወር ውስጥ የተገኘ (ወሩን) በፆም ማሳለፍ አለበት::ግና የታመመ ወይም በጉዞ ላይ እያለ(በዚህ ሳቢያ ፆም የፈታ) ከሌሎች ቀናት ቁጥሮችን (ፆም የፈታቸውባቸውን ቀናት ያክል) ይፆም:: አላህ በዚህ ድንጋጌው (የሚሻው) ነገሮችን ለናንተ ቀላልና ምቹ ማድረግ ነው::ችግር ውስጥ እንድትወድቁ አይሻም::(ሌላው የዚህ ድንጋጌ ዓላማ) ቁጥሮችን እንድትሞሉ (ፆም የፈታችሁበትን ቀን በመመለስ የረመዷንን ወር በተሟላ መልኩ እንድትፆሙ) ማስቻል ነው:: ለአላህም(ይህን) መመሪያ ለሰጣችሁ ተገቢውን ክብር ታመሰግኑት ዘንድ (ይህ ድንጋጌ ፀና)::»(አል-በቀራህ 2:185)*

ይህ ምሳሌ እንደሚያመለክተው፣ የአላህ(ሱ.ወ) ሃይማኖት እጅግ በጣም ቀላል ስለሆነ፣በአላህ(ሱ.ወ) በሐቅ ለሚያምኑ ሰዎች ምንጊዜም ቀላል መንገድ አለላቸው:: አላህ(ሱ.ወ) በእርሱ ሃይማኖት ለመኖር የሚመኙ ሰዎች ምንም ችግር እንዲያጋጥማቸው አይፈልግም::ለሰዎች አስቸጋሪ የሚሆኑትን ነገሮች ስለሚያውቅ ሸክማቸውን የሚያቃልልላቸው አላህ(ሱ.ወ) ነው:: በቁርአንም በማንኛውም ሰው ላይ ከአቅሙ በላይ የሆነ ሸክም እንደማይጭንበት ይነገራል:-

---

[40] سورة : البقرة

﴿ يُرِيدُ ٱللَّهُ أَن يُخَفِّفَ عَنكُمْ ۚ وَخُلِقَ ٱلْإِنسَٰنُ ضَعِيفًا ﴾[41]

*«አላህ(ፋትዋዎቹና በሸሪዐ የከበሩ በሆኑ ድንጋጌዎች ሕይወትን) ሊያቃልልላችሁ ይሻል:: የሰው ልጅም እጅግ ደካማ ሆኖ ተፈጥሯል::»(አን-ኒሳእ 4:28)*

﴿ وَلَا نُكَلِّفُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا ۖ وَلَدَيْنَا كِتَٰبٌ يَنطِقُ بِٱلْحَقِّ ۚ وَهُمْ لَا يُظْلَمُونَ ﴾[42]

*«ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አናስገድዳትም::ከኛ ዘንድ እውነትን የሚናገር መዝገብ አለን::እነርሱ (ቅንጣት) አይበደሉም::(አል-ሙእሚኑን 23:62)*

ብዙ ሰዎች ከአላህ(ሱ.ወ) የጋለ ውዴታና ርህራሄ አንፃር ሲታይ፣በጣም ውለታ-ቢስ በሆነ መንገድ ይሠራሉ:: ከዓለማዊ ምኞቶች ጋር ባላቸው ቁርኝት የተነሳ ኢባዳ ማድረግ በሚገባቸው መጠን ባለመገዛት በተከታታይ አንዱን ሁኔታ ከሌላው በማከታተል እንደ ምክንያት ያቀርባሉ::በርግጥ፣ ይህንን በማድረግም ራሳቸውን በማታለል ዓለም ውስጥ ናቸው :: ምክንያቱም በቁርአን እንደተገለጸልን አላህ(ሱ.ወ) ከምንም ነገር የተብቃቃ ጌታ ነው:-

﴿ إِن تَكْفُرُوا۟ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَنِىٌّ عَنكُمْ ۖ وَلَا يَرْضَىٰ لِعِبَادِهِ ٱلْكُفْرَ ۖ وَإِن تَشْكُرُوا۟ يَرْضَهُ لَكُمْ ۗ
وَلَا تَزِرُ وَازِرَةٌ وِزْرَ أُخْرَىٰ ۗ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّكُم مَّرْجِعُكُمْ ﴾[43]

*«ብታስተባብሉ አላህ ከናንተ የተብቃቃ ነው:: ለባሮቹ ክህደትን አይወድም:: ብታመሰግኑት በናንተ በእጅጉ ይደሰታል::ኃጢያተኛ ነፍስ የሌላውን ኃጢአት አትሸከምም:: ከዚያም መመለሻችሁ ወደ ጌታችሁ ነው::»(አዝ-ዙመር 39:7)*

ይጠንቀቁ! የአላህ ባሪያ መሆንዎን በተዘዋዋሪ በማስተባበል ምክንያቶችን አይስጡ! ይህንን የሐሰት ምክንያት በአዕምሮዎ ውስጥ እንኳ ውል ሊል አይገባም:: ይህን የሐሰት ምክንያት ገና ወደ አዕምሮዎ ሳያመጡና ራስዎን ሳያታልሉ አላህ(ሱ.ወ) ይህንንም እንደሚያውቅ አይርሱ:: ራስዎንም እያታለሉ ሳሉ ሳያስቡት መልአከ ሞት ቢያገኝዎት ወደዚህ ዓለም ተመልሰው አላህን ለመገዛት ምንም ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖርዎት መመለስ መቼም

---

[41] سورة : النساء
[42] سورة : المؤمنون
[43] سورة : الزمر

አይሳካሉትም:: በዚህ ምድር እየቻሉ (ጤናማና ቻይ ሆነው) ባለመድረጉ በእለተ ትንሳኤ የሚሰማውን ከፍተኛ ጸጸት አላህ(ሱ.ወ) በዚህ ቁርአን እንዲህ ይገልጻል:-

﴿يَوْمَ يُكْشَفُ عَن سَاقٍ وَيُدْعَوْنَ إِلَى السُّجُودِ فَلَا يَسْتَطِيعُونَ ۝ خَاشِعَةً أَبْصَارُهُمْ تَرْهَقُهُمْ ذِلَّةٌ ۖ وَقَدْ كَانُوا يُدْعَوْنَ إِلَى السُّجُودِ وَهُمْ سَالِمُونَ ۝﴾[44]

*«ባት የሚገለጥበትንና ከኃደያን ሰጁድ እንዲያደርጉ የሚጠየቁበትንና (ሰጁድ ማድረግ) የማይችሉበትን ቀን(ዕለተ ቂያማን) (አስታውሳቸው)::(የዚያን ቀን) ዓይኖቻቸው ይሰበራሉ:: (በፍርሃት ይዋጣሉ)፤ውርደትም ትሸፍናቸዋለች::(በምድር ዓለም) ደህና ሆነው እያለ (ለካለ ጤንነት እያላቸው መርጦ የመሥራት ነፃነትም ሳይነፈጋቸው:: ሱጁድ እንዲያደርጉ በእርግጥ ደጠሩ ነበር፤ (በወቅቱ ፈቃደኛ ለልሆኑም)::» (አል-ቀለም 68:42-43)*

## « አላህ ገፉሩ ረሂም ነውና ይምረኛል! »

ብዙ ሰዎች የአላህን(ሱ.ወ) መኖር አውቀው ይህንኑ ቢቀበሉትም ኃያልነቱን ማድነቅ የሚገባቸው ያክል አያደንቁም፣በመታለል ስህተት ላይ የሚወድቁት በአላህ(ሱ.ወ) ጌትነት ሣይሆን ይልቁንም በባህርዩ ላይ ነው::ለምሳሌ አላህ(ሱ.ወ) ለባሪያዎቹ ቸር፣ ውዳጅና ከፍተኛ እዝነት ያለው መሆኑን በትክክል የሚያምኑ ቢሆኑም እንኳን ከሃዲዎችን የሥራቸውን ውጤት የሚመነዳና የሚቀጣ የመሆኑን ባህርይ በርግጥ አያጤኑትም:: አላህን(ሱ.ወ) በሚገባቸው መጠን የማያከብሩት እነዚህ ሰዎች ለአላህ(ሱ.ወ) ምንም ፍራቻ የሌላቸው ወይም ጥቂት ፍራቻ ያላቸው ሰዎች ናቸው:: በወዲያኛው ዓለም ረገድ፤ ለአላህ(ሱ.ወ) ፍርሃት የሌለውና ለሚሠራው ሥራ የሚቀጣ መሆኑን የማያምን ሰው ማናቸውንም ክፉ ድርጊቶችን በቀላሉ መፈጸም ስለሚችል ፤ይህ ለእርሱም በጣም አደገኛ ነው:: እንዲህ ያሉ ሰዎች በምንም መንገድ ከእውነት ጋር ላልተገናኙና ለተሳሳቱ ሀሳቦች ተሸንፈው ምንም እንኳ አላህ(ሱ.ወ) የሚያወግዘውን እያንዳንዱን ሃጢያት ቢፈጽሙም አላህ(ሱ.ወ) «ገፉሩ ረሂም» ስለሆነ ይቅር እንደሚላቸው አድርገው ይወስዱታል:: ሠይጣን

[44] سورة: القلم

ሰዎችን በዚህ አቅጣጫ በመቅረብ የአላህን(ሱ.ወ) ገፋሩ ረሂምነት ብቻ እንዲያስቡና ምንም ነገር ቢሰሩ ይቅርታ እንደሚደረግላቸው አድርገው እንዲገምቱ ያደርጋቸዋል። በጥልቀት ብንመረምር፣ ሃይማኖትን የለሽ የሆኑ የኀብረተሰብ አባላት የተዛባ (የተሳሳተ) አመለካከት ላይ በመመሥረት ከአላህ(ሱ.ወ) መመሪያ ውጭ ይጓዛሉ።እርሱ የከለከላቸውንም ያፈጽማሉ። የማይሰግዱ ወይም የማይፆሙ፣ችግረኞችን የማይረዱና የማይደግፉ፣ለኢስላም የማይቆረቆሩ፣ ከስስት የተነሳ ሃብታቸውን የማያካፍሉ ከሌሎች ያልተገባ ጥቅም የሚወስዱ፣የሚነዱሉ፣ የሚሰርቁና በሌሎች ንብረት አላግባብ የሚጠቀሙና በአካባቢያቸው ያሉትን ሰዎች ወደ ምግባ ብልሹነት የሚገፋ፣ሰዎች እነዚህን ኃጢአቶችን የሚፈጽሙት «ያም ሆነ ይህ አላህ(ሱ.ወ) ገፋሩ ረሂም ነውና ይቅር ይለናል» የሚለውን ሃሳብ በመያዛቸው ነው።ዳሩ ግን፣ ምንም እንኳን አላህ(ሱ.ወ) ተውበትን(ንስሐን) የሚቀበልና ንስሐ የገቡትን ይቅር የሚል ቢሆንም፣እንደዚሁ በዘላለማዊ ዳኝነቱ አግባብ የሆነ ዋጋ ለማንኛውም ተግባር የሚከፍልም እርሱው ራሱ ነው። በርግጥ በፍርድ ቀን ክፉ የሠሩትም ሰዎች የሚገባቸውን ዋጋ ይቀበላሉና።ይህንን አስመልክቶ ቁርአን የሚከተለውን እውነታ ይገልጽልናል:-

أَمْ حَسِبَ ٱلَّذِينَ ٱجْتَرَحُوا۟ ٱلسَّيِّـَٔاتِ أَن نَّجْعَلَهُمْ كَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ
سَوَآءً مَّحْيَاهُمْ وَمَمَاتُهُمْ ۚ سَآءَ مَا يَحْكُمُونَ ﴿٢١﴾ وَخَلَقَ ٱللَّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ بِٱلْحَقِّ
وَلِتُجْزَىٰ كُلُّ نَفْسٍۭ بِمَا كَسَبَتْ وَهُمْ لَا يُظْلَمُونَ ﴿٢٢﴾[45]

***«(ምን!) እነዚያ ክፉ የሠሩት ከነዚያ ካመኑትና መልካም ተግባራትን ከፈፀሙት ጋር እንደምናደርጋቸው ያስባሉን? ሕይወታቸውም ሞታቸውም? ብይናቸው ምን ይህል የከፋ ነው! አላህ ሰማያትንና ምድርን ፍትሃዊ ለሆነ ግብ ፤ሁሉም ነፍሶች-ቅንጣት ሳይበደሉ የሠሩትን ዋጋ ያገኙ ዘንድ ተፈጥሮ ፈጠራቸው።»(አል-ጀሣያህ 45:21-22)***

---

[45] سورة : الجاثية

﴿وَاتَّقُوا يَوْمًا تُرْجَعُونَ فِيهِ إِلَى اللَّهِ ۖ ثُمَّ تُوَفَّىٰ كُلُّ نَفْسٍ مَا كَسَبَتْ وَهُمْ لَا يُظْلَمُونَ﴾[46]

*«ወደ አላህ የምትመለሱበትንና እያንዳንዱ ሰውም ሳይበደል የሠራውን ዋጋ የሚያገኝበትን ቀን ተጠንቀቁ::»(አል-በቀራህ 2:281)*

ይሁን እንጂ ማንኛውም ሰው ፣ሰው ነውና በተፈጥሮ ስህተት የመሥራት ዝንባሌ ስላለው እና በሕይወቱ ውስጥ ስህተት መሥራት ስለሚችል ለፈጸማቸው ስህተቶች የመጸጸት ስሜት ሊኖረው እንደሚችል ልንገልጽ እንችላለን:: ማንም ፍጹም ነኝ ሊል አይችልም:: በዚህም የተነሳ፣ አንድ ሰው በዚህ ዓለም ላይ እያለ አላህ(ሱ.ወ) ይቅርታ እንዲያደርግለት ሊለምን /ሊፀፀት/ ይችላል:: አላህ(ሱ.ወ) ለማንኛውም ሰው እስኪሞት ድረስ የመጸጸት ዕድል ቢፈቅድለትም፣ማንኛውም ጸጸት ከልብ መሆን እንዳለበትና ተቀባይነት እንዲያገኝ መደረግ እንዳለበት ቁርአን ያስተምረናል:: በሚቀጥለው ምዕራፍ ከልብ ፀፀትን ማቅረብ ተቀባይነት የማግኘት ቅድመ ሁኔታ መሆኑን አላህ(ሱ.ወ) ይነግረናል:-

﴿إِنَّمَا التَّوْبَةُ عَلَى اللَّهِ لِلَّذِينَ يَعْمَلُونَ السُّوءَ بِجَهَالَةٍ ثُمَّ يَتُوبُونَ مِن قَرِيبٍ فَأُولَٰئِكَ يَتُوبُ اللَّهُ عَلَيْهِمْ ۗ وَكَانَ اللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمًا ۝ وَلَيْسَتِ التَّوْبَةُ لِلَّذِينَ يَعْمَلُونَ السَّيِّئَاتِ حَتَّىٰ إِذَا حَضَرَ أَحَدَهُمُ الْمَوْتُ قَالَ إِنِّي تُبْتُ الْآنَ وَلَا الَّذِينَ يَمُوتُونَ وَهُمْ كُفَّارٌ ۚ أُولَٰئِكَ أَعْتَدْنَا لَهُمْ عَذَابًا أَلِيمًا﴾[47]

*«አላህ የሚቀበለው የነዚያን ኃጢአት ባለ ማወቅ-የሚሰሩትንና ወዲያውኑም ንሰሐ የሚገቡትን ሰዎች ንሰሐ ነው:: አላህ የእንዲህ ዓይነት ሰዎችን ንሰሐ ይቀበላል:: አላህ ዐዋቂ ጥበበኛ ነውና:: እነዚያ ሞት እስኪመጣባቸው ድረስ ኃጢአት የሚሠሩና (ማዕረ ሞት ላይ ሲሆኑ) እኔ አሁን ንሰሐን ገብቻለሁ::»* የሚሉ ወገኖች እነዚያም ከሓዲ

---

[46] سورة: البقرة
[47] سورة : النساء

*ሆነው የሞቱት ንስሐቸው ተቀባይነት የለውም ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣት አዘጋጅተናል።» (አን-ኒሳእ 4:17-18)*

ሁኔታው እንዲህ ስለሆነ፣አንድ ሰው ወደ ስህተት ሲወድቅ «ምንም አይደለም ያም ሆነ ይህ አላህ ገፉሩ ረሂም ነውና ይቅርታ ያደርግልኛል።» በማለት ነገሩን እንደ ተራ ነገር ከመቁጠር ይልቅ ሁኔታውን ለማስተካከል በወኔ ተነስቶና ወደጌታችን ከልብ በመመለስ በስህተቱ መፀፀት ይገባዋል። ለሰው አስፈላጊው ነገር ከልብ በመነጨና በቅንነት የአላህ(ሱ.ወ) አገልጋይ መሆን ነው። በዚህ መንገድ ብቻ ነው የአላህን(ሱ.ወ) ምህረት ለማግኘት ተስፋ ማድረግ የሚቻለው ።አላህ(ሱ.ወ) ዘንድ ጋሻ(መከላከያ) የማያበጁና ይቅርታ የማይጠይቁ ያም ሆነ ይህ አላህ(ሱ.ወ) ይቅር እንደሚላቸው የሚያስቡ ሰዎች ከቶ ያልጠበቋቸው ውጤቶች ያጋጥሟቸዋል።አላህ(ሱ.ወ) ምንም ነገር ቢሆን ይቅር ይለኛል ብለው በማሰብ እርሱን የማያስደስተውን ተግባራት እንዳይፈጽሙ ይጠንቀቁ። አለበለዚያ ዘላለማዊ ሕይወትዎን በገዛ እጅዎ በተፈጠሩት ስህተት በሚደርስ አስከፊ አደጋ ውስጥ ይከቱታል።

## « ጀነትማ እንገባለን...! »

በኢስላማዊ መንገድ ኑሯቸውን መምራት በተሳናቸው ሰዎች ራሳቸውን ከሚያታልሉባቸው ነገሮች አንዱ ጀነት የመግባት መብት እንዳላቸው አድርገው የማሰብ ጉዳይ ነው።ከእነዚህ አብዛኞዎቹ ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩን ቢቀበሉም እንኳን በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ሕይወት ስለማይመሩ ግን በርግጥ ወደጀነት እንደሚገቡ የተሳሳተ እምነት አላቸው። ሰዎች ለምን ወደዚህ አስተሳሰብ እንደሚደርሱ ባናውቅም ራሳቸውን ከሌሎች ጋር በሚያነፃፅሩበት ጊዜ ግን አብዛኞዎቹ ሰዎች የተሻሉ በመሆናቸው ወደጀነት የመግባት መብት እንዳላቸው አድርገው ይስባሉ። ነገር ግን በጣም የሚያስደንቀው እነዚህ ሰዎች «ጥሩነት» የሚለውን ሀሳብ የሚመሠርቱት በቁርአን መስፈርት ላይ ሳይሆን በራሳቸው የአላዋቂ መመዘኛዎች ላይ ነው። የሚመርጡት አላህ(ሱ.ወ) የሚቀበለውን የሕይወት መንገድና ስነ-ምግባር ሳይሆን የሚኖሩበት ማህበረሰብ የሚቀበለውን የአኗኗር መንገድና ስነ-ምግባር በመሆኑ በተሳሳተ መንገድ ባቀረቡት መመዘኛዎቻቸው ወደ ጀነት ለመሄድ

የተዘጋጁ አድርገው በመገመት ራሳቸውን ያታልላሉ። በርግጥ ያለጥርጥር አላህ(ሱ.ወ) ለአንድ ሰው ወደ ጀነት ለመግባት እንደ ሚፈቅድለት ተስፋ ማድረግ ጥሩና ይህንንም መፈለግ የሚያበረታታ ነገር ነው። ይሁን እንጂ ይህ ከልብ የሚሆነው አንድ ሰው መላ ሕይወቱን አላህን(ሱ.ወ) በመፍራትና ወደ እርሱም መቃረቢያ መንገድን በመፈለግ ባለማቋረጥ ወደጀነት የሚያስገባውን ሥራ ሲሠራ ነው።አላህ(ሱ.ወ) የማይቀበለውን የሕይወት አኗኗር እየኖሩ፣ ለእርሱ ያለብዎትን ግዴታ ሳያሟሉ ወደጀነት እገባለሁ ማለት፣ ፍጹም ከልብ ያልመነጨና ቁልጭ ያለ ራስን ማታለል ነው። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት አንድ ሰው ለአላህ(ሱ.ወ) ያለበትን ግዴታ ችላ በማለትና ለግላዊ ስሜቱና ፍላጎቱ እጅግ በርካታ ጊዜና ትኩረታቸውን በማባከን አላህ(ሱ.ወ) ለእውነኛ ሙዕሚናኖች በጀነት ያዘጋጀውን ታላቅ ድግስ በቀላሉ ሳይለፉ ሊቋደሱ ነው ማለት ነው። ይህ አስተሳሰብ የሚያመለክተው ግለሰቡ ቁርአንን ምንም አለማወቁን ነው። በቁርአን የሚገኙትን እውነታዎች በደንብ የሚረዳ ሰው፣ ሰዎች ራሳቸውን ለማታለል ካላቸው ዝንባሌ በሚነሱ የተሳሳቱ አስተሳሰቦች ላይ ተመሥርቶ ጀነት መግባት እንደማይቻል ያውቃሉ። አንድ ሰው በቁርአን የተገለጸው ጀሀነም መኖሩን ሲያውቅና ስለዚህ ሲያስብ፣ለአንዲት ሰከንድ እንኳን በጀሀነም ለማሳለፍ አያስብም።ጀሃነም ከምንገምተው በላይ በሆነ ሥቃይ፣ መከራና አበሳ የተሞላ ስለሆነ አንድ ሰው ወደ እሳቱ እንዳይገባ ወደ አካባቢው ድርሽ እንዳይል እጅግ ጠንክሮ ይታገላል። በቁርአን እንደተገለጸው የጀሃነም ሥቃይ ሰዎች ወደፊት መኖርን እንዳይመኙና ተቃጥለው መጥፋት ማስመኘት የሚችል ሥቃይ ይሄል፡-

*«በአንድ ላይ ተጠፍረው ከውስጧ ወደ ሚገኝ ጠባብ ሥፍራ በተጣሉ ጊዜም ከዚያው (ተቀጣጥሎና ለመደ ሆኖ)መክሰምን ይመኛሉ።» (ሱረቱል ፉርቃን 25:13)*

ይጣራሉ፡-

وَنَادَوْا يَٰمَٰلِكُ لِيَقْضِ عَلَيْنَا رَبُّكَ ۖ قَالَ إِنَّكُم مَّٰكِثُونَ ﴿٧٧﴾[49]

---

[48] سورة: الفرقان
[49] سورة: الزخرف

*«ማሊክ ሆይ! ጌታህ (ከምንገኝበት ስቃይ) በሞት ይገላግለን።»በማለት(የስቃይ) ድምፅ ያሰማሉ።(ማሊክም):-«(የስም)! እናንተ (ከውስጧ ዝንተ ዓለም) ተቀማጮች ናችሁ።» ይላቸዋል።» (አዝ-ዙኽሩፍ 43:77)*

አላህን(ሱ.ወ) እንደሚገባቸው የማያመልኩና ባህርዩንም የማያውቁ ሰዎች እርሱ ለከሃዲዎች ያዘጋጀላቸውን የገሃነም እሳት አስፈሪነት ትኩረት አይሰጡትም። ይህም የጥንቃቄ ጉድለትን በላያቸው ያመጣባቸዋል።ስለዚህ ጀሃነምን በመፍራትና ከእርሱም ለመሸሽ ከመሥራት ይልቅ አለማዊ የሆኑት ድርጊቶቻቸው ከጊዜው(ፋሽን) ጋር ስለመሄዳቸው በጥልቀት ይጨነቃሉ። ይህ ዓይነቱ አመለካከት በማህበረሰባቸውን ውስጥ በስፋት ተንሰራፍቷል። የግል ፍላጐቶቻቸውንና ስሜቶቻቸውን ለማርካት የአላህን(ሱ.ወ) ትዕዛዝና ክልከላዎች የሚተላለፉ ሰዎች «የተወሰነ ቅጣት በጀሃነም ተቀብለን ከዚያም ወደ ጀነት እንሄዳለን» የሚል እምነት ይይዛሉ። በዚህ ዓለም ላይ በሚኖሩበት ጊዜ የፈለጉትን መሥራት የሚችሉና ከዚያም ይቅርታ ከማግኘታቸው በፊት ለጥቂት ጊዜ በጀሃነም የሚቀጡ ይመስላቸዋል። በርግጥ አላህ(ሱ.ወ) ካልፈቀደው በስተቀር እንደህ አይነቱ ነገር ለማንም ሰው ዋስትና አልተጠም።

የእሳት ሥፍራ የዘላለማዊ ሥቃይ ቦታ ሲሆን በአላህ(ሱ.ወ) ትዕዛዝ መሠረት የማይኖር ማንኛውም ሰው ይህ ዘላለማዊ ቅጣት ሊፈረድበት ይችላል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከዚህ እሳት የሚለቀቁ የሚመስላቸውና አላህን(ሱ.ወ) በተገቢው መንገድ የማይፈሩና የማይጠነቀቁ ሰዎች የእርሱን ፍርድ የማይገነዘቡ ወይም የማይረዱ ሰዎች ናቸው።በርግጥ አላህ(ሱ.ወ) በዚህ ዓይነት ከንቱ ነገር ስለሚያምኑና ሰዎች ምን ሥቃይ እንደሚያጋጥማቸው በቁርአን ላይ ገልጿል:-

۝ وَقَالُوا لَن تَمَسَّنَا النَّارُ إِلَّا أَيَّامًا مَّعْدُودَةً قُلْ أَتَّخَذْتُمْ عِندَ اللَّهِ عَهْدًا فَلَن يُخْلِفَ اللَّهُ عَهْدَهُ أَمْ تَقُولُونَ عَلَى اللَّهِ مَا لَا تَعْلَمُونَ ۝ بَلَىٰ مَن كَسَبَ سَيِّئَةً وَأَحَاطَتْ بِهِ

خَطِيٓـَٔتُهُۥ فَأُوْلَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلنَّارِۖ هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿٨١﴾ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ
ٱلصَّٰلِحَٰتِ أُوْلَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلْجَنَّةِۖ هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿٨٢﴾[50]

*«እሳት በተወሰኑ ቀናት እንጅ አትነካንም» አሉ:: (ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው:- በአላህ ዘንድ ቃል ኪዳን ተገብቶላችኋልን? (ይህ ከሆነ) አላህ ቃልኪዳኑን አያፈርስም:: ወይስ በአላህ ላይ የማታውቁትን ትላላችሁ?» በፍፁም! (በእሳት ትዳረጋላችሁ)! ወንጀሎችን የፈፀሙና በኃጢአት የተዋጡ (ወገኖች ሁሉ) እንዲሁ የእሳት ሰዎች ናቸው:: ከውስጧ ዘንተ ዓለም ይኖራሉ:: (በአንጻሩ) እነዚያ ያመኑት መልካምንም ሥራ የሠሩት እነርሱ የጀነት ሰዎች ናቸው:: ዘንተ ዓለም ከውስጧ ይኖራሉ::»(አል-በቀራህ 2:80-82)*

በሌላ የቁርአን ጥቅስም :-

ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ قَالُواْ لَن تَمَسَّنَا ٱلنَّارُ إِلَّآ أَيَّامًا مَّعْدُودَٰتٍۖ وَغَرَّهُمْ فِى دِينِهِم مَّا كَانُواْ
يَفْتَرُونَ ﴿٢٤﴾[51]

*«ይህ (የዚህ ሽሽታቸው ሰበቡ):- «እሳት የሚያገኘን ለተወሰኑ ቀናት ያክል ብቻ ነው::» ማለታቸው ነው::በሃይማኖታቸው ላይ መቅጠፋቸው አምናቸው::»(ኣሊ-ዒምራን 3:24)*

ከዚህ በላይ ያየናቸው ጥቅሶች እንደሚገልጹት ማን ምን ዓይነት ሥቃይ እንደሚደርስበትና አንድ ሰው በእሳት ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ዐዋቂው አላህ(ሱ.ወ) ብቻ ነው:: «ጊዜዬን ጨርሼ እወጣለሁ» ለሚሉ ሰዎች የሚያጋጥማቸው የተስፋቢስነትና የአጋኘ የለሽነት ተሞክሮና በራሳቸው እብሪትና የተሳሳተ አስተሳሰብ አላህ(ሱ.ወ) በሚከተሉት ሱራዎች ይገልጸዋል:-

قَالَ ٱلنَّارُ مَثْوَىٰكُمْ خَٰلِدِينَ فِيهَآ إِلَّا مَا شَآءَ ٱللَّهُۗ إِنَّ رَبَّكَ حَكِيمٌ عَلِيمٌ ﴿١٢٨﴾[52]

---

[50] سورة : البقرة
[51] سورة : آل عمران
[52] سورة : الأنعام

*«እሳት መኖሪያችሁ ናት:: በውስጧም ዘንታ ዓለም ትኖራላችሁ አላህ የሻቸው ሲቀሩ::» ይላቸዋል::ጌታህ በእርግጥም ጥበበኛም ዐዋቂም ነውና::»(አል-አንዓም 6:128)*

فَمَأْوَىٰهُمُ ٱلنَّارُ ۖ كُلَّمَآ أَرَادُوٓا۟ أَن يَخْرُجُوا۟ مِنْهَآ أُعِيدُوا۟ فِيهَا وَقِيلَ لَهُمْ ذُوقُوا۟ عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴿٢٠﴾[53]

*«ግና እነዚያ ያመፁት መኖሪያቸው እሳት ናት:: በርሷ ሲወጡ በከጀሉ ቁጥር ወደርሷ ይመለሳሉ::» ይባላሉም»(አስ- ጅዳህ 32:20)*

يُرِيدُونَ أَن يَخْرُجُوا۟ مِنَ ٱلنَّارِ وَمَا هُم بِخَٰرِجِينَ مِنْهَا ۖ وَلَهُمْ عَذَابٌ مُّقِيمٌ ﴿٣٧﴾[54]

*«በእሳት መውጣትን ይመኛሉ::ግና ፈፅም በርሷ አይወጡም:: ለነርሱም ቋሚ ቅጣት አለባቸው::» (አል-ማኢዳህ 5:37)*

ከላይ በሚገኙት ጥቅሶች ውስጥ ከተጠሱት ሰዎች ላለመሆን ከፈለጉ ደጋግመው በማሰብ ምንም ነገር ቢያደርጉ፣ምንም ነገር ቢሆን ወደጀነት እሄዳለሁ ለሚለው መሠረተቢስ እምነት መንገድ አይስጡ:: ወይም ቅጣቴን ከተቀበልኩ በኋላ ከጀሃነም እለቀቃለሁ አይበሉ:: ማስረጃ በሌላቸው መለኪያዎች ሣይሆን በቁርአን መሠረት ራስዎን ይፈትሹ:: አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን ጀነትን ለማግኘት ምን ዓይነት ሰዎች መሆን እንደሚገባን በዝርዝር ነግሮናል::ማናችንም ጀነትን የመግባት ዋስትና እንደሌለን አይዘንጉ:: ይቂቅስ በተቃራኒው እያንዳንዳችን በዱንያ ተታለን የአላህን መመሪያ ከጣስን ወደ ጀሃነም የመሄድ አደጋ ሊያጋጥመን እንደሚችል እርግጥ ነው::በዚህ ጉዳይ ለአላህ(ሱ.ወ) ከልባቸው ያደሩና እርቀ አስተዋይ ነቢያት እንኳን እርሱን በጸሎት እንደለመኑ ቁርአን ይጠቁመናል:-

رَبِّ قَدْ ءَاتَيْتَنِى مِنَ ٱلْمُلْكِ وَعَلَّمْتَنِى مِن تَأْوِيلِ ٱلْأَحَادِيثِ ۚ فَاطِرَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ أَنتَ وَلِىِّۦ فِى ٱلدُّنْيَا وَٱلْءَاخِرَةِ ۖ تَوَفَّنِى مُسْلِمًا وَأَلْحِقْنِى بِٱلصَّٰلِحِينَ ﴿١٠١﴾[55]

---

[53] سورة : السجدة
[54] سورة : المائدة

*«ጌታዬ ሆይ! ከብርና ሥልጣን ሰጠኸኝ:: ሕልሞችን መተንተንም አስተማርከኝ:: የሰማያትና የምድር ፈጣሪ (የሆንክ አምላክ ሆይ)! በዚህችም ሆነ በመጭው ዓለም ረዳቴ አንተ ብቻ ነህ::ሙስሊም አድርገህ ግደለኝ:: ከመልካም ሠሪዎችም ፈረጀኝ::(ሲልም አላህን ተማፀነ)::» (ሱረቱ የሱፍ 12:101)*

ማንም ቢሆን ራሱን ማታለል ፈጽሞ አይገባውም:: አጉንብሶ ራሱን ለአላህ(ሱ.ወ) እስተናንሶ እስካልተገዛና የርሱን ውዴታ እስካላገኘ ድረስ የጀነትን በር ሊገባ አይችልም:: በቁርአን ሱራ በሚከተለው ገልጽ ምሳሌ መሠረት ይህ እንደማይቻል አላህ(ሱ.ወ) ይገልጽልናል:-

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَذَّبُوا۟ بِـَٔايَـٰتِنَا وَٱسْتَكْبَرُوا۟ عَنْهَا لَا تُفَتَّحُ لَهُمْ أَبْوَٰبُ ٱلسَّمَآءِ وَلَا يَدْخُلُونَ ٱلْجَنَّةَ حَتَّىٰ يَلِجَ ٱلْجَمَلُ فِى سَمِّ ٱلْخِيَاطِ ۚ وَكَذَٰلِكَ نَجْزِى ٱلْمُجْرِمِينَ[56]

*«እነዚያ አንቀፆቻችንን ያስተባበሉትና በነርሱ ላይም የተኩራሩት ግመል በመርፌ ቀዳዳ ውስጥ ማለፍ እስከምትችል ድረስ የሰማይ በሮች አይከፈቱላቸውም::ጀነትም አይገቡም:: አመፀኖችን በእንዲሁ ዓይነት አኳኋን እንቀጣለን::»(አል-አዕራፍ 7:40)*

## « እኔ ከሲሳው በምን ተለየሁ? »

ሰዎችን ወደ ስህተት ከሚጥሏቸው ነገሮች ውስጥ የጋራ አስተሳሰብ ትልቅ ተፅዕኖ አለው::በተለይ ኢስላም በሚገባ በማይተገበርበት ማህበረሰብ ውስጥ ሁኔታው የተሳሳተ ወይም መጥፎ ቢሆንም «መንጋውን መከተል» እንደ ደንብ ሆኖ ይቆጠራል::አንድ ሰው ምንም እንኳን ትክክለኛውን በኅሊናው ቢያውቀውም ብዙ ሰዎች ስህተት ላይ አይሆኑም በማለት አስተሳሰቡን በተሳሳቱት ሀሳብ በቡድን ተፅዕኖ ፀጥ ያደርግና ከብዙሃኑ ጋር አብሮ ይጓዛል:: በርግጥ የብዙሃኑን አመለካከት ለማንኛውም ነገር መለኪያ አይደለም:: ሰዎች ትክክለኛውን ሃሳብ ከስህተቱ የሚለዩበት ብቸኛ መመሪያ ቁርአን ነው:: በቁርአን መመሪያ ይልቅ ሌሎች መለኪያዎችን ተቀብለው የሚከተሉት

[55] سورة : يوسف
[56] سورة : الأعراف

ሰዎች በከፍተኛ ስህተቶች ውስጥ ይወድቃሉ:: አላህ(ሱ.ወ) በቁርአኑ ከብዙኀኑ ጋር መሄድን አስመልክቶ በግልጽ ያስጠነቅቀናል:-

﴿وَإِن تُطِعْ أَكْثَرَ مَن فِي الْأَرْضِ يُضِلُّوكَ عَن سَبِيلِ اللَّهِ ۚ إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا الظَّنَّ وَإِنْ هُمْ إِلَّا يَخْرُصُونَ﴾[37]

*«ምድር ላይ ባሉት ለብዛኛዎቹን ብትከተል የአላህን መንገድ እንድትስት ያደርጉሃል:: የሚከተሉት ጥርጣሬን ብቻ ነው::ዋሾዎችም ናቸው::»(አል-አንዓም 6:116)*

እያንዳንዱ ሰው በአንድ ነገር ላይ ከተስማማ አብሮ መጓዝ ወሳኝ ነው:: በሚለው አስተሳሰብ ላይ በመመሥረት የአብዛኛውን ሃሳብ የመቀበል መሠረታዊ አስተሳሰብ የከሠረ አስተሳሰብ ነው:: ይህም ማለት፣ አንድ ሰው ከብዙኀኑ ጋር ለመጓዝ ትክክል መሆኑን የሚያውቀውን ካልተወ በስተቀር በሌሎች መወቀስን፣ መወገዘንና መገለልን ይፈራል:: ይህ አስተሳሰብ በወጣት ወይም በጉልማሳ ሰዎች መካከል የሚስተዋል አስተሳሰብ ነው:: በዚህ ምክንያት ብቻ፣የብዙሃኑን እምነት ለማግኘት ሲሉ መላ ህይወታቸውን የኢባዳ ኃላፊነታቸውን መከተል የሚያቅታቸውና የአላህን(ሱ.ወ) ትዕዛዘት ችላ የሚሉ ሰዎች አሉ:: አንድ ሰው ሌሎች የማያስቡትን በማስላት እንደነርሱ ማድረግ የለበትም::በቁርአን አላህ(ሱ.ወ) ሰዎችን ከማንኛውም ጥገኝነት ነፃ ያደርጋቸዋል::አንድ ሰው ተጠሪነቱ ለአላህ(ሱ.ወ) ብቻ ሲሆን፣ በቁርአን እንደሚያምንና ይህንንም እንደሚከተል ለማስረዳት ብቻ ይጠራል:: ሀቁም እያንዳንዱ ሰው ይህንን እውነታ የሚያውቀው ሆኖ ብዙዎች ግን ከብዙሃን ጋር አብሮ የመጓዝ ምክንያቶችን በማቅረብና በአካባቢው ያሉትን ማሞኘት እንችላለን በማለት ራሳቸውን ያታልላሉ::ይሁን እንጂ፣ ወደ ወዲያኛው ዓለም በሚዘዋወሩበት ጊዜ አብረዋቸው የተጓዙት በርካታ የማኀበረሰብ አባላት ራሳቸውን ማዳን እንደማይችሉ ሁሉ እነርሱንም እንደማያድኗቸው ይረዳሉ:: አላህ(ሱ.ወ) ስለ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ሁኔታ በቁርአን ይገልጽልናል:-

---

[37] سورة : الأنعام

كَلَّا لَئِن لَّمْ يَنتَهِ لَنَسْفَعًا بِالنَّاصِيَةِ ﴿١٥﴾ نَاصِيَةٍ كَاذِبَةٍ خَاطِئَةٍ ﴿١٦﴾ فَلْيَدْعُ نَادِيَهُ ﴿١٧﴾
سَنَدْعُ الزَّبَانِيَةَ ﴿١٨﴾ كَلَّا لَا تُطِعْهُ وَاسْجُدْ وَاقْتَرِب ۩ ﴿١٩﴾[58]

*«(ከአደራረጉቱ) ይታቀብ፤) ባይቀጠብ ለናቱን ይዘን (ወደ ገሃነም) እንጎትተዋለን:: ሀሰተኛና ስሕተተኛ የሆነች ለናቱን::ገብረ-አበሮችን ይጥራ::(እኛም ወደ እሳት የሚያስገቡትን) ዘበኞቻችንን እንጠራለን::(ከደርጊቱ ይታቀብ፤)(ሙሐመድ ሆይ! ይህን ከሐዲ) አትታዘዘው:: ለገድ፤)(ወደ አላህ) ተቃረብም::»(አል-ዐለቅ 96 :15-19)*

በዚህ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሰው ከአካባቢው ሰዎች ጋር ለመስማማት የአላህን(ሱ.ወ) ፈቃድ ንቋል በፍርድ ቀንም ፊት ለፊት እንደሚቆም አስበ አያውቅም:: አሁን ከፍተኛ ግምት ከሰጣቸውና ለእነርሱ እምንታ ሲል አላህን(ሱ.ወ) ከናቀበት ብዙሃን ሃይማኖት የለሾች ጋር ወደ እሳት ይሄዳል:: ጉዳዩ ይህ ስለሆነ ከብዙሃኑ ጋር ለመሄድ የሚል ምክንያት በመስጠት ራስዎን አያታሉ፣ ከእምነቱም ራስዎን አያርቁ:: ከቁርአን ትክክል ስለመሆኑ ያወቁትን ፈጽሞ አይተው ብቻዎን የሚያደርጉትም ቢሆን እንኳን ትክክል የሆነውን ይከተሉ:: አላህን(ሱ.ወ) ፈቃድ ለማትረፍ የሚያሳዩት ቁራጥነት በእርሱ ቃላት የምህረት ጥበቃ ሥር ለዘላለም ለመኖር ምክንያቶች መንገድዎ ይሆናሉ::

## « ሳይንስና ስልጣኔን እየተከተልኩ ነው! »

ሰዎች ሃይማኖቻቸውን ችላ እንዲሉ ከሚገፋፏቸው ምክንያቶች አንዱ አላህ(ሱ.ወ) እና የፍርድ ቀንን ወደአለመቀበል ስህተት ውስጥ የሚዶላቸው የሣይንቲስቶች መኖር ነው::ያለንበት ዘመን ሳይንስ ታላላቅ እርምጃዎችን ያሳየበትና፣ በሣይንሳዊ አመለካከትም፣እስካሁን በታሪክ ታይተው የማይታወቁ ነገሮች እየተፈለሰፉ ያሉበት ጊዜ ነው::ከሣይንስና ቴክኖሎጂ ባስገኘልን ዕድል በአላህ(ሱ.ወ) የተፈጠሩላቸው እንከን የለሽ ሥርዓቶችን እየተገነዘብን፣ፍጡራን እንዴት እንደተፈጠሩ የሚገልጽልን እውነታዎች ይበልጥ በቅርበት

[58] سورة : العلق

እየተረዳንና የቁርአንን ተአምር አንድ ባንድ እየተገነዘብን በዓለም ላይ ያለውን ሥርዓትና ቅርፅ እያስተዋልን ነው።

ይሁን እንጂ ሣይንስን ለራሳቸው ዓለማዊ ጥቅም የሚያውሉና በሃይማኖት ላይ ላላቸው ተቃውሞ እንደ ድጋፍ ለመጠቀም የሚሞክሩ ሰዎችም አሉ። እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን እንደ ሣይንቲስት አድርገው ቢያቀርቡም እንኳን ሣይንስን የሚጠቀሙበት እውነትን ለማጥናትና ለማወቅ ሣይሆን የራሳቸውን አመለካከት (አይዲኦሎጂ) ለመደገፍ ነው።በዓለም ላይ ያሉትን የሕያዋን ነገሮችን እንከን የለሽ አፈጣጠር አስደናቂ/ ተአምራዊ/ተፈጥሮአዊ ጠባዮችን ችላ በማለት እያንዳንዱ ነገር የተፈጠረው በራሱና በአጋጣሚ እንደመጣ አድርገው የተሳሳተ አስተሳሰብ ያቀርባሉ። ዓላማቸውም ራሳ ው የአላህን(ሱ.ወ) መኖር ችላ ለማለትና ማኅበረሰቦቻቸውም እንዲሁ እንዲያደርጉ ነው።በዚህ መንገድም አንዱ ለሌላው ኃላፊነት የሌላቸውን ግለሰቦችን የሚገኝ ብት ማኅበረሰብ በመመሥረት ማንኛውም ዓይነት የስነምግባር ዝቅጠት እንዲስፋፋ የማድረግ ፍላጐት አላቸው።የራሳቸውን ሀሳቦች ብቻ ለማሠራጪት በቀረጡት በእነዚህ ሣይንቲስቶች ተፅዕኖ ሥር በርካታ ኅብረተሰብ በቀላሉ ይወድቃል።ሣይንቲስቶችም በማንኛውም ርዕስ ላይ ምርጥ ግምገማ ለማድረግ ብቃት እንዳላቸው ተደርጐ ይቆጠራል። ይህ ግን የተሳሳተ ግምት ነው። በርግጥ ሣይንስን ለእውነተኛ ዓላማ የሚጠቀሙበትና በዕውቀታቸው በብዙ ነገሮች ላይ ልንጠቀም የምንችልባቸው ሳይንቲስቶች አሉ።ይሁን እንጂ፣ በሣይንስ አካባቢ ከዚህ ክፍል ውጭ በመሆን እውነታዎችን አጣመውና ለራሳቸው ዓለማዊ ጥቅም ሲሉ ሌሎችን የሚያሳስቱ ሰዎች አሉ። በዚህ ምክንያት ሳይንቲስቶች፣እንደማንኛውም ሌላ ሰው፣ የሚዳኙት በሣይንሳዊ ሠነዶች ወይም በአጠኑት የትምህርት ዓይነት ሣይሆን የያዙትን ዕውቀት ለተፈጠሩበት ዓላማ በማዋልና ባለመዋላቸው፣ ህይወታቸውም አላህ(ሱ.ወ) በሚፈቅደው መሠረት በመምራታቸው መሆን ይገባዋል። በአላህ(ሱ.ወ) ለሚያምን ሰው ይህ ትክክለኛው አቀራረብ ነው። ቀደም ሲል አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን ብዙሃኑን መከተል ጉዳ መሆኑን እንዳየነው ትክክለኛ እምነትን የሚቃወመውም ብዙሃኑ ነው። ሁኔታው ይህ ስለሆነ አንድ ሰው ዝርዝር

ነገሮችን ሳይመረምር፣ ሳያጠናና የሌሎችን ቃል መቀበል ሳይኖርበት፣ በራሱ ዕውቀትና ኀሊና ላይ በመመሥረት ወደ ትክክለኛው መደምደሚያ መድረስ ይገባዋል።በሚከተሉት የቁርአን አንቀጾች ላይ አላህ(ሱ.ወ) ይህን አጉልቶ ያሳየናል፡-

وَلَا تَقْفُ مَا لَيْسَ لَكَ بِهِۦ عِلْمٌ ۚ إِنَّ ٱلسَّمْعَ وَٱلْبَصَرَ وَٱلْفُؤَادَ كُلُّ أُو۟لَٰٓئِكَ كَانَ عَنْهُ مَسْـُٔولًا ﴿٣٦﴾[59]

*«የማታውቀውን ነገር አትከተል።ጆሮ፣ዓይንና ልቦና ሁሉም(በእነተ ትንባሌ በደር ጊታቸው ተጠያቂዎች ናቸውና።»(አል-ኢስራእ 17:36)*

አንድ ሰው አላህ(ሱ.ወ) እንደሚያስተምረው ትክክለኛውን ነገር የመቀበልና ሌሎችም እንዲቀበሉ የመምከር ኃላፊነት አለበት። ይህ እውነታው ሲሆን፣ ራስዎንና በአካባቢዎ የሚገኙትን ለማምንት ምክንያቶች ለማስቀደም መምከር በወዲያኛው ዓለም ምንም ጥቅም አያስገኝም። አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን ምንጊዜም ሰዎችን ወደ አለማመን የሚጋብዙ ሰዎች ስለመኖራቸውና በዚህም ጉዳይ ላይ ብዙሃን ሰዎችን የሚያዘናጉ ተስፋዎችን የሚያቀርቡ መሆናቸውን አስመልክቶ ማስጠንቀቂያ ይሰጠናል። እንዲህ ያሉት ሰዎችን እነርሱም የሚከተሉት ሥቃይ እንደሚያገኛቸው ይገልጽልናል፡-

﴿١١﴾ وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لِلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱتَّبِعُوا۟ سَبِيلَنَا وَلْنَحْمِلْ خَطَٰيَٰكُمْ وَمَا هُم
بِحَٰمِلِينَ مِنْ خَطَٰيَٰهُم مِّن شَىْءٍ ۖ إِنَّهُمْ لَكَٰذِبُونَ ﴿١٢﴾ وَلَيَحْمِلُنَّ أَثْقَالَهُمْ وَأَثْقَالًا
مَّعَ أَثْقَالِهِمْ ۖ وَلَيُسْـَٔلُنَّ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ عَمَّا كَانُوا۟ يَفْتَرُونَ ﴿١٣﴾[60]

*«እነዚያ የካዱት ለእነዚያ ለአመኑት፡-«የኛን መንገድ ተከተሉ። ኃጢአቶቻችሁን እንሸከምላችኋለን።» አሉ።ከሓጢአቶቻቸው ቅንጣት ታክል አያሸከሙም። እነርሱም ውሸታሞች ናቸው።የራሳቸውን የሓጢአት ሸክም«(የነዚያን ያጠመሟቸውን ሰዎች) ሸክምም ከራሳቸው ጋር አዳብለው ይሸከማሉ። በትንሳኤ ቀንም ይቀጥፉት ስለነበረው (ሁሉ ይጠየቃሉ)።»( አል-ዐንከቡት 29:12-13)*

[59] سورة : الإسراء
[60] سورة : العنكبوت

## ራስን ማታለልና መዘዙ!

በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ ነቢዩ ኢብራሂም(ዐ.ሰ) የአላህን(ሱ.ወ) መኖር፣ ታላቅነት እንደተገነዘቡ፣በራሳቸው ልቦና ወዲያውኑ እርሱን የማገልገልን አስፈላጊነት መረዳታቸውን ገልጾልናል:: እያንዳንዱ ሰውም ኅሊና እንዳለው ማወቅ አለብን::ኅሊና የሌላቸው ተብለው የሚቆጠሩትን ኅሊናቸው በጣም ከዳበረው ሰዎች የሚለያቸው ነገር የፊተኞቹ እውነት መሆኑን ለሚያውቁት ነገር ዓይናቸውን ሲጨፍኑና ጆሮአቸውን ሲደፍኑ! የኋለኞቹ ግን ይህንን አያደርጉም::

በቁርአን በአላህ(ሱ.ወ) እንደተመሰገኑትና በእያንዳንዷ የኅሊናቸውን ድምፅ እንደሚያዳምጡት እንደ ኢብራሂም(ዐ.ሰ) ያሉ ነቢያት ቀጥተኛ ነገርን በመከተልና በወዲያኛው ዓለም የሚገኘውን ምርጥ ዋጋ ተስፋ ስለሚያደርጉና ፣የተዋበና ሰለማዊ ሕይወትን ይመራሉ::ኅሊናቸውን ያኮሰሹ ሰዎች በአንጻሩ የመከራ ያጋጥማቸዋል:: እነዚህ ሰዎች ትክክለኛና እውነት የሆነውን ቀና መንገድ ባለመከተል በወዲያኛው ዓለም የሚመጣባቸውን ከባድ ቅጣት በማወቅ በድብቅ ሥቃይ፣የተሰወረ የኅሊና ሥቃይ ይበዛባቸዋል::የትም ሄዱ፣ምንም ሠሩ፣ ይህ ሥቃይ አይቀርላቸውም::በዓለም ከፍተኛውን ንብረት ቢኖራቸውና ከአንዱ አገር ወደሌላ ቢጓዙም እንኳ ከዚህ መንፈስ ውጥረት በፍጹም አይድኑም::

በጥሞናና በሐቅ ካየነው የዚህ የኅሊና ሥቃይ ምንጭ አላህ(ሱ.ወ) እነዚህ ሰዎች ከተሳሳተ መንገዶች እንዲመለሱ ለማድረግ ከአላህ(ሱ.ወ) ዘንድ የተሰጠ ከፍተኛማስጠንቀቂያ ነው:: በዚህ ምክንያት፣ ሰዎች ወደ ኅሊናቸው እንዲመለሱና እውነተኛ ንስሐ ገብተው ጸባያቸውን እንዲያርሙ ስለሚያርግ ነው::ሐቀኝነታቸውን ለተው ሰዎች ግን ይህ እውነተኛው የሥቃይ ቅጣት ነው::የሚያጋጥማቸውን የሥቃይ ቅጣት ምክንያት ቢያውቁትም! ሁኔታውን ለማስተካከል እርምጃዎችን ከመውሰድ ይልቅ ምክንያቱን ችላ ይሉታል::

በዚህ ተቃርኖ የተነሳ በሕይወታቸው ላይ በሚደርሰው ውጥረት ምክንያት በፍጹም በእውነት በደስታና በሰላም የተረጋጋ ሕይወት ሊኖሩ አይችሉም።

ስለዚህ፣በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ እንዳልነው፣እውነትን ቢያውቁትም እንኳን ለመረዳት ችላ በማለትና በእምቢተኝነት ራሳቸውን የሚያታልሉ ሰዎች መላ ሕይወታቸውን የሚኖሩት በመንፈሳዊ ሥቃይና ውጥረት ውስጥ ነው። ኅሊናዎቻቸው በዚህ መንፈሳዊ ውጥረት የታወከና የሥቃይ ቅጣት የሚያስጨንቀው ሆኖ ሳለ፣ ምኞት ማጣታቸውን በሰው ሠራሽ ደስታዎች ለማታለል ይሞክሩ እንጂ፣ የኅሊና ሥቃይ ቅጣትን ማቀለያው ብቸኛ መንገድ መፀፀትና ራስን ለአላህ(ሱ.ወ) ሙሉ በሙሉ አሳልፎ መስጥት ነው ፈውሱ።

እርስዎም ኅሊናዎን ከማድመጥ ይልቅ በተለያዩ ምክንያቶች ራስዎን በማታለል የራስዎን ግላዊ ምኞቶችና ስሜት ከተከተሉ ራስዎን ከርሱ ለማዳን የማይችሉት ውስጣዊ የቅጣት ሥቃይ ያጋጥሞታል።ይህ ዓይነቱ ራስን ማታለል የሚያስከትለው ውጤት እስከፊነት በዚህ ዓለም ላይ የተገደበ ሳይሆን አላህ(ሱ.ወ) ሳዘጋጀው መጻኢ ዓለም የሚቀጥል ነው። ራሳቸውን የሚያታልሉና ስለ አኺራ ችላ የሚሉ እነዚህ ንቃተ ህሊናቸውን ያኮላሹ ግለሰቦች በወዲያኛው ዓለምም ከፍተኛ ሥቃይና ሐዘን የሚደርስባቸው መሆኑ ቅንጣት ጥርጣሬ የለውም። በርግጥ በቁርአን ላይ የፍርዱ(አኺራ) ቀን «የትርፍና የኪሣራ ቀን» ተብሎ ይጠቀሳል፦

يَوْمَ يَجْمَعُكُمْ لِيَوْمِ ٱلْجَمْعِ ۖ ذَٰلِكَ يَوْمُ ٱلتَّغَابُنِ ۗ وَمَن يُؤْمِنۢ بِٱللَّهِ وَيَعْمَلْ صَٰلِحًا يُكَفِّرْ
عَنْهُ سَيِّـَٔاتِهِۦ وَيُدْخِلْهُ جَنَّٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدًا ۚ ذَٰلِكَ ٱلْفَوْزُ
ٱلْعَظِيمُ ۝ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ وَكَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَآ أُو۟لَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلنَّارِ خَٰلِدِينَ فِيهَا ۖ وَبِئْسَ
ٱلْمَصِيرُ[61] ۝

---

[61] سورة : التغابن

*«እናንተን ለመሰብሰቢያው ቀን የሚሰበስብበትን (እጅግ ለከፈረ) ዕለት(እለተ ትንሳኤ (አስታውሱ):: የሥራ ውጤት መዳረሻ(ሁሉም የዘራውን የሚያጭድበት) ዕለት ነው::በአላህ ያመነና መልካም ተግባራትን የሠራ (አላህ) ኃጢአቱን ይሰርዝለታል:: ከሥርቿ ወንዞች ከሚፈሱባት ጀነትም ያስገባዋል:: በውስጧ ዘንተ ዓለም ይኖራሉ:: ይህ ትልቅ ስኬታማነት ነው:: እነዚያ የካዱትና አንቀጾቻችንን ያስተባበሉት እነርሱ የእሳት ሰዎች ናቸው:: በውስጧ ዘወትር ይኖራሉ:: (ገሃነም) እጅግ ለከፊ መመለሻ ናት!»(ሱራቱ አት-ተጋቡን 64:9-10)*

በነዚህ ሱራዎች ላይ የተገለጸው ኪሣራው በማያምነው ግለሰብ ሞት ይጀምርና እስከ ትንሳኤ በመቀጠል እውነተኛው ቤቱ ጀሃነም መሆኑን ካወቀ በኋላ ትጣቱን ይጨምራል::ቁርአን በሠይጣን ቃልኪዳኖች የተሞንና ዓለማዊ አኗኗርን እንደምክንያት በማቅረብ ራሳቸውን የሚያታልሉ ሰዎች በጀሃነም የሚያጋጥማቸውን አንዳንድ ነገሮች ይነግረናል:: ስለ ሞት ሲታሰብ ጭንቀት የሚመጣው በእውነቱ የሚያስጨንቅ ስለሆነ ነው:: ለዚህ ነው ላለማሰብ እንዳናስብ የምንሞክረው! ጡሩንባው ይነፋል!ይህ የዛቻው ዕለት ነው:: እያንዳንዱ ግለሰብ ከነጂና ከምሥክር ጋር አብሮ ይመጣል:: በዚህ ረገድ «ሥርዓት የማትጠብቅ ስለነበርክ!ዛሬ መሸፈኛህን ስለገፈፍንልህ! ቁልጭ ብለህ ታየህ::» ነፍስ የስራዋን ዋጋ ለመቀበል ከአላህ ፊት በሁለት መላእክት ታጅባ ትቀርባለች::አንደኛው ወደ ፍርዱ ቦታ ይነዳታል::ሌላኛው ይመሰክርባታል:: ዛሬ ላይ ስለዚያ ታላቅ ቀን እንድናስብበት ታውጇል:: ክስተቱን አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን እንዲህ ይነግረናል:-

١٨ وَجَآءَتۡ سَكۡرَةُ ٱلۡمَوۡتِ بِٱلۡحَقِّۖ ذَٰلِكَ مَا كُنتَ مِنۡهُ تَحِيدُ ١٩ وَنُفِخَ فِي ٱلصُّورِۚ ذَٰلِكَ يَوۡمُ
ٱلۡوَعِيدِ ٢٠ وَجَآءَتۡ كُلُّ نَفۡسٖ مَّعَهَا سَآئِقٞ وَشَهِيدٞ ٢١ لَّقَدۡ كُنتَ فِي غَفۡلَةٖ مِّنۡ هَٰذَا
فَكَشَفۡنَا عَنكَ غِطَآءَكَ فَبَصَرُكَ ٱلۡيَوۡمَ حَدِيدٞ ٢٢ وَقَالَ قَرِينُهُۥ هَٰذَا مَا لَدَيَّ عَتِيدٌ ٢٣
أَلۡقِيَا فِي جَهَنَّمَ كُلَّ كَفَّارٍ عَنِيدٖ ٢٤ مَّنَّاعٖ لِّلۡخَيۡرِ مُعۡتَدٖ مُّرِيبٍ ٢٥ ٱلَّذِي جَعَلَ مَعَ ٱللَّهِ

إِلَٰهًا ءَاخَرَ فَأَلْقِيَاهُ فِي ٱلْعَذَابِ ٱلشَّدِيدِ ﴿٢٦﴾ ۞ قَالَ قَرِينُهُۥ رَبَّنَا مَآ أَطْغَيْتُهُۥ وَلَٰكِن كَانَ فِي
ضَلَٰلٍۭ بَعِيدٍ ﴿٢٧﴾ قَالَ لَا تَخْتَصِمُوا۟ لَدَىَّ وَقَدْ قَدَّمْتُ إِلَيْكُم بِٱلْوَعِيدِ ﴿٢٨﴾ مَا يُبَدَّلُ ٱلْقَوْلُ
لَدَىَّ وَمَآ أَنَا۠ بِظَلَّٰمٍ لِّلْعَبِيدِ ﴿٢٩﴾ يَوْمَ نَقُولُ لِجَهَنَّمَ هَلِ ٱمْتَلَأْتِ وَتَقُولُ هَلْ مِن مَّزِيدٍ ﴿٣٠﴾[62]

***«ማዕረ ሞት በእርግጥም ይመጣበታል::«ይህ ትሸሸው የነበረው (ሞት) ነው::[63]»(ይባላልም):: በቀንደም ውስጥ ይነፋል[64]::ያ (ቀን) የዛቻው (መፈፀሚያ) ቀን ይሆናል:: እያንዳንዷ ነፍስ አንደኛዋ ነጂ ሌላኛዋ መስካሪ በሆኑ (ሁለት መላእክት) ታጅባ ትመጣለች::» (ለኃጢአተኛም) :- ከዚህ(ቀን) ተዘናግተህ ነበር:: አሁን ግርዶህን አንስተንልሃል:: ዛሬ የማየት ኃይልህ ጠንካራ ነው::»(ይባላል):: ባልደረባው (መልአኩም):- «ይህ [1](የሥራ መዝገብ) (በርሱ ላይ ይመሰክር ዘንድ) በእኔ የተሰናዳ ነው::» ይላል::«(ሐቅን) የተቀናቀነ ከሐዲን ሁሉ ገሀነም ውስጥ ወርውሩ::» ጸድቅን ከልካይ ወሰን አላፊና ተጠራጣሪ የነበረን (ከሐዲ ሁሉ) «ያን ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ ያደረገን:: ከብርቱ ቅጣት ውስጥ ወርውሩት::» (የሚል ትእዛዝ ይተላለፋል):: ባልደረባው (ሰይጣንም):- «ወሰን አላፊ አላደረግኩትም::እርሱ (ራሱ) (ከሐቅ በእጅጉ) በራቀ ጥመት ውስጥ ነበር::» (አላህም) ይላቸዋል:-«ዛሬ ከእኔ ዘንድ አትወዛገቡ:: ማስጠንቀቂያ ልኬላችሁ ነበር::»ከእኔ ዘንድ ቃሉ (የተላለፈው ፍርድ) አይለወጥም::ባሪያዎቼን በዳይም አይደለሁም:: ገሀነምን:-«ሞላሽን?» በማለት የምንጠይቅበትንና:- «ተጨማሪ አለን?» የምትልበትን ቀን (አስታውስ)::»(ሱረቱል ቃፍ 50:19-30)***

አንድ ሰው በዚህ ዓለም ባለው ጊዜ ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ስለሚፈተን፣ ይህም የፈተና ወቅት፣ባማካይ፣ለስድስት ወይም ሰባት አሥርታት ከሚለካ ጊዜ ላይ የተውጣጣ ነው:: የሰው የዘላለማዊ ሕይወት ጠባይ በዚህ የፈተና ወቅት ይወሰናል:: አንድ ሰው ይህን አጭር፣ግን እጅግ በጣም አስፈላጊ፣ወቅት ራስን በማታለል ካባከነ ፈተናውን ይወድቃል:: በተቃራኒው ደግሞ፣ከእውነቱ መሸሸ

---

[62] سورة : ق
[63] ሞት ለማንም የማይቀር ፅዋ ነው::ከሞት የሚያመልጥ የለም::ሞት ለሙዕሚናት ወደ ወደ ተድላና ስኬት፣ለከሐዲያን ደግሞ ወደ ውድቀት መረማመጃ ድልድይ ነው::
[64] የፍርዱ ቀን መጀመር በቀንዱ መነፋት ይታወጃል::ሁሉም ነፍሶች በመላእክት ታጅበው ወደ ፍርዱ ቦታ ይተማሉ::

በስውየው በራሱ ላይ ነው አደጋው:: ኅሊናውን አደንዝዞ በማይጨበጡ ልዩ ልዩ ምክንያቶችና ሱጂኦች(አመክንዮዎች) ራሱን ለማጽናናት በሚሞክርበት በእያንዳንዱ ጊዜ በርግጥ ከባድ ኪሣራ ላይ እየወደቀ ነው:: አላህ(ሱ.ወ) ካልፈቀደው፣የዚህ የዕውቀት ማጣት ውጤቱ እርይታ ሊኖረው የማይችል ኪሳራ ይሆናል:: ሁኔታው ይህ ስለሆነ ራስን ማታለል አስፈላጊ አይደለም:: በእያንዳንዷ ግልጽ ዕውቀትና ጥንቃቄ ላይ ተመሥርቶ አላህን(ሱ.ወ) የማግኘት፣ለዲኑ ያለበትን የኃላፊነት ግዴታ መወጣት ያሻል::

እውነታው፡- አንድ ሰው ራሱን በማታለሉ እውነቱን አይለውጥም::ኃላፊነቱን ሊያስወግድ አይችልም:: አንድ ሰው የኅሊናውን ድምፅ (ደወል) ከሰማና የአላህን(ሱ.ወ) መመሪያ-ቁርኣንን ከተከተለ ሁሉም ነገር ለርሱ-ይቻላል! ለእውነተኛ አማኝ ለአኼራ ተግቶ በጥሞና ከመሥራት በቀር ሌላ መንገድ አይፈልግም:: ለአንድ ሰው መልካሙና በጣም ጠቃሚው መንገድ እያንዳንዷን ጊዜ ወደሞትና ወደ ፍርድ ቀን እንደምታቀርበውና ማንኛውም በአዕምሮው የሚብሰለሰል ሀሳብና ድርጊት በአላህ(ሱ.ወ) እንደምትታወቅ ባለማቋረጥ ማስታወስ ነው::

ይህ ከልብ ወደ አላህ(ሱ.ወ) የሚመራ መንገድና በርግጥ በጣም ቀላል መሆኑንም ይወቁ:: ከጥቂት ማሰብና ግልጽ ውሳኔ በኋላ አንድ ሰው ያ ውሳኔ በሚመጣው ግልጽ ዕውቀት መላ ሕይወቱን ሊኖር ይችላል:: ያንን ግልጽ ዕውቀት አንድ ጊዜ ካተረፈ በኋላ ራሱን በማታለል የከፋ ጥፋት እንዲያደርስ አይፈቅድለትም:: ራስዎን ማታለል ልክ በእሳት እንደመጫወት አድርገው ይቁጠሩት:: አንድ ሰው እየተደሰተና ሙሉ በሙሉ ራሱን ለዓለማዊ ነገሮች አስገዝቶ ባለበት ሰዓት! በማንኛውም ጊዜ ሕይወቱን ሊወስዱ የመጡ መላዕክቱ ከጉኑ ሊያገኛቸው እንደሚችል አይዘንጋ:: በቁርአን ላይ «በጭካኔ ንቀል» ተብሎ እንደተገለጸው ፣እንዲህ ተብለው መላእክቱ ሲላኩ ይህ ጨዋታና መሰል ሽፍጥ ተጋላጭ ላለመሆኑ ምን ዋስትና አለው? «ምን ያህል ጥሩ ነገር ሠርቻለሁ?» ሊል ይችላል:: በዚህ ዓለም ላይ መላ ሕይወቴን በልቻለሁ፣ ጠጥቻለሁ፣ ራሴን አስደስቻለሁ እናም ኃላፊነቴንና የታዛዥነቴን

ግጼታዬን ችላ ብያለሁ ሊል ይችላል? በርግጥ አይችልም።ይህ ሀሳብ ደንታ ለሌለው ሰው ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም። በተቃራኒው ደግሞ፣ በዚያን ጊዜ ሰውዬው ሊገለጽ የማይችል ጭንቅና ሃሳብ የሚያጋጥመው ሲሆን፣ ዘላለማዊ የሥቃይ ቅጣትንም ይቀበላል። ይህ ለአንዲት አፍታ እንኳን ሊናቅ የማይገባው ሐቅ ነው። አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን ላይ ራሳቸውን የሚያታልሉ ሰዎችን ፀፀትና ረዳት የማጣት ሁኔታ በሚከተለው አኳኋን ይገልጸዋል፡-

﴿وَأَنِيبُوٓا۟ إِلَىٰ رَبِّكُمْ وَأَسْلِمُوا۟ لَهُۥ مِن قَبْلِ أَن يَأْتِيَكُمُ ٱلْعَذَابُ ثُمَّ لَا تُنصَرُونَ ﴿٥٤﴾ وَٱتَّبِعُوٓا۟ أَحْسَنَ مَآ أُنزِلَ إِلَيْكُم مِّن رَّبِّكُم مِّن قَبْلِ أَن يَأْتِيَكُمُ ٱلْعَذَابُ بَغْتَةً وَأَنتُمْ لَا تَشْعُرُونَ ﴿٥٥﴾ أَن تَقُولَ نَفْسٌ يَٰحَسْرَتَىٰ عَلَىٰ مَا فَرَّطتُ فِى جَنۢبِ ٱللَّهِ وَإِن كُنتُ لَمِنَ ٱلسَّٰخِرِينَ ﴿٥٦﴾ أَوْ تَقُولَ لَوْ أَنَّ ٱللَّهَ هَدَىٰنِى لَكُنتُ مِنَ ٱلْمُتَّقِينَ ﴿٥٧﴾ أَوْ تَقُولَ حِينَ تَرَى ٱلْعَذَابَ لَوْ أَنَّ لِى كَرَّةً فَأَكُونَ مِنَ ٱلْمُحْسِنِينَ[65] ﴿٥٨﴾

*«ቅጣቱ ወደ ናንተ ከመምጣቱና (ከቅጣት የሚያድናችሁ) ረዳት የማታገኙ ከመሆናችሁ በፊት ወደ ጌታችሁ (በንስሐ) ተመለሱ። ለርሱ እጅ ስጡም።ተዘናግታችሁ በድንገት ቅጣቱ ሳይመጣባችሁ በፊት ከጌታችሁ ወደናንተ የተወረደውን መልካም (መዕክቱ) ከሚሳለቁት ነበርኩ።» ከማለቷ ወይም ደግሞ ቅጣቱን በምታይበት ወቅት «ሌላ (የሕይወት) ዕድል ቢሰጠኝ ኖሮ ከመልካም ሠሪዎች እሆን ነበር።» ከማለቷ በፊት (ወደ ሰላህ ተመለሱ።)»(አዝ-ዙመር 39:54-58)*

*-ተፈጸመ-*

ረመዳን 1428 ዓመተ ሂጅራ (መስከረም 2000 ዓመተ ልደት)

የጸራሲው የኢንተርኔት ድህረ-ገጽ www.harunyahya.com ነው



[65] سورة : الزمر